ፍኖተ
# ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ ሚያዚያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም. ዋጋ ብር 6.00

2ኛ ዓመት ቅጽ.2 ቁ.39

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!



## ኢህአዴግ እውቀቱም ወዳጁም ማስመሰልና ጉልበቱ ነው!!

አቶ ስዩም መንገሻ ወ/ሰማያት

6

# የውድሮ ዊልሰን ማዕከልና የአሜሪካን ኤምባሲ ተወካዮች ከአንድነት ፓርቲ ጋር ተነጋገሩ



16

## ጋምቤላ የሼክ መሐመድ አላሙዲን ሰራተኞች ላይ በደረሰው ጥቃት 3 የውጪ ሀገር ዜጎች ና 5 ኢትዮጵያውያን ተገደሉ

13

## ብርሃንና ሰላም ለሳንሱር የሚዳርገውን ውል ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ እንዲፈርም የአንድ ሳምንት ጊዜ ሰጠ

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ለሳንሱር የሚዳርገውን አዲስ ውል የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ አሳታሚ አንድነት ፓርቲ እንዲፈርም የአንድ ሳምንት ጊዜ ሰጠ ፡፡

የኢህአዴግ መንግስት አስቀርቼዋለሁ የሚለውንና በሕገመንግስቱ የተከለከለውን ቅድመ ምርመራ(ሳንሱር) በድጋሚ የሚያስጀምር ውል ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት መዘጋጀቱ ውጥረት ፈጥሮ መሰንበቱ የሚታወስ ሲሆን አሳታሚዎች ከብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ጋር ውይይት መጀመራቸውንና ማተሚያ ቤቱ ተጨማሪ ጊዜ እንሚሰጥ ቅርበት ካላቸው ምንጮች ተሰምቶ ነበር፡፡ ለፍኖተ ነፃነት ትላንት ከማተሚያ ቤቱ የደረሰው ማስጠንቀቂያ አዘል ደብዳቤ ግን በአሳታሚዎችና በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት መሀከል የነበረውን ውጥረት የሚያባብስ ሆኗል፡፡

ጉዳዩን አስመልክቶ ያነጋገርናቸው የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ኤዲቶሪያል ቦርድ አባል የሆኑት አቶ ዳንኤል ተፈራ ድርጅቱ ያዘጋጀው ውል ሕገመንግስቱ የሚጥስና ቅድመ ምርመራን የሚያሰፍን መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ወደ ገፅ 16 ዞሯል

## የሰሜን ጐንደር ሕዝብ የቁም እስረኛ ሆኗል

13

## የውሸት ዕድገት መሐንዲሶች

10



# የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ተፈረደበት

ወደ 8 ዞሯል

## ትላንት ንግድ ባንክ ገንዘባቸውን በሚያወጡ ደንበኞች ተጨናንቆ ዋለ

በትላንትናው እለት በአዲስ አበባ የሚገኙ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች ገንዘባቸውን በሚያወጡ ደንበኞች ሰልፍ ተጨናንቀው መዋላቸውን የዝግጅት ክፍላችን ተባባሪ ሪፖርተር ዘገበ፡፡

ሪፖርተራችን በተዘዋወረባቸው ተክለሃይማኖት፣ፒያሳና አራት ኪሎ በሚገኙት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች እንደተመለከተው በርካታ የባንኩ ደንበኞች ገንዘባቸውን ለማንቀሳቀስ

ወደ 16 ዞሯል

## ምክር ቤቱ ከአጀንዳ ክርክር እስከ እጅ ለማዉጣት መወከል

2

## የኢትዮጵያ መምህራን ጥያቄና የትምህርት ሥራ እውን መምህራን የደሞዝ ጭማሪ አልጠየቁም?

5

ኢትዮጵያ ለሦስት መንግሥታት ያክል "የህዝብ ተወካዮች" የሚመደቡበት ስርዓት አስተናግዳለች፡፡ በነዚህ አመታት የተሻለ የህዝብ ተወካይነት የነበራቸው "ህዝብ አልወከላቸውም" የተባሉት የአፄ ኃይለ ሥላሴ ሁለቱ ምክር ቤት መሆናቸው አስገርሟል፡፡ የነገሩ አካሄድ ወደ አንድ ጫፍ መጥቶ የህዝብ ተወካዮች የተባሉት ሰዎች ከሀገር ይልቅ ፓርቲ ብቻ የሚያስቀድሙበት ደረጃ ላይ ደረስናል የሚለው ሰለሞን ስዩም አሁን አሁንማ ሰዎቹ እጅ ለማውጣት ብቻ የተቀመጡ ይመስላል ይለናል፡፡



ሰለሞን ስዩም
era4st@yahoo.com

# ምክር ቤቱ ከአጀንዳ ክርክር እስከ እጅ ለማዉጣት መወከል

## ህገ መንግሥቱ ምን ይላል?

የኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 45 የኤፌዴሪ መንግሥት ፖርላሜንታዊ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በአንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 4 ደግሞ «የምክር ቤቱ አባላት የመላው ሕዝብ ተወካዮች ናቸው» ሲል ይደነግጋል፡፡ ሕገ-መንግሥቱም የምክር ቤት አባላቱ ተገዥነት «ለህገ መንግሥቱ»፣ «ለሕዝብ» እንዲሁም «ለህሊናቸው ብቻ ይሆናል» ሲል ይደመድማል፡፡

ይህንን በሚመለከት ጥናት የሚያደርጉ ምሁራን ፖርላማው ከሚሸራቸው ህገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎች የመጀመሪያው «ለህገ መንግሥቱ» ታማኝ መሆን አለባቸው የሚለውን ነው፡፡ በ2001 ዓ.ም ምክር ቤቱ ሥልጣኑን ቀስ በቀስ እየሸረሸረ ለሥራ አስፈፃሚው ሰጥቷል የሚያስብለውን ድምጽ ሰጥቶ ነበር፡፡ በአመቱ «ፖርላማው ከሕገ-መንግሥቱ ጋር የሚጋጩ ሕጎችን እያወጣ ነው» ያስባለው የመንግሥት ቤትን በውል ተከራይተው ያሉ ሰዎች ግዴታቸውን የማይወጡ ከሆነ እንዲሁም « ህገ -ወጥ» ግንባታ አድርገዋል ብሎ ሲያምን የማፍረስ ኃላፊነት እንዲኖረው ማድረጉ ነበር፡፡ ኤጀንሲው ከሕግ አውጪው የተሰጠው ስልጣን ከህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 26 ጋር በግልጽ ይጋጭ እንደነበር ተነግሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን የሰጡት የቀድሞ የም/ቤቱ አባል እና የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ የወጭ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ተመስገን ዘውዴ ህጉ የፍርድ ቤት ሥልጣን በመሸርሸር ተወዳዳሪ እንደሌለው" ይናገራሉ፡፡ አቶ ተመስገን « የሁላችንም እኩልነት በፍርድ ቤት ፊት ሆኖ ሳለ፣ የፍርድ ሂደቱ --- process of law) ታጥፎ አንድ ተቋም ራሱ ከሳሽ፣ ራሱ ፈራጅ በሆነበት ሁኔታ ምን የዜግነት ዋስትና አለን ?» በማለት ይጠይቃሉ፡፡

ሌላው የምክር ቤቱን «ለህገ-መንግሥት ብቻ» ተጠያቂነትን ከባድ ጥያቄ የሚጋርጥበት በፀረ-ሽብር ህጉ አፀዳደቅ የታየው ሁኔታና በአዋጁ ውስጥ ተካተዋል የሚባሉት አንዳንድ አንቀፆች ናቸው፡፡ በህጉ ውስጥ የተካተቱትን አንቀፆች መታገስ ያቃታቸው የወቅቱ የፖርላማ አባልና የኤፌዴን ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ለፖሊስ የተሰጠውን መብት በተመለከተ «አገራችንን ለጎበዝ አለቆች እና ለፖሊሶች አሳልፈን ልንሰጥ ነው» በማለት የምክር ቤቱን ግድ የለሽነት ተቃውመዋል፡፡ በወቅቱ ምክር ቤቱ ኃላፊነት በጎደለው መልኩ ለሥራ አስፈፃሚው «ህጋዊ አፈና» ማመቻቸቱ አነጋግሯል፡፡

## የፓርቲ የፖለቲካ ቁርጠኘነት ወይስ የህሊና ታማኘነት

በአፄ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግሥት የነበሩት የፖርላማ አባላት ስለ ሁለት ነገር ይጨነቁ እንደነበር ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ያብራራሉ፡፡ በወቅቱ የነበሩት አባላት በዋነኝነት ለህግ የበላይነት ከመቆርቆራቸውም በላይ ፈሪሀ- እግዚአብሔር የነበራቸው በመሆኑ ለእውነት ወገናዊነት እንደነበራቸው ያብራራሉ፡፡ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ በበኩላቸው "ይህ ጉዳይ ከመንግሥት እና ከሀገር ታማኝነት ወደ አንዱ በማድላት የሚገለፅ ነው» ይላሉ፡፡ በዶ/ር ዳኛቸው ትንተና መሠረት የምክር ቤቱ አባላት ታማኝነት ሀገር (State) ወይም በመንግሥት (government) መካከል ባላቸው የማበላለጥ ንድፍ መሆኑን ያወሳሉ፡፡ የህዝብ ተወካዮች ባለው ነባራዊ ባህልና የፖለቲካ ከባቢ ለሀገር ጉዳይ ቅድሚያ የሚሰጡ ከሆነ ለመንግሥት (government) ያለው ቅድሚያ (Priority) ይቀንሳል፡፡ «ያ ማለት በእጅ አዙር ፓርቲን /ሥርዓትን መገንባት ነው» ይላል፡፡ ሮቤርት ፕያቦደር፡፡ የሮቤርት ፕያቦደር ሃሳብ በፖርላማ ያቀረቡትን ሃሳቦች ካለቸው ሀገራዊ ፋይዳ በመገምገም አባላቱ ከተወከሉበት ፓርቲ ይልቅ ሀገራዊ ፋይዳው ጎልቶ በመታየቱ ቢደግፉት ያ ሀገራዊ ተቆርቋሪነት ይሆናል፡፡

« New perspectives on the house of representatives» በተባለ መጽሐፋቸው እንዳካተቱት የተወካዮቹ ህሊና (nescience)ማለት ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ሃሳቦች ይሆናሉ፡፡

## Precooked decision

ኔልሰን ፓልስብር « Cabinet Ministers and parliamentary government» በተባለ ጽሑፋቸው የስዊድን የህግ አውጭው አሰራር ለህግ የሚያደርገውን ጥንቃቄ አብራርተዋል፡፡ በስዊድን ሁኔታ ህግ የሚወጣው "ሮያል ኮሚሽን" በተባለ ልዩ ተቋም ነው፡፡ በዚህ የሮያል ኮሚሽን አባልነት የሚካተቱት ባለሙያዎች ከተለያዩ ዘርፎች የሚመለመሉ ሲሆን በሌሎች ሀገሮች (think thank) የሚባለው አይነት ቡድን መሆኑ ተብራርቷል፡፡ ሮያል ኮሚሽንን ልዩ የሚያደርገውና ደረጃውንም ከፍ የሚያደርገው በተቋሙ ውስጥ ተቃዋሚዎች ቀድሞም ስለማካተቱ ሃሳባቸውን ከመጀመሪያውኑ በደንብ ማስረግ እንደሚችሉ ነው፡፡ « የስዊድን ተቃዋሚዎች የመንግሥት ሥልጣን ባለመያዝ ብዙ ነገር አያጡም» ይላሉ ኔልሰን ፖልስብር፡፡

በሌላ ጠርዝ ያለው የኢትዮጵያ ፓርላማ በሚፀድቁ ህጎች ባለማወያየት ይኮነናል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የሚነሳው ትችት በዓመቱ መጀመሪያ ለአንዳንድ ጉዳዮች በእጅጉ የሚፈለጉ ህጎች ያለምንም ውይይት የሚፀድቁ ሲሆን አንዳንድ ጊዜም ለጉዳዮቹ የተመደቡ ቋሚ ኮሚቴዎች እንኳ እንደማያዩ ይነገራል፡፡ ሁለተኛው ወቅት የም/ቤቱ መዝጊያ አካባቢ ሲሆን «በዚህን ሰሞን የአዋጁን ርዕስ»

እንኳን በደንብ ሳይሰሙ እጅ የሚያወጡ አይጠፉም» ይላሉ፡፡ አንድ የቀድሞ የም/ቤቱ አባል የነበሩ ሰው፡፡ «ይህም ባይሆን ም/ቤቱ የግዑዞች ስብስብ ይመስላል» ይላሉ፡፡ የኢትዮጵያ የተወካዮች ም/ቤት ሲቪ ያዩ አንድ ተወካይ « በየትኛውም ሀገር በባሰ መልኩ ያልተማሩ ሰዎች ያሉበት ይመስለኛል» ብለዋል፡፡ በሌላ አቅጣጫ የችግሩ ዋነኛ ምንጭ ተደርጎ የሚወሰደው ገዢው ፓርቲ የም/ቤቱ አባላት የሆኑ ተወካዮቹን ነፃነት ባለመጠበቁ አባላቱ የሁለት እና ሦስት ቀናት በፊት ማጽደቅ እንዳለባቸው ትእዛዝ እንደሚሰጣቸው ነው፡፡ የገዢውንም ፓርቲ ሆነ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትንም የሚያስማማው ሌላው ችግር ሊፀድቁ የታሰቡት ህጎች ከ48 ሰዓታት በፊት ባለመስጠታቸው ተነበው የሰላ ሂስ የማይቀርብባቸው መሆኑ ነው፡፡ ብቸኛው የተቃዋሚ ፓርቲ የፖርላማ ተወካይ የሆኑት የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ የሊዝ አዋጁ የፀደቀበትን ሁኔታ ሲያብራሩ «መስከረም 2004 ዓ.ም የመጨረሻው ሰኞ ፓርላማው ተከፈተ፡፡ በዚያኑ እለት የሊዝ አዋጁ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ነገር ግን በእለቱ ብሔራዊ ቤተ-መንግሥት ግብዣ ስለነበር በእለቱ ማንም አዋጁን ዞር ብሎ አላየውም፡፡ ሆኖም በነጋታው ፓርላማ ተገኝተን ህጉ -መጽደቅ ነበረበት፡፡ እንግዲህ ያንን ሁሉ ውዝግብ ያስነሳው አዋጅ በዚህ መልኩ ነበር የፀደቀው » በማለት ነው፡፡

ፓርላማው ጠቅላይ ሚኒስትሩን ወይስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፓርላማውን?

በፓርላሜንታዊ መንግሥት አሰራር ሚኒስትሮች ፓርላማ በመገኘት በሥራ አስፈፃሚው (ካቢኔው) ስም ፕሮፖዛላቸውን ተከራክረው ማሳመን አለባቸው፡፡ ጠንካራ ም/ቤት ባለበት ሀገር ካቢኔው ለወጡ ህጎች የሜካኒካዊ አስፈፃሚነት ደረጃ ብቻ እንኳ ቢይዙ ከስኬት አይርቁም እስከ መባል ተደርሷል፡፡ አሌክስ ሙለር የተባሉ ሆላንዳዊ የፓርላሜንታዊ መንግሥት ተንታኝ ቢሮክራሲውም ሆነ ህግ አውጭው ፖሊሲ የማይወስኑበት ሀገር አስፈፃሚው / ካቢኔው ከፍተኛ የፖለቲካ ተክለ ሰውነት እንደሚገነባ ያብራራሉ፡፡ ይህ አካሄድ ፓርላማ የሚያሽከረክረው መንግሥት /legislative government/ የሚባለውን ፈጽሞ ያስቀራል፡፡ ይልቅ ካቢኔው ፓርላማውን የፈለገውን አይነት ህጎች እንዲያፀድቅለት በማድረግ የፓርላሜንታዊ መንግሥት ሴራ /Conspiracy of parliamentary government / የሚባለውን ኃሊዮት እንደሚተገብር ይነገራል፡፡ የፓርላሜንታዊ መንግሥት ሴራ የሚባለው በሁለት መልኩ የሚታይ ነው፡፡ የመጀመሪያው ፓርላማው በአስፈፃሚው ትእዛዝ ህጎችን በአብላጫ ድምጽ እንዲያፀድቅ ማድረግ ነው፡፡ አንድ ከህትመት ውጭ የሆነች ጋዜጣ የፕሬስ ህጉ-የፀደቀበትን ሁኔታ በሚመለከት «የፕሬስ ህጉ ፓርላማ ሲደርስ በጥድፊያ ፀደቀ፡፡ ሸንጎው አዳራሽ ከመድረሱ አስቀድሞ በብዙዎች ዘንድ ስለ ህጉ አፋኝነት ሲነሳ፣ በመንግሥት በኩል ደግሞ ስለሚያጎናጽፈን ሃሳብን የመግለጽ ነፃነት እና ይዞት ስለሚመጣው ኃላፊነት የውይይት አጀንዳ ሆኖ ነበር፡፡ ... ነገር ግን የሕገ-መንግሥቱን መሠረታዊ መርሆዎች ይፃረራል እየተባለም ሕጉ የፀደቀው በአብላጫ ድምጽ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሸንጎ በአብላጫ ድምጽ ከመጽደቅ የሚድን አንዳች ህግ ያለ አይመስልም» ብላለች፡፡ ጋዜጣዋ በአብዛኛው ኢትዮጵያ ውስጥ ይነሳል የተባለውን ስጋር (concern)ስትገልጽ « ይህ ህጎችን ሁሉ በአብጫ ድምጽ እያሳለፈ የሚፀድቀውን ሸንገጎ ማን «ኃይ» ይበለው ? የትኛው የመንግሥት አካል እየሠራኸ ያለኸው የሕግ መንግሥቱን መሠረታዊ መርሕ የሚፃረር ነው ብሎ ማን ይንገረው? ክፍተት አለ" በማለት ነበር፡፡ አንዳንዶች ይህንን ሁኔታ ከመንግሥት አወቃቀሩ በኃልዮት ደረጃ ብቻ መገደብ መሆኑን ያወሳሉ፡፡ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ሦስቱ የመንግሥት አካላት በኃሊዮት እንጂ በተግባር እንዳልተለያዩ ገልፀው "ሥራ አስፈፃሚው የመንግሥት አካልና ግሕ ተርጓሚው ‹የተጣመሩ› ሊባሉ የሚችሉ ናቸው፡፡» ይላሉ፡፡ እንደ ዶ/ሩ ማብራሪያ ‹ሥራ አስፈፃሚው የመንግሥት አካል ህገ መንግሥቱን እንዳይጥስ፣ ሥርዓት ጠብቆ እንዲሄድ ተቆጣጣሪው ሕግ ተርጓሚው ነው፡፡› ካሉ በኋላ ‹ይህ ህግ ተርጓሚ ክፍል› ሌሎችንም የመቆጣጠር ሥራ በህግ ደረጃ ተጥሎበታል፡፡ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ግን ገዢው ፓርቲ በሕዝብ ተወካዮችም፣ በሥራ አስፈፃማውም፣ በህግ ተርጓሚውም ክፍል ውስጥም የበዛ ጉልበት አለው» በማለት ይደመድማሉ፡፡ ባለፉት 20 ዓመታት ወደ ም/ቤቱ ተልኮ ሳይፀድቅ የቀረ አንድም ረቂቅ ህግ በሌለበት ሀገር ፓርላማው የሚቆጣጠረው መንግሥት (legislative government) ቀርቶ የሥራ አስፈፃሚ መንግሥት (Cabinet government) እንኳ የለም የሚሉ ተንታኞች ይበዛሉ፡፡

ሁለተኛው የፓርላሜንታዊ መንግሥት ሴራ በሰፊው የተነተኑት ሪቻርድ ፌኖ ም/ቤቱ የመረጠው ጠ/ሚኒስትር በተሰጠው ሥልጣን የተለያዩ ተቋማት ኃላፊነት የማያጫቸውን ባለሙያዎች መርሁ ከሚያተኩርበት የሙያ ብቃት ውጭ ለፖለቲካ ታማኝነት ቅድሚያ በመስጠት እንደሚተገብር ጽፈዋል፡፡ በድህነት ጉዳዮች ጥናት የተሰማሩ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ አንድ ባለሙያ ምሳሌ ያቀርባሉ፡፡ « ጠ/ሚ/ሩ የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኛን የማጨት ስልጣን አላቸው፡፡ ነገር ግን በመለስ ዜናዊ አመለካከት የኢህአዴግ ‹ቲፎዞ› ያልሆነ ሰው ቦታ የለውም» እኚህ ሰው በግልጽ እንኳ ባይሆን ኢህአዴግን በሆነ መልኩ የሚደግፉ ሰው ለፖርላማው ማቅረባቸውን ጠቅሰው «ታዲያ ምን ችግር አለባቸው፤ ፓርላማው እንደሆነ በኢህአዴግ ተወካዮች የተሞላ በመሆኑ አብላጫ ድምጽ የግላቸው ነው» በማለት ይገልፃሉ፡፡ ባለሙያው «ፍርድ ቤትን የመሰለ የተለየ ነፃነት የሚሻ ተቋም በዚህ መልኩ በቀላሉ ከያዝክ ምን የማታደርገው ነገር ይኖራል?» በማለት በጥያቄ ይደመድማሉ፡፡

እንደ አብዛኛዎቹ ተንታኞች ሀገሪቷ አሁን ከደረሰችበት ማማ አንፃር ፓርላማው በጠ/ሚ/ሩ የሚመረጥ /የሚሰራ እንጂ ጠ/ሚ/ሩ በፓርላማው የሚመረጡበትና የሚወድቁበት ዘመን ማለፉ ነው፡፡

## «የተቃዋሚዎች ያለህ!» በፓርላማ

ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊን «ካጀገኗቸው» ጉዳዮች አንዱ በም/ቤት በቀረቡ ቁጥር የሚሰጧቸው መልሶች ናቸው፡፡ ጠ/ሚ/ሩ ንቁ አይደሉም የሚባሉትን የም/ቤቱ አባላት በተቃዋሚ ተወካዮች ላይ በሚሰነዝሯቸው ዘለፋዎች ያስፈግጓቸው ነበር፡፡ ነገር ግን የገዢው ፓርቲም ሆኑ የተቃዋሚው ጎራ ተወካዮች ጠ/ሚ/ሩን የሚጠይቋቸውን ጥያቄዎች ከም/ቤቱ ስብሰባ ቀን እጅግ አስቀድመው በጽሁፍ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን በለቱም ያንኑ ቃል በቃል ከማንበብ በቀር ማሻሻያና ማብራሪያ ማቅረብ እንደማይችሉ ታይቷል፡፡ ጠ/ሚ/ሩ ለረዥም ሰዓታት የተዘጋጁባቸውን እነዚህን ጥያቄዎች ከ« 1001»በሚመሳሰል መልኩ ይተነትናል፡፡ ሆኖም ጉዳዩ የበለጠ አሳሳቢ የሚሆነው ጠ/ሚ/ሩ በባህሪያቸው ነገሮችን በሴራ/በግልባጭ የመተንተን ልምድ ስላላቸው መልስ የመጠየቅ አሊያም የጥያቄውን አቅጣጫ የመምራት (Rebottle) እድል የለም፡፡ በዚህ አኳኋን ጠ/ሚ/ሩን በጥያቄዎች እና በድንገት መጣሽ ጥያቄዎች ማፋጠን አይችልም ማለት ነው፡፡ ከ2002 ዓ.ም ወደዚህ ባለው ሁኔታ ደግሞ ም/ቤቱ በተቃዋሚዎች ድርቅ በመመታቱና ጠ/ሚ/ሩ በም/ቤቱ ላይ አላቸው በሚባለው «እልቅና» መሠረት «ራሳቸውን ጠይቀው ራሳቸው ይመልሳሉ» እስከመባል ተደርሷል፡፡ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ « ስትራቴጂና የአምስት ዓመት እቅድ» መጽሐፍ « በዘመነ ኢህአዴግ . . . ህጋዊ እውቅና የተሰጣቸው ከዘጠና በላይ ፓርቲዎች አሉ ቢባልም እንዲሁም እስካሁን ድረስ አራት ምርጫዎች መካሄደቸው ቢታወቅም. . . ተቃዋሚዎች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በውሳኔ ሰጭነት ለመሥራትም ሆነ ተጽእኖ ለመፍጠር የሚያስችል ትርጉም ያለው ቦታ የላቸውም» በማለት አስፍሯል፡፡ በ19972 ዓ.ም በነበረው ብሔራዊ ምርጫ ከ547ቱ ወንበሮች 12

ወደ 11 ዞሯል

# በእርግጥስ የኢህአዴግ አገዛዝ ልማታዊ መንግስት ነው ወይ ?

ኢህአዴግ ስልጣን ከጨበጠ ከሁለት ዐመት በኋላ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ጋር በመስማማት ድርጅቱ ያቀረበለትን የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች አንድ በአንድ ተግባራዊ ያደርጋል። የፖሊሲውን ምንነትና በተግባር ላይ ሲመነዘር ምን ዐይነት ውጤት እንደሚያመጣና እንዳመጣ ከዚህ ቀደም ባወጣኋቸው ጽሁፎቼ ላይ በሰፊው አብራርቼአለሁ። ጽሁፎቹን እንደገና ማገላበጡ የኢህአዴግ አገዛዝ የልማት መንግስት መሆኑና አለመሆኑን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል ብዬ አምናለሁ

ያም ሆነ ይህ እ.አ በ1993 ዓ.ም ተግባራዊ የሆነው የተቅዋም ፖሊሲ(Structural Adjustment Program) ቲዎሪያዊ መሰረቱ ኒዎ-ሊበራሊዝም ነው። ይህም ማለት ቲዎሪው በይዘት ላይ ያተኮረ ሳይሆን ክስተታዊ ነው ማለት ነው። በሌላ አነጋገር በቲዎሪው መሰረት የአንድን አገር ወይም ህብረተሰብ ኢኮኖሚም ሆነ አጠቀላይ ህብረተሰብአዊ ችግር የሚረዳው ወደ ውስጥ በመግባትና በሰፊውና በጥልቀት በማጥናት ችግሩን በማውቅ ሳይሆን የተወሰኑ የማክሮ ኢኮኖሚ መሳሪያዎችን በመውሰድና ከዚህ በመነሳት ችግሩ እንደሚፈታ ለማሳመን በመሞከር ነው። ሀለተኛ፣ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የማክሮ ኢኮኖሚ ሞዴል የአንድን ህብረተሰብ ችግር ከኢኮኖሚ አንፃር ብቻ ነው የሚመለከተው። ከመጀመሪያውኑ ፖለቲካዊ፣ ኢንስቱቲሽናዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ነገሮችን በማጣመር የችግሩን ጥልቀት ለመረዳት ጥረት አያደርግም። ለምሳሌ የካፒታሊስትን ስርዓት የዕድገት ታሪክ ስንመረመር ከባህል አብዮት በፊት ከመጀመሪያውኑ በተወሰኑ መሳሪያዎች ብቻ የነበሩባቸውን የኢኮኖሚ ችግሮች ለመፍታት አልቃጡም። በሶስተኛ ደረጃ፣ ከዚህ በፊት ደጋግሜ ለማብራራት እንደሞከርኩት የማክሮ ኢኮኖሚ ሞዴሉ አጠቃላይ የሆነ ህብረተሰብአዊ ሀብትን ለመገንባት የሚያስችል አይደለም። ሞዴሉ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ የሀብት ሽግሽግ በማድረግ የተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል። በዚህ መልክ ፈጣሪና ኢንቬስት ለማድረግ የሚችል አዲስ ኃይል ብቅ እንዳይልና እንዳያድግ ያደርጋል። በአራተኛ ደረጃ፣ በማኑፋክቱር ላይ ከተመሰረተ የምርት እንቅስቃሴ ይልቅ ንግድና የተቀረው የአገልግሎት መስክ እንዲስፋፋ ያደርጋል። በተለይም ከአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገትና ፍላጎት እንዲሁም የሀብት አቅርቦት ጋር ሊሄዱ የማይችሉ ትላልቅ ሆቴል ቤቶች በመስራት ውሃንና ኃይልን እንዲሁም ምግብን በከፍተኛ ደረጃ እንዲጋራ የሚያደርግ ነው። በዚህ መልክ ያልተስተካከለ ዕድገት እንዲኖር ማገዙ ብቻ ሳይሆን የአብዛኛው ህዝብ አትኩሮ በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲሆን ያስገድዳል። በአምስተኛ ደረጃ፣ ሰፋ ያለ የስራ ክፍፍል እንዳይዳብር ዕንቅፋት ይሆናል። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አገዛዙ በሚከተለው የተቀናቃኝ ፖሊሲ በግል ሀብታቸው የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን ቀስ ቀስ እያለ ያጠፋቸዋል። ምክንያቱም በኢኮኖሚ እያደገና እየዳበረ የሚመጣ ኃይልም ለፖለቲካ አገዛዝ አያመችም በማለት አይ በሙስና ውስጥ እንዲዘፍቅ ያደርገዋል፤ አሊያም ደግሞ ሀበቱን በመንጠቅ ያዳክመዋል። ስለሆነም እንደዚህ ዐይነቱ የኢኮኖሚ ሞዴል ተግባራዊ በሆነባቸው አገሮች በሙሉ ሰፊ ውንብድና መስፋፋቱ ብቻ ሳይሆን የመንግስት መኪናዎች የበለጠ ጨቋኝ እየሆኑ በመምጣት ህዝቦች አፎይ ብለው እንዳይኖሩ ተደንግጎባቸውል። ተፈጥሮአዊ መብታቸው በመነጠቅ በፍርሃት ዓለም ተውጠው እንዲኖሩ የተገደዱ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች በየአገሩ እንዳሉ የታወቀ ነው። በስድስተኛ ደረጃ፣ ለአንድ አገር ዕድገት አስፈላጊው የሆነው የሳይንስና የቴክኖሎጂ ምርምርና ምጥቀት እንዳይኖር ከመጀመሪያውኑ ያግዳል። ሳይንስና ቴኮኖሎጂ ካልዳበሩ ደግሞ የተለያዩ የምርት ማምረቻ መሳሪያዎችንና፣ እንዲሁም ለአንድ ህብረተሰብ አስፈላጊ የሆኑ የፍጆታ ዕቃዎችንንም ሆነ ከአደጋ ሊከላከሉ የሚችሉትን መሳሪያዎች ሊያመርት አይችልም ማለት ነው። በአንጻሩ ግን ዕውነተኛ በመንግስት የተደገፈ የልማት ፖሊሲ ያካሄዱ አገሮች በሙሉ ቅድሚያ የሰጡትና አሁንም የሚሰጡት በቴክኖሎጂ ላይ

የተደገፈ ኢኮኖሚ መገንባትን ነው። ዋና ዓላማቸውም ሰፋ ያለና የጠለቀ ሀብት በመፍጠር ጠንካራ አገር መመስረት ነው። ለዚህም ነው ዛሬ ራሳቸውን መቻልና መከበር የበቁት።

ከዚህ ስንነሳ ኢህአዴግ ስልጣን ከጨበጠ ጀምሮ የሚያካሄደው የኢኮኖሚ ፖሊሲ በምንም መልኩ ሰፋ ያለ ሀብት የሚፈጥር አይደለም። የቢራ ፋብሪካ ማስፋፋት፣ በሰሊጥ ተከላ ላይ በማትኮር ጥሬ ሀብቱ አገር ውስጥ እስከመጨረሻ ድረስ እንዳይመረት አድርጓል። በዚህም መልክ መሰረታዊ የሆነን የኢኮኖሚ ህግን ጥሷል፤ እየጣሰም ነው። አንድ አገር የጥሬ ሀብቷን እንዳለ ከነነፍሱ ወደ ውጭ የምትልክ ከሆነ በኢኮኖሚ ልታድግ አትችልም። በአስራ አምስተኛውና በአስራስድሰተኛው ክፍለ-ዘመን ይህንን የተገነዘቡት እንግሊዝና ፈረንሳይ በጊዜው የነበረባቸውን የኢኮኖሚ ድክመት ለመቅረፍ የወሰዱት እርምጃ የግዴታ የጥሬ-ሀብት ወደ ውጭ እንዳይላክ በማድረግ ነበር። በአስራአራተኛውና በአስራአምስተኛው ክፍለ-ዘመን ጣሊያን በኢኮኖሚ የበለጸገች ስለነበረች እንደ እንግሊዝ የመሳሰሉትን የጥሬ-ሀብት አምራች አድርጋ ነበር። በጊዜው ስልጣን ላይ የነበረው በሄነሪ ሰባተኛው የሚመራው አገዛዝ ይህንን በመረዳት ወደ ማኑፋክቱር አብዮት በማሸጋገር የበግ ሱፍና ሌሎች የጥሬ-ሀብቶች ወደ ውጭ እንዳይወጡ ነው ያገደው። እንደዚሁም ፈረንሳይ በእነ ኮልበርት ዘመን ከእንግሊዝ የሚመጣባትን የኢኮኖሚ ጭነትና መዛባት ለመቋቋም የቻለችውና ወደ ኢንዱስትሪ አብዮት ለመሸጋገር የበቃችው የጥሬ-ሀብቷን በመቆጣጠርና እዚያው አገር ውስጥ ደረጃ በደረጃ እንዲመረት በማድረግ ነው። ከዚህ ስንነሳ የኢህአዴግ ፖሊሲ አንድ በአንድ የዴቬሎፕሜንታል ስቴትን የኢኮኖሚ ፖሊሲን የሚጻረርና አገራችንን ለረዥም ዐመታት ደካማና ደሀ እንዲሁም በውጭ ኃይሎች ተጠቂ የሚያደርጋት ነው።

ሰለሆነም ከአምስት ዓመት ጀምሮ ህዝባችንን ከመሬት እያፈናቀለ ኢንቬስተሮች ለሚባሉ የሚሰጠው ሰፋፊ የጋሻ መሬት በመሰረቱ የዴቬሎፕሜንታል ስቴትን የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚቃወም ነው። 1ኛ) እንደዚህ ዐይነቱ የመሬት ማፈናቀል እርምጃ የተወሳሰበና እርስ በርሱ የተያያዘ በቤተሰብ ላይም ሆነ በአነስተኛና በማዕከለኛ ገበሬዎች የሚታረስ የእርሻ ክንውን እንዳይካሄድ ያግዳል። 2ኛ) ለኢንቬስተሮች የተሰጠው የእርሻ መሬት ለአገር ውስጥ ፋብሪካዎች የጥሬ-ሀብት እንዳያመርት ታግዷል። 3ኛ) አንድ ወጥ የሆነ የአመራረት ስልትና በተወሰኑ ምርቶች ላይ ያተኮረ የእርሻ ክንዋኔ እንዲካሄድ ይገፋፋል። ይህ ደግሞ የተፈጥሮን ህግ የሚጻረርና የአካባቢን መዛባትን የሚያስከትል ነው። ከዚህም ባሻገር በላቦራቶሪው ውስጥ የተዳቀሉ ዘሮች ከመሬት ውስጥ ውሃን የመምጠጥ ኃይላቸው ከፍ ያለ ስለሆነ ከረዥም ጊዜ አንጻር ድርቀትን ያስከትላሉ። 4ኛ) በገጠር

ወደ 10 ዞሯል

# 180 የሃዘንና ጭንቅ ቀን በወፍ በረር ሲቃኝ በተለይ "6" ቀናት

በብሩክ ከበደ

ከላይ በተገለፀው ርዕስ ሥር አዲስ አበባ ከሚያዚያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 1998 ዓ.ም ድረስ ባሉት ተከታታይ 180 ቀናት (6 ወራት) ያስተናገደቻቸውን ዋና ዋና የሚባሉ ምልኪዎችን (የመጥፎ ነገር ምልክቶች) ነቅሰን እንቃኛለን፡፡

ለመቃኘትም ያስፈለገበት ምክንያት የገዥዎችና ጀሌዎቻቸው ድርጊት ያስከተለውን ምላሽ አመላካች የሆነችው ቀዳሚዋ ሚያዚያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም በዚህ ወር 7ኛ አመቷን የምትደፍን መሆኗን ለማስታወስ ብቻ ሣይሆን ፈረንጆቹ "ኤፕሪል ዘ-ፉል" በሚሉት የማሞኘት ቀን ሣይሆን እውነት በሆነችው የኛ ዕለት ቀኗ ሲነሣ አሁንም ድረስ ከፍርሀት መውጣት የሚያቃታቸው አልኮል መጠጥን እንደጊዜያዊ ማዘናጊያ በመምረጥ በየመለኪያዎቻቸው ውስጥ የሚደበቁ መንበረ ስልጣናት እንዳሉ በርካታ ውስጥ አዋቂ ወዳጆቼ በየ ጊዜው ስለሚደርሰኝ አሁንም ጀግናዋን ወር አይ ዞሽ ለማለትና ለመዘከር ነው፡፡

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ ሟች ሰባት አመት ሲሞላው ድል ያለ ድግስ ይደገሣል፡፡ ማቅ ልብሱም ይወልቃል፡፡ ያልቆረቡ ጥንዶች ካልሆኑ ከሌላ ጋር እንዲጣመሩ ወቀሳና ምክር ይጐርፋል፣ይህ ታዲያ ዛሬ ሁሉ ነገር በሰልት በስልቱ በሚጠናቀቅበትና ለሰው ልጅ የነበረው ከፍተኛ ግምትና ፍቅር እንዲህ እንጦሮጦስ ባልወረደበት ደጉ ዘመን ነበር፡፡

ዛሬ የምንዘክረው ሚያዚያ 30 ግን እንደ እምነቱ ተከታዮች ሞት ያልተቀበረ፣ የመዘከሪያ የጊዜ ሰሌዳ ያልተቀመጠለት ብቻ ሣይሆን አንዴ በብሶት ውስጥ ተወለደ እንጂ አሁንም ድንገት መቼና እንዴት ተመልሶ እንደሚመጣ የማይታወቅ፣ እንደ ህይዋን ተረግዞ የሚወለድ፣ከዳዴ ተነስቶ እስከ አዛውንትነት የሚደርስ (የአረቡን ዓለም ልብ ይሏል) ለመሞቱም ማንም በእርግጠኝነት የማይመሰክርለት ሆነ የማይነገርለት የህዝብ መንፈስ ወይም ቀለብ የሆነ ነው፡፡

የኸም ስለሆነ ነው "ቀነ-ጐዶሎ" በየት በኩል እንደሚመጣ የማያውቁና በጣም የሚፈሩት ክስተት ብቻ በመሆኑም መስማትም ሆነ መናገር አይፈልጉም፡፡ በአጋጣሚ አሊያም በግዴታ ከተነሣ እረፍት ስለሚነሣሳቸው ጠርሙስ ወይም መለኪያ ውስጥ ለመሸጐጥ ሲፈጥኑ አያድርስ ነው፡፡ ያኔ እነሱን አያርገኝ፡፡ አጠገባቸው አለመገኘት ይበጃል፡፡ ባለመኪናም ከሆኑ እግረኛን ገጭተው ወይም የትራፊክ መብራት ጥሰው ለማለፍ ደንታ የላቸውም፡፡ ሃሳባቸው ሁሉ ከሚያባርራቸው ህሊና ለማምለጥ ነው፡፡ ይኸንንም ልቡስ (ሥውር) መብረቅ ነው በወፍ በረር የምንቃኘው፡፡ ጭንቅና መከራው ረጅም የነበረው 6 ወር ያስተናገደው ክስተት በተለያየ መንገድ እየተበለተ የጊዜ ቀመር ቢሰላለት ቢያንስ በ60 ዓመት የተከሰተ ድርጊት እንጂ በ180 ቀናት ያለአቅሙ ተጠቅጥቆ የተሞላ እውነት አይመስልም፡፡

በ1983 ዓ.ም በብቸኛዉ አማራጭ ጦር መሣሪያ ኃይል ሥልጣኑን የጨበጠው ኢህአዴግ በየጊዜው የሚያወጣቸው ፖሊሲዎች፣አዋጆችና መመሪያዎች የሚገዛውን ሕዝብ ይሁንታና ፈቃድ እንዲሁም ስምምነት ያልጨበጡ በመሆናቸው ውስጥ ውስጡን አንዳንዴም በየፋ ይነሱ የነበሩ የተለያዩ ሕብረተሰብ ክፍሎች ብሶቶችና ተቃውሞዎች እስከ ግንቦት 1997 ዓ.ም ድረስ ቀጥለው ስልጡኑ ዓለም እየተገዛበት (እየተዳደረበት) በሚገኘው "ፍላጐተ ካርድ ብልጫ" መርህ መሰረት ውስጣዊ ብሶቱንና ቁጭቱን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በጣቱ ፈርሞ "ኡፎይ ግልግል" ብሎ ነበር፡፡ ምንም እንኳን ሃሣብና ድርጊቱ «ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ» ቢሆኑበትም፡፡

መራጭ ምኞቱ ሳያሰምር ቀረና ሥልጣኑን ለመልቀቅ ሆነ ለማጋራት ፍጹም ፈቃደኛ ያልሆነው ኢህአዴግ ገና የምርጫ ካርድ ቆጠራው ሳይጠናቀቅ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ (Marshale low) በማወጅ ተቃውሞና ስብሰባ ማድረግን አገደ፡፡ ድምፅ ቆጠራውም እንዲቋረጠ ትዕዛዝ በመስጠት የህዝቡን ሙሉ ስሜትና ፍላጐት ደፈጠጠ፡፡ በስልጣናቸው የማይደራደሩት ከፍተኛ የኢህአደግ ሹሞችም ከሔሊኮፕተር እስከ ላንድ ክሩዘር እያንቀሳቀሱ ድምፅ መስጫ ጣቢያ በመድረስ ምርጫ አስፈጽማለሁ የሚለው አካል በስራዉ ቢከበርም ባይከበርም ያስቀመጠውን ደንብና መመሪያ በመጣስ ታዛቢዎችን አባረዋል፣ ኮረጆ ዘርግፈዋል፣ የውጪ ታዛቢዎችን ሪፖርት ከማጣጣል አልፈው ዘልፈዋል፡፡ የሀገሪቷ ጠ/ሚኒስትርም ይድረስ ያሉትን "ውጉዝ ከመአርዮስ" በእንግሊዘኛ በሚታተም መንግሥታዊ ጋዜጣ ላይ ጽፈው አስነብበዋል፡፡ ነገሩ ሁሉ ከድምጽ መስጫ ወረፋ እስከ ግብአተ መሬት ትንቅንቅ ድረስ የሚዘልቅ ጣር መሰለ፡፡

ቁንጮው ሰው በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ቀርበው "ሁለት ጣት ይቆረጣል" ባሉት አምባገነናዊነትና የህዝብን ፍላጐት በኃይል ለመደፍጠጥ በተደረገው ወታደራዊ እርምጃ በአዲስ አበባ ብቻ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም በአንድ ጀንበር በአልሞ ተኳሾች ጥይት 43 ዜጐች ወድቀዋል፡፡ መተሬ (ሰናይፐር) ተኳሾች ያለቆቻቸዉ ወንበር እንዳይነቃነቅ በየሀገሮቻቸው ማለትም ትናንት በሊቢያ ዛሬ በሶሪያና የመን ነዋሪ የሆኑ ንጹሃን ዜጐች እንዴት እንዳረገፉና እያረገፉ መሆናቸውን ዕድሜ ለኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በደንብ ተመልክተናል፡፡

በዚሁ በአዲስ አበባችንም አግዝ እንጂ አጣራ ባልተባለ ኃይል ከ10 ሺህ በላይ የሚሆኑ ወጣቶችና አዛውንቶችን ጨምሮ ታማሚ ከጤነኛ፣ሰራተኛ ከተማሪ ሣይለይ ጣር ባስከተለዉ ፍርሃት በመዋጥ በውድቅት ሌሊት የመኖሪያ ቤቱ በር እየተሰበረና በየተገኘበት አየታፈሰ ወደ ዝዋይና ደዴሣ በመለዮ ለባሽ ተሽከርካሪ እየተጫነ ተግዟል፡፡

ይኸን የሕዝብ "ድምፄ ይከበር" ጥያቄ ለጊዜው በጦር ኃይሉ የደፈጠጠዉ ኢህአዴግ በሚቆጣጠራቸው መገናኛ ብዙሃን "የአትክልትና ፍራፍሬ አብዮት ጠንሳሾች፣የደርግ ኢሰፓ ቅሪቶች፣ነፍጠኞችና ጠባቦች የሕዝቡን ሥልጣን በኃይል ለመያዝና ሕገ-መንግሥቱን ለመናድ የሚያደርጉት መፍጨርጨር ነው" እያለ በሕዝብ ድምጽ የተሸነፉትን ሁሉ በሥሩ እያሰባሰበ ኮንኖ ቢያስኮንንም ሕዝቡ ይባልጥኑ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጐን እንዲሰለፍ አደረገው እንጂ አላፈገፈገም፡፡ ከዚህም ቁርጠኝነቱ የተነሣ የመንግሥት ሚዲያዎችን "ውጉዝ ከመአርዮስ" ከማለት አልፎ አልሰማም አላይም እስከማለት ደረሰ፡፡ ህሊናቸው አልቀበልም ያላቸው ጋዜጠኞችም አገር ጥለው እስከ መሰደድ ያለውን አማራጭ ያዙ፡፡ ሕዝቡም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ "እኔ ፈቅጄ እስከ መረጥኩ ድረስ ሰይጣንም ይግዛኝ፡፡ ከኔ በላይ በፍጹም አታውቁልኝም" ሲል ድምጹን አሰማ፡፡

የከተማዋ ነዋሪ ከከፍተኛው ሀዘንና ሰቆቃ ገና ሳያገግምም በየአዳራሹ ድምጽ ከሰጣቸው መሪዎቹ ጋር እየተገናኘ "ድምፄን አደራ ድምፄ እንከን ቢገጥመው ከኢህአዴግ በላይ እናንተን ነው የምጠይቀው!" ሲልም ክፉኛ አስጠነቀቀ፡፡

በዚህም የሕዝቡ ዳግመኛ አንድ ሆኖ ኢህአዴጐች በቃችሁኝ፣ሰለቻችሁኝ ዓይናችሁን ላፈር! ሲል የገለፀው አቋም ገዢ ፓርቲውን ክፉኛ አስደነገጠው፡፡ ገዥዎች ባለቀቃቸው ድንጋጤ ተውጠውም ቅንጅት የሚባለውን ሕጋዊ ፓርቲ በገንዘብ፣በሃሣብ፣በቁሣቁስ ብቻ ሳይሆን በፀሎትም ይደግፋሉ ብለው የሚገምቷቸውን፤የሚጠራጠሯቸውን ሁሉ አስረዋል፣ አሰቃይዋል፣ ሥራ እንዳይሠሩ፤እንዳይማሩ አውከዋል፡፡ ከፍተኛ ሰብአዊ መብት ጥሰት ፈጽመዋል፡፡ ፓርቲው በሞትና ስቃይ ጋራ የተቀናጀ እስኪ መስል ድረስ ለሕዝቦች መብት ስቃዩን አንዲቀበል አድርገውታል፡፡ ተሳክቶላቸዋልም ሰነጣጥቀው አክስመውታል፡፡ ከዛ በፊትም ውስጥ ውስጡን የተፎካካሪ ፓርቲዎችን አንድነት ለመነጣጠል ብሎም ለመበታተን የተለያዩ ስትራቴጂኮች ሥራ ላይ ውለዋል፡

ወደ 15 ዞሯል

# ርዕሰ አንቀፅ

ፍኖተ -ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሠረተ፡፡ ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሥር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር የፓርቲው ጋዜጣ ነው፡፡

**ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል ይፈልጋል፡፡ የማንኛዉም ሰዉ ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲዉን ለማቅረብ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነዉ**

ዋና አዘጋጅ፡-
ሰለሞን ስዩም
አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ወረዳ 1
የቤ.ቁ 028

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ብስራት ወ/ሚካኤል

አርታኢ፡-
አንዳርጌ መሥፍን

አምደኞች፡- ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ወንድሙ ኢብሳ
አንዱዓለም አራጌ
ግርማ ሞገስ
ደረጀ መላኩ
ቀለሙ ሁነኛው
በለጠ ጎሹ

ኮምፒውተር ጽሑፍ፡-
የሺ ሃብቴ
ብርቱካን መንገሻ

ህትመት ክትትል፡-
አያክሉህም ጀንበሩ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ

አሣታሚው፡-
አንድነት ለዴሞክሲና ለፍትህ ፓርቲ(አንድነት)

አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤ.ቁ አዲስ


አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07 የቤ.ቁ 984

የዝግጅት ክፍሉ
ስልክ +251 118-44 08 40
+251 922 11 17 62
+251 926 81 46 81
+251 913 05 69 42
+251 923 11 93 74

ፖ.ሳ.ቁ፡ 4222

ኢሜይል፡- fnotenetsanet@yahoo.com
udjparty@gmail.com
andinet@andinet.org

ፋክስ ቁጥር፡- +251-111226288



## ለፓርቲ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ እንኳን ለሀገር ጥቅም እጅ የሚያወጡ የፓርላማ አባላት የሚኖሩን መቼ ነው?

በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 54 ቁጥር 1 ላይ በየአምስት አመቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በሁሉን አቀፍ፣ ነፃ ቀጥተኛና ትክክለኛ በሆነ ድምፅ በሚስጥር ስርዓት ይመረጣሉ ተብሎ ከተደነገገ በኋላ ለይስሙላም ቢሆን አራት ሀገራዊ ምርጫዎች ተካሂደዋል፡፡ ምርጫ የሚካሄደው ለይስሙላና ሌሎች ሀገራት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያለ ለማስመሰል ነው የምንለው እንዲሁ የገዡውን ፓርቲ አገዛዝ ከመጥላት የመነጨ ብቻ አይደለም፡፡ ያለፉት አራት ምርጫዎች ፍንትው አድርገው ያሳዩን ይሄንኑ ‹‹ይስሙላነት›› ስለሆነ ብቻ ነው፡፡

ይሄው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታን እንደ ላንቲካ የሚታይ እንጂ የማይበላ ያደረገው ገዡው ኢህአዴግ በፌደራል ስርዓት አወቃቀሩ ውስጥ ካሉት ሦስት አካላት(ህግ አውጭ፣ ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈፃሚ) የተወካዮች ምክር ቤት ወይም ህግ አውጭው ከፍተኛውን ስልጣን ይይዛል፡፡ እንደ ሥልጣኑ ግዝፈትና ስፋት በአግባቡ ተጠቅሞበታል ወይ? ከጀርባ ሆኖ የሚገፋውን ሃይል ተቋቁሞ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረቱን አድርጓል ወይ? የኢትዮጵያ ህዝብ ችግር ላይ ይከራከራል ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች እንዳሉ ሆነው ማለታችን ነው፡፡

ከመቶ ሺ ሰው በላይ ወክለው አይን፣ ጆሮና አፍ በመሆን ለአምስት ዓመት በእንደራሴነት ለማገልገል ወደ ፓርላማ የሚመጡት የህዝብ ወኪሎች የህግ አውጭነቱን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ የኃላፊነት ሸክም ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ለሚረዳ ሰው ከመቶ ሺ ሰው በላይ ወኪል እንደመሆን የሚከብድና የሚያጎብጥ ስራ ያለ አይመስለንም፡፡ ይሄን ሀላፊነት ምን ያህል እንደራሴዎች ተረድተውታል? የሚለውን ትዝብት ለራሳችሁ ለተመራጮችና ለኢትዮጵያ ህዝብ እንተወዋለን፡፡

በእኛው ሀገር ፓርላማ ታሪካዊ ዳራውን ትተን በነፃ አውጪነት ሰበብ ወደ ሚኒሊክ ቤተ መንግስት የዘለቀውንና መንግስት የሆነውን ኢህአዴግን ብንመለከት ያየናቸው የፓርላማ አባላት አብዛኛው ማለት በሚያስደፍር መልኩ የህዝብ ኃላፊነታቸውን ዘንግተው የፓርቲያቸውን ጥቅም በማስቀደም አይረቤ በሆኑ ህጎች ላይ ሁሉ እንደ ጭራሮ እጃቸውን ሲዘረጉ ተመልክተናል፡፡ ከላይ የጠቀስነው የሃላፊነቱ ክብደትና የአባላቱ የመከራከር አቅም በማይገናኙበት ጠርዝ ላይ እንደቆሙ ለማስተዋል ይችላል፡፡

ንቁ፣ ተከራካሪ፣ የሚሞግቱና ስለሃገራቸው የሚጨነቁ እንዲሁም ለፓርቲ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ እንኳን ለሃገር ጥቅም ሲሉ ትንሽ የተቃውሞ ድምፅ የሚያሰሙ የፓርላማ አባላት የሚኖሩን መቼ ነው? የሚለው ጥያቄ አሁንም መልስ አላገኘም፡፡ ይሄ ጥያቄ በኢትዮጵያ ህዝብ ትብብር መመለስ አለበት ብለን እናምናለን፡፡ ትልቁን ቤት የሚመጥኑ ሰዎች መግባት አለባቸው እንላለን፡፡

ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በኋላ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ፍንጭ ያሳየ ቢመስልም ገና በለጋ እድሜው ‹‹በካራቴ›› ተብሎ ድራሹ እንዲጠፋ ተደርጓል፡፡ እንዲህ ሆኖም አብዛኞቹ የፖለቲካ ሰዎችና ተንታኞች እንደሚስማሙበት ትንሽ ነፍስ የዘራ ፓርላማ የታየው ከ1997 ዓ.ም በኋላ ነው፡፡ ለእስር ከተዳረጉት የቅንጅት ተመራጮች ውስጥ ከእስር የተረፉት ጠቅላይ ሚኒስትሩን በመሞገትና በመከራከር ህይወት ያለው ፓርላማ ተስፋን እንድናይ ጋብዘውን ነበር፡፡ ይሄው ተስፋ ግን ብዙም ሳይቆይ ነፍስ ላይ እንደተለኮሰች ሻማ ድርግም አለ፡፡ በሌሎች ሀገራት ያለውን የሰለጠነ የፓርላማ ክርክር እያየን መቁለጭለጭ ስራችን ሆነ፡፡ ህግ ይረቀቃል፣ ይፀድቃል፤ ይረቀቃል፣ ይፀድቃል፣ የፓርላማችን ተደጋጋሚና አሰልቺ ስራ ይሄው ነው፡፡

ከ1997 ዓ.ም የተሰየመው ፓርላማም ቢሆን አብላጫ ድምፅ በርካታ ህጎችን አፅድቋል፡፡ በዚያኛው የፓርላማ ዘመን ከወጡ ህጎች መካከል ደግሞ የፕሬስ ህግ፣ በመያዶች ላይ የወጣው ህግና የተለያዩ ስሞች የተሰጡትና የተተቸው የፀረ ሽብርተኝነት ህግ ይገኙበታል፡፡ በተለይ የፀረ ሽብርተኝነት ህጉ “ሕጋዊ አፈና” “በርካታ በተምታቱ ጉዳዮች የታጨቀ” እና “ኢህአዴግ በተለይ ሀቀኛ ተቃዋሚዎችንና ጋዜጠኞችን ለማጥቃት የሚጠቀምበት” ሰላማዊ ሰልፍ ሊያሳስር የሚችልበት አይነት ትችቶችን ያስተናገደው የፀረ ሽብርተኝነት ህግ ከረቂቅነት ጀምሮ እስከ መፅደቅ የደረሰው በዚያው የፓርላማ ዘመን ነው፡፡

በእርግጥም እነዚህ ለአብነት ያነሳናቸው አከራካሪ ህጎች ከጥቂት ሀቀኛ ተቃዋሚዎች በስተቀር (በወቅቱ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ፣ አቶ ተመስገን ዘውዴ፣ ፕ/ሮ በየነ ጴጥሮስ፣ ዶ/ር መረራ ጉዲና) የመሳሰሉት የመረረ ስጋታቸውን ማቅረባቸው የሚታወስ ነበር፡፡ ቀሪዎቹ ግን እጅ በማውጣት ብቻ “ህግ” እንዲሆን ተባበሩ፡፡ ታዲያ አንዳንዴ እንኳን ለፓርቲ ብቻ ሳይሆን የሀገር ጥቅምን ሊጎዳ የሚችል ህግ ላይ መከራከር ማንን ገደለ? አቋም የመውሰድ በጐ ልምድስ አለን ወይ? ይሄ ጥያቄ ጋዜጣችንን ያስጨንቃል፡፡ በጐውን የክርክር ልምድም ማምጣት አለብን ብሎ ያምናል፡፡

አሳዛኙ ነገር በገዡው ፓርቲ እየተቆነጠሩ በሚሰጡ አንድና ሁለት ደቂቃዎች ስጋተቸውን የሚገልፁ የተቃዋሚ እንደራሴዎችን ማየት አልፈለገም፡፡ በ2002 ዓ.ም ጠርናፊና ተጠርናፊ አዘጋጅቶ ያለ የሌለ ኃይሉን በማሰባሰብ ጠቅልሎ ለመውሰድ ችሏል፡፡ ይሄም ለፓርላማው “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” አይነት ነው፡፡

በ2002 ዓ.ም ምርጫም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ስጋት የሆኑ ተከራካሪዎች ተወግደዋል፡፡ ህግ አውጭዎች የፓርቲያቸውን ፈቃድ ለመፈፀም ዝግጁ ናቸው፡፡ ክርክር በሌለበት መለወጥ እንዴት ይኖራል? አሁን በህትመት ላይ የሌለችው አዲስ ነገር በአንድ ወቅት እንደዚህ ዘገባ ነበር፡፡

“ሙግት የፓርላማው ባህል አይደለም ጠቅላይ ሚንስትሮቻቸውን ከፊታቸው አቁመው በጥያቄ የሚያጣድፉ አገሮች የፖለቲካ ባህል ግን እንደቀናን አለን” የሚል ነበር፡፡ ጋዜጣችንም ይሄ ባህል እንዲመጣ በጥንካሬ ትሰራለች፣ ንቁ የም/ቤት አባላት እንዲፈጠሩ ማድረግም ተገቢ እንደሆነ ታምናለች፡፡

ለገዡው ፓርቲ እስካሁን የተሳካለት ተከራካሪ ፓርላማ አለመፍጠሩን የሚያስማማን ከሆነ ወደ መፍትሔው መሄድ ይኖርብናል፡፡ ኢህአዴግ የሚፈልጋቸውን አፋኝ ህጎች ለማርቀቅ ይመቸው ዘንድ በመዳፉ ጨብጦ የሚያስረው ፓርላማ እንደሚፈልግ እሙን ነው፡፡ ፓርላማችን የሞቀ ሙግት የራቀውና ቀዝቃዛ የሆነበት አንዱ ምክንያት ይሄው ነው፡፡

ይሄ ባህል መቀየር አለበት፡፡ ህዝቡ እንደራሴ አደርጐ የሚመርጣቸው ነገ አንገት የሚቆልፍ ህግ ሲወጣ የሚያጨበጭቡ ብቻ እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ይገባዋል፡፡ ማወቅ ይገባዋል፡፡ በሁለተኛ ደግሞ በኢህአዴግ በኩልም ተመርጠው የገቡት የግድ መደገፍ ብቻ የሚጠበቅባቸው አይመስለንም፡፡ መቃወም በሚገባቸው ሰዓት በሆዳቸው ከሚቃወሙና በእጃቸው ከመደገፍ ተላቀው ያመኑበትን የመሞገት ልምድ ማዳበር አለባቸው፡፡ ይሄ ከታሪካዊ ተጠያቂነት ነፃ ያወጣናል በተጨማሪም ንቁ ፓርላማ መፍጠር የህዝቡም ኃላፊነት ነው፡፡ በሀገራችን ፖለቲካ ላይ በንቃት በመሳተፍ ተከራካሪ ፓርላማ በመፍጠር ላይ እንስራ፡፡

ጋዜጣችን “ፍኖተ-ነፃነት” ብለናታል፡፡ “ፍኖት” ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር “የነፃነት መንገድ” ማለት ነው!!

# የኢትዮጵያ መምህራን ጥያቄና የትምህርት ሥራ እውን መምህራን የደሞዝ ጭማሪ አልጠየቁም?



ሚዚያ 14 ቀን 2004 ከምሽቱ የሁለት ሰዓት ዜና ቀጥሎ ጠ/ሚኒስተሩ ፓርላማ ውስጥ ሆነው ቀደም ሲል ያካሄዱትን የጥያቄና መልስ ፕሮግራም እንዲደገም በሕዝብ ተጠይቋል ተብሎ ሲተላለፍ በቴሌቪዥን ተከታትያለሁ፡፡ ሕዝብ ከሳቸው አንደበት በቀጥታ መስማት ያለበት የሀገር አሳሳቢ ጉዳዮች ነበሩ፤ የተነሱት፡፡ እኔን ይበልጥ ያሳሰበኝ አቶ መለስ በመምህራን ጉዳይ ላይ የተናገሩት ነው፡፡ ቃል በቃል ባልጠቅሳቸውም ፍሬ ነገሩ እንዲህ የሚል ነበር፡-

«መምህራን የደሞዝ ጥያቄ አልጠየቁም፡፡ ያልተጠየቅነውን አላስተናገድንም፡፡ ማህበራቸው ድሬደዋ ተሰብስቦ የጠየቀው የደሞዝ እስኬል ማስተካከያ ነው፡፡ ፍትሀዊ ስላልነበረ ያስተካከልነው እስኬሉን ነው፡፡» አሉ አቶ መለስ፡፡ ሥራ ስለሚበዛባቸው

ሠንጠረዥ 1፡- የመምህራን የሁለት ዘመን ደሞዝ ከመሠረታዊ ምግብና ተለባሽ ሸቀቶች ዋጋ ጋር በንጽጽር

| ተ.ቁ. | የመምህራን ማሰልጠኛ ምሩቅ መነሻ የወር ደሞዝ | 1958/59 እ.ኤ.አ. | 1993/94 እ.ኤ.አ. |
|---|---|---|---|
| 1 | | 200 ብር | 230 ብር |
| 2 | የምግብ ምርቶችና መጠናቸው | ዋጋቸው በብር | |
| | 100 ኪሎ ጤፍ | 20-25 | 250-280 |
| | 3 ዕንቁላል | 0.15 | 1.00 |
| | 20 ዕንቁላል | 1.00 | 6.67 |
| | 1 ሊትር የምግብ ዘይት | 0.75 | 8.00 |
| | 1ኪሎ ሥጋ | 1.00 | 12.00 |
| 3 | የልብስና የጫማ ዓይነቶች | ዋጋቸው በብር | |
| | 1 ሙሉ ልብስ ሱፍ | 120.00 | 1,000.00 |
| | 1 ጥንድ የውጭ ጫማ | 25.00 | 400.00 |
| | 1 ጥንድ የሀገር ውስጥ ጫማ | 8-12.00 | 100-120.00 |
| | 1 ጥንድ የግር ካልሲ | 0.50 | 10-15.00 |
| | 1 ከፍተኛ ጥራት ያለው የውጭ ሸሚዝ | 15.00 | 120.00 |
| | 1 የውስጥ ልብስ (ፓንት) | 1.00 | 10.00 |

ምንጭ፡- አቶ ከበደ ፍሬሰንበት "Studies on Social Status of Ethiopian Teachers, 1994" ለሚለው ጥናታዊ ሥራቸው አስረጅነት አቶ አያሌው ሽበሺን "Survay of Salary Increments of Employees after Graduating in Certificate, Diploma and First Degree" ከሚለው ጥናታዊ ጽሁፋቸው እንደጠቀሷቸው፡፡/ አቶ ገሞራው ካሳ

ወይም መረጃ አቅራቢዎች ተዘናግተው የመሰንበቻውን የመምህራንን ከከተማ እስከ ገጠር መጯጯህ አልሰሙት እንበል? የመምህራንን 20ዎቹን ጥያቄዎች ስለቆዩ ረስተዋቸው ይሆናል፡፡ ማህበራቸው ያሉት ድሬደዋ መሰብሰቡን ከሰሙ በዛ ስብሰባ ላይ የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ ተነስቶ በከፍተኛ ደረጃ ማወዛገቡን እንዴት ሳይሰሙ ቀሩ? ከዚህ ሁሉ በላይ የሆነውን እራሳቸው የተሳተፉበትና በአንደበታቸው የተናገሩትን ላስታውሳቸው፡፡ የካቲት 22 ቀን 2001 ዓ.ም. ከመላው ሀገሪቱ ተውጣጥተው የተጠሩ ወደ 3 ሺህ የሚሆኑ መምህራንን በጽ/ቤታቸው የስብሰባ አዳራሽ ሲያነጋግሩ «አሁን የገበያው ሁኔታ ስላልተረጋጋ ደሞዝ ቢጨመርላችሁ ገንዘቡ እኪሳችሁ አያድርም፤፤ አይጠቅማችሁም፡፡ ገበያውን አረጋግተን ይጨመርላችኋል፡፡ በጭማሪው የምትጠቀሙት ያኔ ነው» በማለት ቃል ገብተው የነበረው ስለደሞዝ ጭማሪ እንዲጠይቁ በተፈቀደላቸው መምህራን ባይጠየቁ ኖሮ ከምን ተነስተው ነበር ተሰብሳቢውን እንደዛ ያስፈነደቁት? እሳቸው ቢረሱትም ጧት ማታ እጅ እጃቸውን የሚያዋቸዉ መምህራንና ቤተሰቦቻቸው አይረሱትም፡፡ እንደውም ከዛን ጊዜ ጀምሮ የደሞዛቸው 50% ቢጨመር፤ 100% ቢጨመር፤ ይሄን ያክል ቢጨመር፤ እያሉ መምህራን በሂሳብ አራት መደቦች ተጠምደው መክረማቸውን ማን በነገራቸው? የሀገሪቱ አቅም እስከምን ይችላል፤ ተገቢና ትልቅ ጥያቄ ነው፡፡ እንደ ድፍረት አይቆጠርብኝ እንጂ መካካድና መሸዋወድ ግን ለማንም ለምንም አይበጅም፡፡ መምህራን ከሰሞኑ የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ አላነሱም ማለት ትልቅ ስህተት ነው፡፡ በዚህ ላይ አቶ መለስ ጨርሶ እሰጥ አገባ ውስጥ መግባት የለባቸውም፡፡ እውነቱን ለማወቅ ቀላል ዘዴ አለ፡፡ ለ4 ኪሎ ቅርብ ከሆኑት ት/ቤቶች አንዱን ይጎብኙና መምህራንን፤ ተማሪዎችን፤ ወላጆችን፤ ርዕሰ መምህራንን ያነጋግሩ፡፡

«የደሞዝ ጭማሪ ሳይሆን የደሞዝ እስኬል ማስተካከያ ነው የተደረገው፡፡ ይሄን ማስተካከያ 99.9% የሚሆኑት መምህራን ደግፈውታል፡፡ ከ 3 መቶና ከ4 መቶ ሺህ በላይ ከሆኑት መምህራን መሀከል የተቃወሙት 5 መቶ ያክል ቢሆኑ ምንድን ነው ችግሩ?» አሉ ትንሽ ቆጣ ብለው፡፡ የእኔ ጥያቄ ለመሆኑ እነዚህን ቁጥሮች (99.9% እና 500) ከየት ነው ያገኟቸው? የአፍ ወለምታ ነው እንዳይባል ደጋግመው ነው የተናገሩት፡፡ ፀሐይ የሞቀውን የደሞዝ ጭማሪ

ወደ 11 የዞሯል

# ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች ሁሉ እንኳን ደስ ያላችሁ!



ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
mesayewa2011@gmail.com

መ/ር ደረጀ መላኩ
dereje.melaku@yahoo.com

ሰኞ ሚያዚያ 8 ቀን 2004 ዓ.ም ምሽት ላይ የጀርመን ድምጽ የአማርኛው ክፍል የተሠበረውን የነፃውን ፕሬስ ቤተሰብ ልብ የሚያጽናና ዜና ማሠማቱን የኢትዮጵያን ጉዳይ ሁሉ የምትከታተሉ ታስታውሣላችሁ፡፡

ለዶቼ ቬሌ ሬዲዮ የዋሽንግተን ዘጋቢ ጋዜጠኛ ዓለም አቀፉ «የፀሐፊዎች ነፃነት'' ተቆርቋሪ ''Pen international'' ሚያዚያ 5 ቀን 2004 ዓ.ም የወጣውን ጋዜጣዊ መግለጫ ዋቢ በማድረግ የሚከተለውን አስደሳች ዜና ለኢትዮጵያውያን ኖኝቶታል፡፡

ፔን ኢንተርናሽናል ''Journalist Eskinder Nega wins 2012 Pen freedom Award'' በሚል ርእስ ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ እስክንድር ነጋን ''A leading advocate for press freedom and freedom of expression in Ethiopia'' ሲል ገልጾታል፡፡

''The Ethiopian writer Eskinder Nega is that bravest and most admirable of writers one who picked up his pen to writ things that he knew would surely put him at grave risk''

በአምባገነኖች እስር ቤት ውስጥ የሚማቅቁ ጋዜጠኞችን ህይወት በቅርብ የሚከታተሉ አንድ የህሊና ሠው በበኩላቸው ሽልማቱ ሁለት መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ለአሜሪካ ድምጽ የአማርኛው ፕሮግራም እንዲህ ሲሉ ቃለ ምልልስ ሠጥተው ነበር፤ «ሽልማቱ በአንድ በኩል የነፃውን ፕሬስ አርበኞች ተጋድሎ ዋጋ እንዲኖረው ያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በወያኔ ኢህአዴግ አገዛዝ እስር ቤት ውስጥ የሚገኙ ጋዜጠኞችና የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች (አባላት) የፍርድ ሂደትን በተመለከተ ዓለም በትኩረት እንደሚያየው የጠቆመ ነበር» ብለዋል፡፡

የታሪክ ፌዝ ሆነና የዛሬ ሃያ አመት ግድም ገዢዎች ለመሆን ወግ የደረሳቸው የያኔዎቹ ታጋዮች ዛሬ በላቀ የኑሮ ደጃ ላይ የሚገኙት ኢህአዴጋውያን «እንዳያማህ ጥራው . . .» በሚል ዘዴ የነፃ ፕሬስ አብዮት ሻማ ለኮሱ፡፡ ይሄን ተከትሎ ለዚች ሀገር ታላቅ ህልም የነበራቸው ኢትዮጵያውያን በጋዜጣ ሥራ ላይ ተሠማሩ፡፡ እንደሚነገረው ከ200 በላይ የጋዜጣና በርካታ የመጽሔት አይነቶች ለህትመት በቅተው ነበር፡፡ በጥባጭ ካለ . . .እንዲሉ ሠፊ ተነባቢነት የነበራቸው የነፃው ፕሬስ ውጤቶች ቀስ በቀስ ከስመዋል፡፡

አንዳንዶች በራሣቸው ድክመት ከገበየው መውጣት ግድ ሲሆንባቸው በርካቶች ግን የሥርዓቱ ሠይፍ ተመዞባቸው ከነፃው ፕሬስ መንደር ተቆራርጠው ቀርተዋል፡፡ የተወሠኑት ግን እስርና እንግልት እንዲሁም ማስፈራሪያው ሳይበግራቸው እስከ ግንቦት 1997 ዓም ድረስ በስራቸው ላይ ነበሩ፡፡

ከእነዚህ ውስጥ እኔ በጣም የማከብራቸውና የማደንቃቸው እንደሁም የኢትዮጵያ የነፃ ፕሬስ ታሪክ ሲነሳ ምን ጊዜም ቢሆን የማይረሱት የሚከተሉት ይመስሉኛል፡፡

ለፕሬስ ነፃነት ሲሉ በማእከላዊ ወንጀል ምርመራ የእስር ገፈት ቀማሽ ሆነዋል፡፡ ለምሳሌም ያህል ጋሼ ሙሉጌታ ሉሌ፣ ጎሹ ሞገስ፣ አረጋ፣ ከበበው፣ ታዬ፣ ደርበው እና ትእግስት የሚረሱ ሠዎች አይደሉም፡፡

የኢትዮጵስ ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረው «ጋሼ ተፈራ አስማረ ሀውልት ሊቆምለት የሚገባ ሠው ነበር፡፡ ጽድቁ ቀርቶብኝ . . .» ሆነ'ጂ

«የኢትዮጵ ሲሳይ አጌና ፣ የሀዳር ዳዊት፣ ውብሸት ታዬ፣ ብዬአየሁ፣ ተመስገን፣ አጥናፉ አለማየሁ . . . ወ.ዘ.ተ» ውለታችሁን አንድዬ ይክፈለው እንጂ እንደናተ ያለ የሲቪል ጀግኖችን የሚያከብር መንግሥት እስካሁን በኢትዮጵያ አልተነሳም፡፡

ትንሽ ስለ እስክንድር

ጋዜጠኛ እና የፖለቲካ ተንታኝ የሆነው እስክንድር ነጋ ገድል ከነፃው ፕሬስ ውልደት ጀምሮ አሁን የመጨረሻው አፋፍ ላይ እስከ ደረሰበት ጊዜ የሚዘልቅ መሠለኝ፤፤

ብዙዎች ከእስክንድር ጋር እረጅሙን ጉዞ የጀመሩ ዛሬ አጠገቡ የሉም፡፡ ያ! እንደ እሳት የሚፋጀው የብእር ትሩፋታቸው ከአንባቢ ማእድ ከራቀ ሰባት አመት ሞላው፡፡ አንዳንድ የብእር ገበሬዎች እስር ቤት ባፈራዉ ህመም ምክንያት መተኪያ የሌላት ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡ ብዙዎቹ የሚወዷት ሀገራቸውን ጥለው ተሠደዋል፡፡ ለምሳሌ ጋዜጠኛ ቅዱስህብት በላቸው፣ ደረጀ ሀብተወልድ፣ የነፃው ፕሬስ ፊት አውራሪ የነበሩት አቶ ክፍሌ ሙላት፣ ከፍያለው ማሞ ይጠቀሳሉ፡፡

እስክንድር ግን ፍፁም ለየት ያለ ባህሪ ያለው ሠው መስሎ ታየኝ፡፡ ከመልካም ቤተሰብ ፍቅርን ሲመገብ ያደገው ይህ ልበ ሙሉ ጋዜጠኛ የምቾትና የተንደላቀቀ ኑሮውን በመተው ለኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት ሲል ከሰባት ጊዜያት በላይ ወደ ወህኒ አምባ ተወርውሯል፣ አንድ ባልታደለች ማለዳ ላይ ደግሞ ባልታወቁ ሠዎች ተደብድቦ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ይኼ ሁሉ ግን ከዓላማው አላዛነፈውም፡፡ ይህ ሠው አሁን ላለው ትውልድ የዓላማ ጽናት ተምሳሌ ነው ማለት ይቻላል፡፡

እስክንድር በእውቀት የመጠቀ ብቻ ሣይሆን የመልካም ባህሪ ባለቤትም ነው፡፡ ለዚህም ነው እንደ ጥጃ እያሠሩ የሚፈቱትን፣ በጋዜጠኘነት ሙያ እንዳይሰማራ ያገዱትንና የአይምሮው ጭማቂ የነበረውን መጽሀፍ ማሳተም አትችልም ያሉትን የዘመናችንን ፈርኦኖቹን አንድም ጊዜ በጥላቻ አይን ያላየው፡፡ ለዚህ ደግሞ ምስክሮቹ በጋዜጣ አሊያም በድረ-ገጽ የሚጽፋቸው በሣል ትችቶች ናቸው፡፡ እርግጥ ነው ይህን የለየለት

ወደ 8 ዞሯል

*አቶ ስዩም መንገሻ ወ/ሰማያት ይባላሉ፡፡ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ/አንድነት/ ማዕከላዊ ም/ቤትና የኢዲቶሪያል ቦርድ አባል እንዲሁም የድርጅት ጉዳይ ም/ሃላፊ ናቸው፡፡ ስለግላቸው፣ ስለፓርቲያቸውና በወቅቱ የአገሪቱ ፖለቲካ ዙሪያ ከባልደረባችን ብዙአየሁ ወንድሙ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡*

# ኢህአዴግ እውቀቱም ወዳጁም ማስመሰልና ጉልበቱ ነው ! !

➢ ስለ ትውልዶዎ፣ ትምህርትዎ የስራ ህይወትዎ ቢገልፁልኝ፡፡

የተወለድኩት እዚሁ አዲስ አበባ ሲሆን ያደኩት በደብረዘይት ከተማ ነው፡፡ በህግ ተመርቄ በግል ስራ እተዳደራለሁ፡፡ ማን መሆኔን በመፈለግ ላይ በመሆኑና ለአገርህ በህይወትህ ባለችህ እወቀትና ችሎታ አንድ ነገር ካለበረከትክ የማንነት ትርጉሙ ስለማይገባኝ ይኸው ይበቃል፡፡

➢ የፖለቲካ ህይወትዎን ቢገልጹልኝ

የፖለቲካ ተሳትፎ የጀመርኩት በመዐህድ የወጣት ካውንስል ነው፡፡ ከዚያም ኢዴፓን ከመሰረቱት የመጀመሪያዎቹ አመራር ከነበሩት ወጣቶች አንዱ ነበርኩ፡፡ ከኢዴፓ ጋር መቀጠል የማንችልበት ሁኔታ በመፈጠሩ ኢዴፓን ለቅቄ መዐህድ ተመለስኩኝ፡፡ መዐህድ ወደ መኢአድ ሲለወጥ አብሬ ሰርቻለሁ፡፡ በነበረበን የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲ አፈታት ችግርና በሌሎች በርካታ የፖለቲካ ምስቅልቅል መኢአድ ውስጥ ችግር ተፈጠረ፡፡ ብርሃን ለአንድነት ለዴሞክራሲ ፓርቲ ተፈጠረ፡፡ ፓርቲውን በዋና ፀሀፊነት ሳገለግል ቆይቼ አሁን ብርሃንና አንድነት ከተዋሀዱ በኋላ በአንድነት ውስጥ በመሳተፍ ላይ እገኛለሁ፡፡

➢ የወቅቱ የአገሩቱን ፖለቲካ እንዴት ይመለከቱታል

እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ሰዎች በኛ አገር ፖለቲካ ማለት በተለይ ተቃዋሚ ፓርቲን መቀላቀል ትርፉ መታሰር፣መንገላታት፣ ከፍ ካለም ሞት፣ከስራ መፈናቀል፣ሰርቶ ለመኖር ያማይቻልበት የተንቀለቀለ እሳት ውስጥ መግባት ተድርጎ እየተተረጎመ ነው፡፡ በትክክል ፖለቲካና ኮረንቲ በሩቅ እንደተባለው ተሸማቆ የመኖር ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ግን ሰዎች ያልፈለጉትን የመቃወም ባህል ካላሳደጉ ሄዶ ሄዶ ራሳቸው ኮረንቲውን ይዘው ያለ ብልሃት መሞትም ይኖራል፡፡

አሁን ባለንበት ዘመን ሁሉንም ጉዳይ የሚመራው ፖለቲካው ነው፡፡ ፖለቲካውን የሚመሩት በተለይ ስልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ከራሳቸው ውጪ ሌላውን ማድመጥ አይፈልጉም፡፡ ለህዝባቸው ፍላጎት ቅድሚያ የሚሰጡ አይደሉም፡፡ የኔ የሚሉትን ጉዳይ የማያስቀድሙ መሆን ነበረባቸው፡፡ ዛሬ በአብዛኛው የአፍሪካ መሪዎች አገራችንን ጨምሮ የያዙት ስልጣን እንዴት ማቆየት እንደሚችሉ የሚጨነቁ ናቸው፡፡ እኔን የነካኝ ዋ! በሚል ግለኝነት ላይ የተጠመዱ ናቸው፡፡ የሥልጣን ጊዜ ዘላለማዊ አይደለም፡፡ ግን እኛው ለራሳችን ተስፋ ልንፈጥር ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ እንዲያው ዝም ብሎ አይገኝም፡፡ እስኪ ሁሉም ስለራሱ ያስብ፤ ያሰላስል፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ



እራሱን ነፃ ስለማውጣት ሊጨነቅ ይገባል፡፡ እዚህ ላይ የእንቁራሪቷን ጉዳይ ማየት ይጠቅማል፡፡ «በአንድ መንደር የዕሳት ቃጠሎ ይነሳል፡፡ በአንድ ትንሽ ኩሬ መሰል የተጠራቀመ ውሃ ውስጥ እንቁራሪት እሪታዋን ታቀልጠዋለች፡፡ እባካችሁ ያን እሳት አጥፉት እያለች ትጮሃለች፡፡ አንድ ሰው በአካባቢው ሲያልፍ ይሰማና አንቺ ደግሞ ምን ልሁን ነው የምትይው? እሳቱ ያለው ከአንቺ በራቀ ቦታ ላይ ነው፤ ያውም ውሃ ውስጥ ሆነሽ ለምንድ ነው? በጩኸት የምታደነቁሪን ብሎ ቢጠይቃት እሳቱ እዚያው ካልጠፋ ወደዚህ መድረሱ አይቀርም፡፡ ያኔ እሳቱን ለማጥፋት ይህንን ውሃ መጠቀማቸውም አይቀርም፡፡ በዚያን ጊዜ ከውሃው እሳቱን ለማጥፋት ሲቀዱና ሲደፉ እኔም ወደ እሳቱ መወርወሬና መሞቴ ነው፡፡ እኔ የምጮኸው ለራሴ ነው» አለችው ይባላል፡፡

ስለዚህ ሁሉም ነገር ቤታችንን እስኪያንኳኳ አንጠብቅ ሁላችንም ለራሳችን እንጩህ፡፡ ያን ጊዜ ድምፃችን ሃይል ይኖረዋል፡፡ በመሰረቱ ነፃነት ዝም ብሎ አይገኝም፡፡ ዋጋ ያስከፍላል፤ ዋጋ የሚያስከፍል ነገር ደግሞ ወጪ አያጣም፡፡ እኛ ለዛ መዘጋጀት አለብን ፡፡ ለሰላማዊና ህጋዊ ትግል ቁርጠኝነት ማሳየት ይገባናል፡፡ በመዐህድ ወጣት ካውንስል እያለሁ አንድ መፈክር ነበረን፡፡ «እየተደበደብን፣ እየታሰርን፣ እየሞትን፣ የዴሞክራሲን ጽዋ ለአምባገነኖች እናስጎነጫለን»፡፡ የሚል ነበር፡፡ ስለሆነም እስኪ በዚህ ትውልድ ስልጣን በጉልበትና በጠመንጃ የሚተላለፍበትን መንገድ ለማስቀረት እንስራ፡፡ ከልባችን እንታገል፡፡ እርግጥ ነው! ጉዳዩ በጣም በጣም ከባድ ይመስላል በተለይ አሁን በአገራችን ካለው የሥልጣን ጥማትና የወንበር ፍቅር አንፃር ሲታይ ሸክሙ ከባድ ነው፡፡ ሆኖም ግን ሁሉም የራሱን ከተወጣ የምንመኘውን ዴሞክራሲያዊ እና ነፃነት ማግኘታችን አይቀርም፡፡ ብቻ እኛ እራሳችንን ነፃ ከማውጣት እንጀምር፡፡ ያኔ ነፃ አገር ለልጆቻችን ማስተላለፍ እንችላለን፡፡ ዛሬ ልጆቼን ላሳድግበት፤ በሰላም ልኑርበት እያልን በፍርሃት ቆፈን ውስጥ ሆነን የድርሻችንን ካልተወጣን እንኳን ነፃ አገር ነፃ ንብረት ልናወርስ አንችልም፡፡ እንኳን በሰላም አጎንብሰን ለመኖር የማንችልበት ሁኔታ ውስጥ እንወድቃለን፡፡ ከዚህ ሁሉ በፊት ለራሳችን ስንል ባመንበት ፅንተን እንቁም፡፡

➢ ኢህአዴግን ትናንትናና ዛሬን እንዴት ያነጻጽሩታል?

የትላንቱ ብሶት የወለደው የኢህአዴጋውያን ስብስብ፤ ጭቆና አስመርሯቸው ለዲሞክራሲና ለነፃነት ያደረጉት ተጋድሎ መሆኑን በተደጋጋሚ ነግረውናል፡፡ እነሱ በተራቸው ዛሬ አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ብሶት በብሶት አድርገውታል፡፡ ልክ ደርግ በግራ “እጁ «እፍኝ የማይሞሉ ወንበዴዎች” እያለ በቀኝ እጁ “ለማንም ለምንም የማይበገር የመከላከያ ሰራዊት እንገነባለን” ሲል ተፈረካክሶ ቀረ፡፡ ዛሬም ኢህአዴግ ጥቂት አበላት፣ ደጋፊዎችና የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ውጭ ብሶት ውስጥ ብንሆንም ለኢህአዴግ “ጥቂት ምንትሶ ያልተሳካላቸው፣ እንዲህ ያልሆነላቸው፣ እንዲያ እንዲሆን የሚመኙ” ወዘተ እያለ መስሚያ ጆሮ፣ የሚመለከት ዓይን፣ የሚያስተውል አእምሮ የነሳው ይመስላል፡፡ በመሰረቱ ዛሬ ኢህአዴግ የለየለት አምባገነን ስብስብ ሆኗል፡፡ የዛሬው ኢህአዴግ ይቺ አገር የሁላችንም እንደሆነች የተሳነው ሆኗል፡፡ በታሪክ አጋጣሚ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ሃያ አንድ ዓመት ሆኖታል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ታሪካዊ ማንነታችንን ለመበረዝ ሞክሯል፡፡ በቅርሶቻችን ላይ የተሳሳቱ አመለካከቶች አራምዷል፡፡ ባህላዊ ዕሴቶቻችንና በእምነታችን ላይ ሳይቀር ጣልቃ ገብቷል፣ ብቻ ብዙ ብዙ ነገሮች ተፈፅመውብናል፡፡ ዛሬም የአገሪቱን ታሪክ ለማበላሸት ቅርሶቻችንና እሴቶቻችንን

ለማውደም ዜጎቿን ለማዋረድ ሀብትና ንብረቷን ለማዘረፍ ተግቶ ይሰራል፡፡ የዛሬ 20 ዓመትአካባቢ እልፍ አእላፍ ጀግኖች በተሰውለት ባንዲራችን ላይ እንደማስታወሰው የጥፋት መልእክቱ «ሀ» ብሎ የተጀመረ ይመስልኛል፡፡ በመሰረቱ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ባንዲራችን አርማችን፣ መለያችን ነው፡፡ ሰንደቅ ዓላማ የነፃነት ምልክት ነው፡፡ ሰንደቅ ዓላማ የማንነት መለያ የአንድ ህዝብ መከበሪያ፣ የባህሉ የመንፈሳዊ ቅርሱና የተስፋው ምንነት ነው፡፡ ራሱን የሚያውቀውም በዚያው ነው፡፡ « እኛ ማን ነን? ምንስ ነን?» በማለት ለሚቀርቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች ከሰንደቅ አላማ ዓርማነት ሰፊና ውቅያኖስ ትርጉም መልስ ይገኝበታል፡፡ አንድ ታላቅ አሜሪካዊ ምሁር ባንድ ወቅት የተናገረው ቃል ትልቅ መልስ ይሆነናል ቃሉ «ማን መሆናችንን ልናውቅ የምንችለው ማንም አለመሆናችንን ስናውቅና በአብዛኛውም ማንን እንደምንቃወም ለማወቅ ስንችል ነው፡፡» ብሏል፡፡ ማንነታቸውን ሲፀየፉ፤ ያልሆኑትን ካልሆኑበት ስፍራ ሲፈልጉ፤ ማን መሆናቸውን ለማወቅ ሳይችሉ፤ በጨለማ እያነጣጠሩበት ያለው ወዳጅ ይሁን ጠላት ለመለየት ሳይችሉ፤ እንዲያው በደፈናው ራሳቸውን ያሳወሩትን ማየት የለብንም በሚፈፀሙ ድርጊቶች መቆጨት አንድ ነገር ሆኖ፤ ለምን ይሄን ያደርጋሉ? ብሎ ማሰብ ብልህነት ይመስለኛል፡፡ ባንዲራችን ጨርቅ ተብሎ ሲጣጣል ያኔ መሆን የነበረበት በተባለው ነገር ከመቆጨት ይልቅ እንዴት ወደ ቀድሞ ክብሩ ይመለሳል? በሚል መጨነቅ ይበጀን ነበር፡፡ ያኔ የተጀመረው የማንነት ማጥፋት ተግባር ዛሬ የት ላይ እንዳለ የምናውቀው ጉዳይ ነው፡፡

➢ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያሉበት ተጨባጭ እውነታ በእርሶ እይታ ምን ይመስላል?

በኢትዮጵያ የተቃዋሚ ፓርቲ እንቅስቃሴ ውስጥ ከአጋጠሙ የስኬትም የውድቀትም ወቅቶች አንዱና ዋነኛው የ1997 ዓ.ም አገር አቀፍ ምርጫ ውጤት እና እሱን ተከትሎ የተፈጠሩ የመበታተን ድርጊቶች አሉ፡፡ የርስ በርስ አለመስማማታችን ለኢህአዴግ ሰርግና ምላሽ ሆኖታል፡፡ ታሪካችን ብዙ ነገሮችን አስተምሮናል፡፡ ኢትዮጵያ ለዘመናት መስዋዕት የሚሆኑላት፣ የሚሞቱላት አጥታ እንደማታውቀው ሁሉ፤ የሚያዋርዷትም ተቸግራ አታውቅም፡፡ ሰላማዊ ትግል እጅግ ውስብስብ ትዕግስት የሚጠይቅ፣ መረጋጋትን የሚሻ፣ ብዙ ድካም፣ ብዙ መሰዋዕትነትን የሚያስከፍል ነው፡፡ ስለዚህም ነው ዛሬ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራረና አባላት ጋዜጠኞች የፖለቲካ ተንታኞች፤ ለዕስር የተዳረጉት፡፡ በርካቶች ለስደት ለእንግልትና ለሞትም የሚበቁት ፡፡ ትግሉ በሃሳብ የበላይነት ለማሸነፍ ያውም በሁሉም መስክ ጡንቻው ከፈረጠመ ሃይል ጋር በመሆን ከባድ የትግል ስልት ነው፡፡ ሰላማዊ ትግሉ ከሁሉ በላይ ስለ ማንነትና ታሪካችን ግድ የማይሰጠው ለአገሪቱ ክብርና አንድነት ከማይጨነቅ ጋር መሆኑ ሲደመር ክብደቱን ያገዝፈዋል፡፡ ይህ ትግል የብዙ ህዝብ ድጋፍ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ መደምደሚያውና ውጤቱ በምርጫ ማሸነፍ በመሆኑ ኢህአዴግ በእውቀት ላይ የተገነባ ትግል በማድረግ ማሸነፍ ይቻላል፡፡ በስሜታዊነት በእርግማን፣ በሀሜት፣ በሹክሽክታ፣ በመፈክርና በጥላቻ ብቻ የተሸነፈ መንግስት እስካሁን አልታየም፡፡ ትናንት እንዲህ ነበር፤ ከትናንት ወዲያ እንደዚያ ነበር፤ ከዚያ በፊት እንደዚህ ነበር፤ ማለት ለመማሪያ ካልሆነ አይጠቅምም፡፡ አሁን የሚያስፈልገን ዛሬ እንዲህ መደረግ አለበት ነገ ያ ሊሆን ይገባል የሚሉ ሀሳቦች ናቸው፡፡ በትናንት ትዝታና በትናንቱ ቁጭት ዛሬን ማሳለፍ መጭውን እያጨለሙና እየተደናበሩ ወደ ለየለት አረንቋ ውስጥ ይከታል፡፡ ህዝቡ ለውጥ ያስፈልገኛል ብሎ የሚያምን ከሆነ በሚያምነው ፓርቲ ዙሪያ መሰብሰብ አለበት፡፡ ነገም ሌላ ስህተት እንዳይፈጠር ወደ ተቃዋሚዎች መቅረብ አለበት፣ መተቸት አለበት፣ ስህተቱን አሁኑኑ መጠቆም አለበት ከዳር ወይም ከመሀል መቆም ወደፊት ለመራመድ ዋስትና አይሆንም፡፡ በእርግጥ ሰላማዊ ትግሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ አልተሰራበትም ሰላማዊ ትግል ብዙ ዘርፎች አሉት በዚህ ወቅት ጋዜጣዊ መግለጫ ከመስጠትና ከማሰራጨት የዘለለ ትግል ተቃዋሚ ፓርቲዎች እያደረግን አይደለም፡፡ ሌሎች በርካታ የሰላማዊ ትግል ስልቶች አሉ፡፡ ምንም እንኳ ህዝቡ በዚህ ረገድ ከዚህ የዘለለ ምን አደረጋችሁ ቢል ተገቢም አስፈላጊም ጥያቄ ነው፡፡ ትግሉን አንድ እርምጃ ወደፊት ማስኬድ ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም የህዝቡ ድጋፍም ከምንጊዜውም በላይ መጠናከር አለበት ፡፡ ያለምንም ማወላወል ከተቃዋሚዎች ጎን ሊቆም ይባል፡፡ ያኔ የተግባሩም ተሳትፎ የውጤቱም ተቋዳሽ መሆን ይችላል፡፡ በተረፈ 1997 ዓ.ም ብቻ በመመኘትና ስለዚያ ጊዜ በመናገር ለውጥ ሊመጣ አይችልም ፡፡ ታላቁ ሊቅ ኮንፊሽየሥ «ሺ ጊዜ ጨለማን ከመርገም አንድ ሻማ ማብራት ይሻላል፡፡» እንዳለውም የችግሩ አካል የነበርን አካለት ቅንነት ካለ መፍትሄው ያለው እኛው ጋር ነው ፡፡ ከየት ይገኛል ለሚለው ከያንዳንዳችን ከውስጣችን ይመጣል፡፡ በሌላ በኩል ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፈን የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና አካላት በመጀመሪያ ምን እየሰራን እንደሆነ ቆም ብለን ልንመረምር ይገባል፡፡ ማንን ነው የምንቃወመው? ለምንድነው የምንቃወመው? ምን ለማግኘት ነው የምንቃወመው? ጉዳዩን በጥናት ላይ የተመረኮዘ በጥልቅ ትንተናዎች የታገዘ ካደረግነው ያለምንም ጥርጥር መልሱን እናገኘዋለን፡፡ መሰረታዊ የአስተሳሰብ ልዩነት ከሌለን ተበታትኖ መጓዙ ድካማችንን ያበዛዋል፡፡ ውጤት አልባ ከንቱ ልፋት ይሆንብናል፡፡ ላለፉት 21 ዓመታት አይተነዋል፡፡ እኛ ስንገነባ ኢህአዲግ በረዥም እጁ በህግም በጉልበትም ሲበትነን፤ እኛም ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሃኒቱ ለመሆን ስንጥር ሁለት ደካሞች እየሆንን ግራ ተጋብተን ህዝቡንም ግራ ስናጋባው ቆይተናል፡፡ ለዚህ ህዝብ ቆመናል ካልን የምር እንቁምለት እንጂ አንቁምበት፡፡ ምርጫው አንድና አንድ ነው፡፡ ለውጤታማነት ተመሳሳይ ክንፍ ያላቸው ርግቦች አንድ ላይ ይበራሉ እንደተባለው አንድ አይነት ዓላማ ያለን ተዋህደን አንድ መሆን ጊዜው የሚጠይቀው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ ካልሆነ ለማን እንደቆምን ምን እንደምንፈልግ የምናወቀው እኛው ብቻ እንጂ ህዝቡ አይሆንም፡፡ በዚህ ረገድ አንድነት ጋር ግልጽ አቋም አለ፡፡ ሌሎችም ተመሳሳይ ርምጃ ለመውሰድ የነገ ቀጠሮ አያስፈልግም፡፡ ጊዜው አሁን ነው፡፡ የፓርቲ አባላትም ሆኑ ህዝቡ ይህንኑ አጠናክሮ ሊጠይቅ ይገባል፡፡ ሁሉም ለለውጥ ይትጋ እላለሁ፡፡



➢ ሰላማዊ ትግሉና የዐገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር እንዴት ይገልጹታል

ከኋለኛው ልነሳልህና የፖለቲካ ምህዳሩ እየጠበበ ነው፡፡ ጥያቄው እሱ አይደለም፤ ይሄ የኢህአዴግ ዋነኛ ስራው ነው፡፡ እያጠበቡ እያጠበቡ መሄድ መደበኛ ሥራቸው አድርገውታል፡፡ ህጋዊ ለመምሰል በየጊዜው በየአቅጣጫው የአፈና ህጎችን የአፈና ደንቦችን፣ የአፈና መመሪያዎችን ያወጣል፡፡ እኔ እሱ ሲያጠብ በኛ በተቃዋሚዎች በኩል ለማስፋት ምን እያደረግን ነው? የሚለው የበለጠ ያስጨንቃል፡፡ በቃ ትግላችንን አጠናክረን ማስፋት አለብን፡፡ ሰላማዊ ትግሉን ሰላም እያሳጣው ያለው ኢህአዴግ ራሱ ነው፡፡ አሁን የሰላማዊ ትግሉ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል፡፡ አየህ ኢህአዴግ በሰላማዊ ትግል በሀሳብ የበላይነት ማሸነፍ አያውቅበትም፡፡ ለኢህአዴግ ጦርነት ይቀለዋል፡፡ ምክንያቱም ለ17 ዓመት ከደርግ ጋር ሲዋጋ ቆይቶ በጉልበት ስልጣን የያዘ ሃይል ነው፡፡ ይህ ሃይል አሁን እንዴት በሃሳብ የበላይነት ይዋጋ! መንገዱን አያውቅም፡፡ ለኢህአዴግ የሐሳብ የበላይነት እንደመግደል ቀላል ሊሆንለት አልቻለም፡፡ ስለዚህ ስርዓቱ እንደጣሊያን ወረራ ዘመን በከፋፍለህ ግዛ ስልቱ የሚመራ ነው፡፡ በብሄርና በጎሳ አሁን አሁን ደግሞ በሃይማኖት ያቧድኗል! ፍርሃት በህዝቡ ውስጥ ይለቃል፡፡ በተለያየ መንገድ ያስፈራራል፤ ነጋዴ ከሆነ በታክስ ወይም ሌላመንገድ ይፈለግለታል፣ ገበሬ ከሆነ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ይከለከላል፣ ሰራተኛ ከሆነ በስራው የመባረር ዕጣ ይገጥመዋል፤ ወጣቱና ሴቱ በፎረም በቅንጅት በሊግ ወዘተ እንዲቧደን ተደርጓል፤ አገር ምድሩን በ5ለ1 ጠርንፎ ሁሉም የኔ በሚል አባዜ ውስጥ ይገኛል፡፡ ከዚህ ሁሉ ውጭ የሆነ ደግሞ የፀረ ሽበር ህግ አለበት፤ ብቻ ዙሪያውን በማጠር አስፈራርቶ አስጨንቆ ደጋፊ ያደርጋል፣ አባል ያደርጋል፡፡ የተረጋጋ ዜጋ የተረጋጋ ማህበረሰብ ማየት አይፈልግም፡፡ ሁሉም ዜጋ በሥጋት በጭንቀት ውስጥ እንዲኖር ይፈልጋል፡፡ እዚህ ላይ አንድ ጓደኛዬ ያጫወተኝን ልጥቀስልህ አንድ የሚያውቀው ሰው በ1997 ዓ.ም የታወቀ የቅንጅት ደጋፊና የአንደኛው የፖለቲካ ፓርቲ አባል ነበረ፡፡ ከዚያ በኋላ ምርጫውም ተካሄደ የሚሆነው ሁሉ የቅንጅት አመራሮችም ታሰሩ፡፡ ይህ ሰው ከዚያ ስራውን በነፃነት መስራት አልቻለም ከዚህ በኋላ የመጨረሻ አማራጭ የመሰለውን እርምጃ ወሰደ፡፡ የኢህአዴግም አባል ሆነ፡፡ ይሁን እንጂ ካድሬዎቹ ይህ በቂ አይደለም፡፡ ስለኢህአዴግ በመድረክ መቀስቀስ አለብህ ብለውት አረፉ፡፡ ግለሰቡም ይህንንስ አልሞክረውም፡፡ ብሎ በችግር ላይ እንደሚገኝ አጫውቶኛል፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግ ዕውቀቱም ወዳጁም ማስመሰልና ጉልበቱ ነው፡፡ ከተፈለገ የጨዋታውን ህግ ይቀይረዋል፡፡ መፈናፈኛ በማሳጣት በሰላማዊ ትግሉ ውስጥ ተሳትፎውን አቅም በፈቀደ መጠን ያሳሳዋል አቅም ያሳጣዋል፡፡ ኢህአዴግ ማንንም አያምንም፤ የተለየ ሀሳብ ያራመደ ሁሉ የወንጀል ታርጋ ይለጠፍበታል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በአገራችን ያለውን የህብረተሰቡን ህይወትና አኗኗሩን እንዴት ይመለከታል?

መቼም በዓለም ላይ እነደ ኢህአዴግ መንገስት በራሱ ፕሮፓጋናዳ የሚዝናና፣ የሚረካና የቁጥር ጫወታ የሚወድ ያለ አይመስለኝም፡፡ እኔ የኢኮኖሚ ባለሞያ አይደለሁም፡፡ ኢህአዴግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ15 በመቶ በላይ ዕድገት ማስመዝገብ አይችልም እንጂ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ኢኮኖሚያችን ከ20 በመቶ በላይ ዕድገት አስመዘገብን ከማለት አይመለስም፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገት የቱንም ያህል ይሁን በህዝቡ የኑሮ ሁኔታ ላይ ምን ለውጥ አመጣ ነው ጥያቄው? ህብረተሰቡ በኑሮ ውድነት፣ በዋጋ ግሽበት የሚገባበት ጠፍቶት ሚዲያው ጧት ማታ ስለጥጋባችን ይተርክልናል፡፡ ልማታዊ አርሶ አደር፣ ልማታዊ ጋዜጠኛ፤ ልማታዊ የማስታወቂያ ባለሞያ፣ ልማታዊ አርቲስት፣ ሌላም ሌላም ልማታዊ በየዕለቱ የሚፈረከባት ሀገር ሆናለች ኢትዮጵያ፡፡ ብቻ ልማታዊ የሚል ቃል ከፊቱ ካልገባ ቃሉ የማይጥም ይመስል፤ በልማታዊነት ስብከት ጠግበናል፡፡ እስካሁን ያልሰማነው ወደፊት የምንጠብቀው ልማታዊ የተቃዋሚ ፓርቲ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ቁም ነገሩ ተጨባጩ እውነታ የየዕለት ኑሮዐችን ላይ ጠብ የሚል ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል ኢህአዴግ በኢኮኖሚ አደኩ ስላለ በሌሎች ነገሮች ላይ ያ ዕድገት አለ ተብሎ እንዲታሰብለት ይፈልጋል፡፡ አንድ አገር በኢኮኖሚ አደኩ ስላለ ብቻ ያውም በማያሳምን መንገድ ሌሎች ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች አከበረ ማለት አይደለም፡፡ የኢህአዴግ ወዳጅ የሆነችው ቻይና በዓለም ላይ ኢኮኖሚያዊ እመርታ ካሳዩ አገሮች ግምባር ቀደም ናት፡፡ ምንም እንኳ በቁጥር የኢህዴግ አድጌያለሁ ቢበልጥም አለም የኢኮኖሚ እድገቷን የተቀበላት ቻይና ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በከፍተኛ ሁኔታ የሚጣስባት አንድ አስተሳሰብ ለአንዲት ቻይና በሚል ወጥ አስተሳሰብ ውስጥ ያለች አገር ነች፡፡ የኛ አገር መንግስት ዕድገት ማጂክ ነው፡፡ ለራሱ ብቻ የሚታየው ይመስለኛል፡፡ ዕድገት በዜጎች የኑሮ ሁኔታ ላይ ለውጥ ካላሳየ እንዴት ነው ቀመሩ? እድገት ሲመጣ ችግር ይበረታል? የሚባል ሳይንስ አለ እንዴ? ካለም ይህን መፀሀፍ ከሶሻሊስት ፍልስፍና ውስጥ ቢሆን ወይም እነሱ ካነበቡት፣ ከተረዱት፣ ይጠቁሙንና አይተንና ተረድተን እንመናቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሁል ጊዜ በኢኮኖሚ ትንተናቸው የዋጋ ግሽበት የኑሮ ውድነት ሲነሳ ስለ ስንዴ፣ዘይትና ዱቄት ግዥ ይነግሩናል፡፡ በቃ ይኸውነው ዘላቂ መፍትሄአቸው፡፡ ይህ ከሆነ አንድ አገር ራሱ ባመረተውና ባፈበረከው እንጂ በግዥ ላይ እንዴት መፍትሄ ይገኛል ብሎ ይቀመጣል? ያውም ራሳቸው እንደነገሩን ስግብግብ የሚሏቸው ነጋዴዎች የተገዛውን እየቸረቸሩ ባሉበት ሁኔታ ይህ መፍትሄ ሊሆን አይገባም፡፡ በዚህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ትንታኔ ወይ ከሳቸው ካልሆነም አማካሪዎቻቸው ላይ ችግር አለ፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግ በኢኮኖሚ አደኩ ማለቱን አልተው የኑሮ ውድነቱና የዋጋ ግሽበቱም በየዕለቱ መናሩን አላቆመም፤ በጅጉ ሊታሰብበት ይገባል፡፡

➢ በመጨረሻም የሚሉት ካለ?

በኢህአዲግ የሚመራው መንግስት ለተቃዋሚ ፓርቲ ያለው አመለካከት የተሳሳተ ነው፡፡ በተለይ በእውነት በሚቃወሙት ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶች ከፀረ ሰላም ድርጊቶች ጋር በማዛመድ የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ይህ ፍፁም ተገቢ አይደለም፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲ መኖር ለዴሞክራሲያዊ ሂደቱ ጉልህ ድርሻ

ወደ 15 የዞሯል

# "የሕዳሴው አርቲስቶች"

መንገሻ ክሉ
mengeshakilu@gmail.com

ከሕዳሴው ግድብ ጋር ተያይዞ ግድቡ ያለዳንኪራና ጮኸት አይቆምም የተባለ ይመስል ለቁጥር ያታከቱ ነባርና አዳዲስ ዘፋኞች ከነጠላ የቀለሉ ነጠላ ዜማቸውን ለቀዋል፡፡ አንዳንድ ሃሜተኞች ማህበራትና የመንግሥት መስሪያ ቤቶችም ነጠላቸውን ሊለቁ ነው ይላሉ፡፡ ከዛም ወርዶ ከየክፍለ ከተማውና ወረዳው እንዲሁም ከየቀበሌው መንግሥት ለዛ የሌላቸውን አንዳንድ ነጠላ ዜማ ሊሰበስብ አቅዷል ይባላል፡፡

አንድ ወዳጄ ‹‹እነዚህ ዘፋኞቻችን ምን ነክቷቸው ነው ድምፃዊ ካድሬ የሆኑት›› ቢለኝ ምናልባት ሀገራቸውን ስለማያውቋት ይሆናላ ስለው፣ መልሶ ‹‹ብዙዎቹ አምነውበት ሣይሆን ከካድሬዎች የቀረበላቸው የድምፃዊ ካድሬ ሁኑ ጥያቄን ዕምቢ ማለት አስፈርቷቸው ነው ይባላልም›› አለኝ፡፡ እኔ ግን ሌላ መላምት አለኝ አለኩት፤ ምናልባት ብዙዎቹ በካሴት ሥራ ተስፋ ቆርጠው ይሆናል፡፡ ወዳጄም በመገረም እያየኝ ጭንቅላቱን ከላይ ወደታች በመነቅነቅ ‹‹አሀ! ለካስ ለዚህ ነዋ . . . ብሎ የታዋቂ አርቲስቶቻችንን ስም በየተራ እየጠራ እነ እከሌ እነ እከሊት ለህዳሴው ግድብ ያልዘፈኑት?›› ሲል ራሱን ጠየቀ፡፡ ለነገሩ በሀገር ሀብት ጡንቻውን ላፈረጠመ ገዢ መደብ ማጐብደድ እንጂ አቅም ከከዳው ደሀ ህብረተሰብ ጐን መቆም ምን ይጠቅማቸዋል? በርግጥ የትኛውም ዜጋ በተለይም የጥበብ ሰዎች በየትኛውም የመንግሥት ስርዓት ውስጥ ለገዢው መደብ ሣያጐበድዱ ለሀገራቸው ሁለንተናዊ ጥቅም ከመንግሥትና ከህዝብ ጋር አብረው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን ለዴሞክራሲና ለነፃነት ጥያቄ፣ ለሉአላዊነት፣ ለፍትህ መጓደል፣ ለሀገራዊ አንድነት መፈረካከስ፣ ለኢኮኖሚው ውድቀት፣ለዜጐች ክብር ማጣትና ስደት ባጥንታችን ስላስቀረን ሙሰና ወዘተ ወዘተ የተዘጉ የዘፋኞቻችን አንደበት ዛሬ አንደምን ለህዳሴው ግድብ ተከፈቱና የኢህአዴግ የፕሮፖጋንዳ ሠለባ ሆኑ?

በርግጥ ለዘፋኞቻችን ልናዝንላቸውም ይገባል፤ ምክንያቱም በነዚህና ከላይ በዘረዘርኳቸው ዋንኛ ጉዳዮቻችን ላይ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ሊሆን የችላልና፤ ወይም የነሱ የሕይወት ፍልስፍና በልቶ ከማደር የዘለለ ላይሆን ይችላል፡፡ ብዙዎቹ ‹‹ሙያችን እንጀራችን ነው›› ሲሉ አድምጠናቸውዋልና፡፡

ሌላው ከተፈጥሮ ያገኘውን ጥሩ ድምፅ ይዞ ታዋቂ ዘፋኝ የሆነ ሁሉ የተለየ አስተሣሰብ ልንጠብቅበት አይገባም፡፡ ቅርብ ጊዜ አርቲስት ሙሉ ዓለም ታደሰ አላቲኖስ የፊልም ማህበር ተጋብዛ በነበረችበት ፕሮግራም ላይ "ታዋቂ ሰዎች ሁሉ አዋቂዎች አይደሉም!" በማለት ከታወቂ ሰዎቻችን ሁሉ የተለየ ነገር አንዳንጠብቅ ጠቁማን ነበር፡፡

አብዛኛው የሕዳሴው ዘፋኞች የሚዘፍኑት የዘፈን ግጥም ከሚመለከተው ክፍል ተለክቶ አሊያም ተስማምቶበት የቀረበ ሲሆን የሰንኞቹ ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትርጉም የገባቸውም አይመስለኝም፡፡

ገጣማዎቹም ቢሆኑ ወይ የሀገራቸውን ሁለንተናዊ መልክ በትክክል አያውቁትም፣ አሊያም እያወቁ ባለሥልጣኖቻችንን ደስ ለማሰኘት ለወቅታዊ ፖለቲካ ፍጆታ ብቻ እንዲውል አስበው መሆን አለበት የፃፉት፡፡

የገጣሚ ሞገስ ተካን "ጉዞ ጀምረናል" የተሰኘውን ዜማና ግጥም ስንኝ በስንኝ ብናይ በስንኞቹ ልክ የገጣሚውን የግንዛቤ ማነስ እናያለን፡፡

ህብረታችን ዕጥፍ ድርብ
ሆኗል በህዳሴ ግድብ

እነዚህን ሁለት ስንኞች ተንትኖ ማየት በጣም አሰልቺ ስለሆነ አልሞክረውም፡፡ ባጭሩ ግን ይሄ ሕዝብ ደሞክራሲ፣ነፃነትና አንድነት እንጂ አንድ ሺህ የሕዳሴ ግድብ ቢገነባለት ህብረትን አያመጣለትም!


የህዳሴ ጉዞ ጀምረናል ጀምረናል
ወደኋላ ማን ይመልሰናል?
ከእንግዲህ ማን ይገታናል?

የህዳሴ ጉዞ የምጀምረው ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት ሲሆንና የጋራ ራዕይ ሲኖረን ብቻ ነው፡፡ እናም የሕዳሴ ጉዞ ጀምሬአለሁ ብሎ የሚገሰግስ ካለ ማንም ሣይገታው በራሱ ጊዜ እውነታ ይገታዋል፡፡ ይሄ ደግሞ ነባራዊ ህግ ነው፡፡ ኢህአዴግ አንድ ነገር ጀምሬአለሁ ካለ አልጀምርም ማለቱ ነው፡፡ ወይም በአንድ ጉዳይ ላይ አበክሮ የሚያወራ ከሆነ በዛ ጉዳይ ዙሪያ ትልቅ ክፍተት አለበት አሊያም ከጉዳዩ ጀርባ ድብቅ ፍላጐት አለው ማለት ነው፡፡

የፍቅረ አዲስ "ባቡሩ" ዜማም በአስተዛዛቢና አስገማች የውሸት ፕሮፖጋንዳዎች የተሞላ ነው፡፡ የሰለቸነውን የኢህአዴግን የፖለቲካ ፕሮፖጋንዳ ጥሩ በሚባል ስነ ግጥማዊ አደራረድርና ዜማ በማቅረብ ማንንም ማሣመን አይቻልም፡፡ ለመሆኑ ፍቅረ አዲስ ያዜመችለት ባቡር ሕዝቡን ከጫኑት ፉርጐዎች ተቆርጦ ብቻውን ወደ አደገኛ አቅጣጫ እየተንደፋደፈ መሆኑን ታውቃለች? እኛ ገና እውነተኛውን ወደ ግባችን የማያደርሰንን ባቡር ቆመን እየጠበቅን እንደሆነስ? ዘፋኞቻችን በየጉደዩ ላይ ሁነኛ አማካሪ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ገጣሚዎቹም ሆኑ ዘፋኞቹ የህዳሴውን ግድብ በተመለከተ ስላለው ሕዝባዊ ድጋፍ በቴሌቪዥን ከሚያዩት ተደጋጋሚና አሰልቺ እንዲሁም በጉትጐታ ከወጣው የድጋፍ ሰልፍ ጀርባ ያሉ እውነታዎችን /በተለይም አብዮቱን በውሸት አብዮት የመቀልበስ ስልት የሰልፎቹን ጊዜ ያጢኗል/ ማሰብ፡፡ እንዲሁም ነገሩን ሁሉ በዝምታ ከምናየው ቢያንስ ከሀገሪቱ ሕዝብ በግምት ዘጠና ፐርሰንት የምንሆነውን ሕዝቦች ሃሣብስ ያውቃሉን? ወይም ደግሞ ተቆጥሮ ከማያልቀውና ለዘገባ ካልተመቸው ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች "በበጐፍቃዳቸው" ተሰባሰበ ስለተባለው ገንዘብና ድጋፋቸውን ሰጡ ስለተባለላቸው ልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የልብ እውነትስ ምን ያህል ያውቃሉ?

በርግጥ ዘፋኞቻችን የኢህአዴግን መሠሪነት ለመረዳት የኑሮ ዘዬአቸው ዕድሉን ስላልሰጣቸው እንጂ ገዢው ፓርቲ በተለይም አውራ ባለሥልጣናቱ ዘፋኞቻችን የሚዘፍኑት ነገር ከዕውነታው ይልቅ ለፖለቲካ ትርፍ የተሰላ መሆኑን ልባቸው ያውቀዋል፡፡

በመጨረሻም ውድ አርቲስቶቻችን የየትኛው ፖለቲካ ፓርቲ አባልና አቀንቃኝ የመሆንና ያለመሆን መብታችሁ እንደተጠበቀ ሁሌም እንደምትሉት ሀብታችሁ ሕዝቡ ነውና ሁልጊዜ በየትኛውም ጉዳይ ላይ የሕዝብን የልብ ትርታ በጥልቀት ለመስማትና ከፍላጐቱ ጐን እንድትቆሙለት በትህትና እያሣሰብኩ የቴዲን ሼመንደፈርን በመጋበዝ ላብቃ፡፡ ደግሞ የረሣሁት ነገር የትኛውም ሕዝብ ዘመን ጠብቆ የሚገልጠው ጥቁር መዝገብ /black list/ እንዳለው አንዘንገ፡፡



# ምን ዓይነት ግጥምጥሞሽ ነው

አንድ ሰሞን ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ሞቱ ተብሎ በአንድ ጊዜ በመላው አገሪቱ ተወራ። በማግስቱ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ የሐሰት ወሬ ነው። ህክምናቸውን እየተከታተሉ ነው። የሚል ዜና ሰማን። ፕሬዝዳንቱ ህክምናቸውን አጠናቀው ይመለሳሉ ብለን ብንጠብቅ የውሃ ሽታ ሆነው ቀሩ። ሰሞኑን ደግሞ የኤርትራው ፕሬዝዳንት አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ሞቱ ተባለና ወዲያውኑ የኤርትራ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አልሞቱም በህክምና ላይ ናቸው በመልካም ጤንነት ላይ ናቸው ተብሎ ዜና ሰማን። እንዲያውም ይህንን ወሬ ያስወሩት የአሜሪካን መንግሥትና የኢትዮጵያ መንግስት ሲል የኤርትራ መንግስት ከሰሰ።

ምን ዓይነት ግጥምጥሞሽ ነው? እኔን ግራ የገባኝ ነገር ሁለቱ ፕሬዝዳንቶች የተኙት ሳውድ አረቢያ ሆስፒታል ውስጥ ይሆን?



# ኢትዮጵያውያን . . .

ከገፅ 5 የዞረ

የአመባገነን ሥርዓት በሠላ ሂስ በርካታ ጊዜ ሸንቁጦታል፡፡ ይህ ደግሞ ለእናት ኢትዮጵያ መፃኢ እድል ከመጨነቅና ከመጠበብ የተነሳ ይመስለኛል፡፡

‹‹አካፋን አካፋ›› ማለት ከአድርባይና ከባንዳ ጋዜጠኛ አይጠበቅም፡፡ እስክንድር ግን የእናት ኢትዮጵያ እጣ ፈንታ እንቅልፍ የነሳው በመሆኑ የወያኔ ኢህአዴግ የእውር ድንብር ጉዞን በተባ ብእሩ ኮንኗል፣ሥርዓቱ በትክክለኛው ሀዲድ እንዲጓዝ ሞክሯል፡፡ ዘክሯል፡፡ ምላሹ ግን እስር ሆኗል፡፡ ከሥራ ማገድ ሆኗል፡፡ ሰውየው እስክንድር ነጋ ሆነ እንጂ ገዢዎቻችን በህይወት የመኖር መብቱን ገፈውታል፡፡ በዚች ሀገር ላይ ሥርዓቱን የተቹ ብዙ ሠዎች የእንጀራ ገመዳቸው ተበጥሶ አይሆኑ ሆነው ቀርተዋል፡፡ መ/ር አያሌው አስረስ አንድ ምሳሌ ነው፡፡

ከግንቦት 1997ቱ ምርጫ በኋላ እውነተኞቹ የነፃው ፕሬስ ጋዜጦች (መጽሔቶች) ዝግጅት ቢሮዎች በመላ ሲዘጉ በሥርካለም አሣታሚ ድረጅት ሥር የሚታተሙት ምኒሊክ፣ ሳተናው እና አስኳል ጋዜጦችም ተመሣሣይ ክፉ እድል ገጥሟቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳ ብዙዎች ሀገራቸውን ለባንዳና አድር ባይ ጋዜጠኞች ጥለው ተሠደዋል፡፡ እስክንድርና ጥቂት መንፈሠ ጠንካሮች ደገሞ የሥርዓቱን የፕሬስ አታሼዎች በር አንኳኩ፡፡ የቀድሞው ሀዳር ጋዜጠ ሰዉ ዳዊት ከበደን ጨምሮ የተወሰኑት ተፈቀደላቸው፡፡ እስክንድር እና ባለቤቱ ሥርካለም ፋሲል ተከለከሉ፡፡ በአገዛዙ ሹምባሾች ውሳኔ መንፈሱ ያልተሰበረው እስክንድር ግን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለ ኢትዮጵያ መፃፉን አላቋረጠም፡፡

ገንዘብ ያልከፈላቸው አጃቢዎች መግቢያ መውጪያ ቢያሳጡትም፣ በጠራራ ፀሐይ ነፍጥ ያነገቱ ሠዎች ቢሮአቸው ወስደው ከባድ ማስጠንቀቂያ ቢሠጡትም ለእናት ኢትዮጵያ የገባላትን ቃል አላጠፈም፡፡ ስንቶቻችን እንሆን እንዲህ አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ወድቀን ለሙያችን ክብር እስከመጨረሻው የምንቆም? መልሱን ለአንባቢው ትቼዋለሁ፡፡

## ሥርካለም እና እስክንድር

ሁለቱ ጋዜጠኞች የትዳር ጓደኛሞች ነቸዉ፡፡ስቃይንም አብረዉ ተቀብለዋል፡፡ ሥርካለም ናፍቆትን ከተገላገለችበት እስር ቤት ሆና ዓለም አቀፍ የፕሬስ ተሸላሚ ተብላ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ አለም አቀፍ እውቅና ያለው ጋዜጠኛና የፖለቲካ ተንታኝ እስክንድር ነጋ ሃሳብን በነፃነት ለመግለጽ እውን መሆን ላደረገው ትግል ተሸላሚ መሆኑ ተበሠረ፡፡

አቦ ምን አይነት እድል ነው ባካችሁ? የሥርካለም ሽልማት ከ1997 ዓ.ም በኋላ የተወሰኑ የነፃ ፕሬስ ውጤቶች በአንባብያን እጅ እንደደርሱ ያደረገ ሲሆን የእስክንድር ነጋ ሽልማት ግን ትንሽ ለየት ያለ ይመስለኛል፡፡

ዛሬ የነፃው ፕሬስ መንደር በመስቀለኛ መንገድ ላይ ይገኛል፡፡ በጣት የሚቆጠር ነፃ ጋዜጣ እና ጋዜጠኞች በሚገኙበት በዚህ ጨለማ ዘመን የእስክንድር ሽልማት እንደ ብርሃን የሚታይ ነው፡፡ ሦስት እና አራት የነበሩት ጋዜጦች ደርዘን ሊሞሉ ይችላሉ፡፡ በእውነቱ ለመናገር ደስታው የእስክንድር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ የፕሬስ ጉዞ ለሚያሳስባችሁ ሁሉ እጥፍ ድርብ ነዉ፡፡

# ሜኖው ወደ ላይ ኪሳችን ወደ ታች

«ኤድያ… ይሄ ፆም ባልተፈታ ኖሮ» ይሄንና መሰል አስተያየቶች በየምግብ ቤቱ ተበራክተዋል፡፡ የአስተያየቱ ከጥልቅ መንፈሳዊነት ወይም ሐይማኖተኝነት የመነጨ ከመሰሎት ተሳስተዋል፡፡ አስተያየቱ የተሰበዘው በአዲስ አበባ የትንሳኤን በአል ተከትሎ በየምግብ ቤቶቹ የታየው የዋጋ ጭማሪ ካበሳጫቸው ተጠቃሚዎች መሀከል ነው፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ የተረጋጋ እየመሰለ ሽቅብ እየወጣ ያለው የዋጋ ንረት የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ራስ ምታት በመሆን ላይ ይገኛል፡፡ የዋጋ ንረቱ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ቢነካም በአንፃራዊነት ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን በእጅጉ ደቁሷል፡፡ ሀቅ ላይ የተመሰረተ ስታስቲካዊ መረጃ የሚያሰራጩ አካላት በሀገሪቱ በሌለበት ሁኔታ የጉዳቱን መጠን ተንትኖ ለማስቀመጥ ቢያዳግትም፣ ለመንግስት የሚዋጥ መረጃ የሚያወጣ የሚመስለውው ማዕከላዊው የስታትስቲክ ኤጀንሲ ባሰራጨው የመጋቢት 2004 ወር መረጃ እንኳን የምግብ ዋጋ ግሽበቱ 45.4 በመቶ ደርሷል፡፡ በተለይ የመንግስት ሰራተኞችና በአነስተኛ የግል ስራ ላይ የተሰማሩ ዜጎች ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሾች ናቸው፡፡

መንግስት በአመቱ መጨረሻ የግሽበቱን መጠን ባለአንድ አሀዝ እንደሚሆን በእቅድ ቢያስቀምጥም ነባራዊ ሁኔታው ይህ እንደማይሆን በማሳየት ላይ ይገኛል፡፡ በቅርብ ቀናት ውስጥ በየምግብ ቤቱ የታየው የዋጋ ጭማሪም ይህን የሚያሳይ ነው፡፡ የስታትስቲክስ ኤጀንሲ የመጋቢት 2004 ወር መረጃ እንደጠቆመው ከቤት ውጪ የተወሰዱ ምግቦች 36.7 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

የምግብ ዋጋ ንረት በዋነኝነት እንዲሁም ሌሎች ምግብ ነክ ያልሆኑ የዋጋ ንረቶች ከቤት ውጪ በሚወሰዱ ምግቦች ላይ የዋጋ ጭማሪ እንዲከሰት አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ አሁን እየታየያለውም የምግብ ቤቶች የዋጋ ጭማሪ ይህን መሰረት ያደረገ ይመስላል፡፡ በያዝነው አመት መስከረም ወር ላይ 28.4 በመቶ የነበረው የምግብ ዋጋ ግሽበት 45.4 በመቶ መድረሱ ለዚህ እንደማሳያ ሊያገለግል ይችላል፡፡

የምግብ ቤቶቹን የዋጋ ጭማሪ አስመልክቼ የጠየቅኳቸው ተጠቃሚዎች ግን ነጋዴዎቹ አጋጣሚውን ተጠቅመው የተጋነነ ጭማሪ እንዳደረጉ ያምናሉ፡፡ የመጀመሪያው አስተያየት ሰጪ በግል ስራ የሚተዳደር ነው አዘውትሮ በሚጠቀምበት ምግብ ቤት ከጭማሪው አንድ ቀን በፊት እንደተመገበ የስታውሳል፡፡ «እሁድ በ35 ብር የተመገብኩትን ምግብ ሰኞ 45 ብር ከፍዬበታለሁ» በማለት በዋጋ ጭማሪው ግርምቱን ይገልፃል፡፡ ጨምሮም «በተለይ በምግብ ላይ የሚታየው ጭማሪ ከወቅቱ የፖለቲካ ጉዳዮች በበለጠ ደረጃ አሳሳቢ ነው» በማለት ይሞግታል፡፡ ሁለተኛውን አስተያየት ሰጪ መስቀል ፍላወር አካባቢ በአንድ ሬስቶራንት ውስጥ እየተመገ ነበር ያገኘሁት፡፡ በአቅራቢያው በሚገኝ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ባልደረባ እንደሆነ ነግሮኝ ውይይታችንን ጀመርን፡፡ እሱ በሚያውቃቸው የተለያዩ ምግብ ቤቶች ከበአሉ በኋላ ጭማሪ መደረጉን አስረድቶኝ «እዚ ቤት ለምሳሌ ከበአሉ በፊት ከነበረው ዋጋ እስከ የስምንት ብር ጭማሪ ተደርጓል» በማለት የጭማሪውን ድንገቴነት ያብራራል፡፡ እንደ አስተያየት ሰጪው ከሆነ በአካባቢው ያሉት ምግብ ቤቶች የመጠጥና የምግብ ንግድን አዳብለው የሚሰሩና ጥሩ ገቢም ያላቸው በመሆናቸው ይሄንን ያክል ጭማሪ ማድረጋቸው የተጠቃሚውን አቅም ያላገናዘበ ነው፡፡

በተዘዋወርኩባቸው የአዲስ አበባ አካባቢዎች እንደታዘብኩት ምግብ ቤቶች ተነጋግረው ዋጋ የጨመሩ ይመስል አብዛኞቹ የዋጋ ዝርዝራቸው ላይ መስተካከያ አድርገዋል፡፡ የተወሰኑት አዳዲስ ሜኖ ያዘጋጁ ሲሆን በቁጥር ከፍ የሚሉት ግን የምግቡን ዝርዝርና ዋጋ አስተናጋጆቹ የሚናገሩ ሲሆን ሁለት ሶስት ቤቶች ውስጥ በእስክርቢቶ የዋጋ መጠኑ መስተካከሉን ታዝቤያለሁ፡፡ ፍቃደኛ ሆነው አስተያየታቸውን ከሰጡኝ የምግብ ቤት ባለቤቶችና ሃላፊዎች ዋጋ ለመጨመር ያስገደዳቸውን ምክንያት ትክክለኝነት ለማስረገጥ ሞክረዋል፡፡ ከሞላጎደል አብዛኞቹ ያቀረቧቸው ምክንያቶች በምግብ ዋጋ ንረት ላይ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በተለይም በስጋ ላይ የታየውን ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ይጠቅሳሉ፡፡ «እኛ አካባቢ የቤት ኪራይ ውድ ስለሆነ የዋጋ ጭማሪው ትክክለኛ ይመስለኛል» የምትለው ሀያ ሁለት አካባቢ የቤተሰቦቿን አነስተኛ ምግብ ቤት የምታስተዳድር ወጣት ነች፡፡ ምግብ ቤታቸው አነስተኛ ጭማሪ እንዳደረገ ታምናለች፡፡ በአካባቢው ብዛት ያላቸው ባርና ሬስቶራንቶች የሚገኙ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የገበያ ፉክክር እንዳለና የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ወጪ መጠየቁ ለዋጋ ጭማሪው ተጨማሪ ምክንያት ታደርጋለች፡፡

በዛው ምግብ ቤት በጋራ ሲመገቡ ያገኘኋቸው ሁለት ጓደኛሞች ጭማሪው ምግባቸውን ከቤታቸው በሳህን ቋጥረው እንዲመጡ የሚያስገድድ መሆኑን ጠቁመው፣ ነጋዴዎቹ አምና መንግስት ያስከፈላቸውን ከፍተኛ ግብር ለማካካስ በዚህ አመት በተደጋጋሚ ጭማሪ ማድረጋቸውን እንደታዘቡ ነግረውኛል፡፡ የምግብ ቤቱ ተቆጣጣሪ በዚህ ባትስማማም፡፡

መስቀል ፍላወር አካባቢ ያነጋገርኩት አንድ የምግብ ቤት ባለቤት በምግብ ዝርዝሮቻቸው ላይ በሙሉ የአምስት ብር ጭማሪ ማድረጋቸውን ነግሮኛል፡፡ የዋጋ ጭማሪ ያደረጉበትን ምክንያት ሲዘረዝርም «ሁሉ ነገር ጨምሮብናል በተለይ ስጋ ላይ ያለውን ጭማሪ ሁሉም ያውቀዋል፡፡ ሰራተኛ እንደ ድሮው በቀላል ክፍያ አታገኝም ካንተ የተሻለ የሚከፍለው ካገኘ ቻዎ እንኳን ሳይልህ ይሄዳል» በማለት ያስረዳል፡፡ እዛው ሬስቶራንት ውስጥ ስታስተናግድ ያገኘኋት ወጣት እንዳጫወተቺኝ ግን መጠነኛ ጉርሻ ከተጠቃሚዎች ብታገኝም የሚከፈላት ደመወዝ በወር 350 ብር ብቻ ነው፡፡

በአንዳንድ ምግብ ቤቶች የዋጋ ዝርዝር ላይ በየፆም ምግቦቻቸው ላይ ሳይቀር የተጋነነ ጭማሪ መታየቱን በመረዳት፣ የስጋ ዋጋ ከፍተኛ ጭማሪ ማሳየቱ በምግብ ዋጋ ላይ ለተደረገው ጭማሪ ዋነኛው ምክንያት ሊሆን እንደማይችል ለመገንዘብ አይከብድም፡፡

በአጠቃላይ ግን በአብዛኞቹ ምግብ ቤቶች እየታየ ያለው የዋጋ ጭማሪ አነሳሽ ምክንያቶች ነባራዊ ቢሆኑም አጋጣሚን ተጠቅሞ ዘመቻ በሚመስል መልኩ የዋጋ ጭማሪ የተደረገ ይመስላል፡፡ አንዳንዶቹ ምግብ ቤቶች ፅዱ መመገቢያ ቤትና ንፁህ ሽንት ቤት ሳይኖራቸው(ጭራሹኑ የሌላቸውም አይጠፉም) ግብታዊ የሆነ የዋጋ ጭማሪ ማድረጋቸው ተገቢም አይደለም፡፡ የሚበላውን ያጣ ሕዝብ መሪዎችን ይበላል እንደሚባለው መንግስትም ለራሱ ሲል ለቦንድ፣ ለግድብ፣ ለልማት እያለ በመዋጮ ያዳከመው ሕዝብ የተጋፈጠውን አስከፊ የኑሮ ውድነት ሊያስወግድ የሚችልበትን መንገድ ሊቀይስ ይገባዋል፡፡ በተለይም በሀገሪቱ ትልቁ ቀጣሪ አካል መንግስት እንደመሆኑ አሁን ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የደመወዝ ጭማሪ ሊያደርግ ይገባል፡፡

**<u>መስቀል ፍላወር አካባቢ ያነጋገርኩት አንድ የምግብ ቤት ባለቤት በምግብ ዝርዝሮቻቸው ላይ በሙሉ የአምስት ብር ጭማሪ ማድረጋቸውን ነግሮኛል፡ ፡ የዋጋ ጭማሪ ያደረጉበትን ምክንያት ሲዘረዝርም <<ሁሉ ነገር ጨምሮብናል በተለይ ስጋ ላይ ያለውን ጭማሪ ሁሉም ያውቀዋል፡፡ ሰራተኛ እንደ ድሮው በቀላል ክፍያ አታገኝም ካንተ የተሻለ የሚከፍለው ካገኘ ቻዎ እንኳን ሳይልህ ይሄዳል>> በማለት ያስረዳል፡፡ እዛው ሬስቶራንት ውስጥ ስታስተናግድ ያገኘኋት ወጣት እንዳጫወተቺኝ ግን መጠነኛ ጉርሻ ከተጠቃሚዎች ብታገኝም የሚከፈላት ደመወዝ በወር 350 ብር ብቻ ነው፡፡</u>**

# መሪን መገንባት ራስን ከመገንባት ጋር ሳይጣመር (እንደ መለስና ኢህአዴግ)

ሰለሞን ስዩም

ስለ መሪነት ማውራት ያለበት ማን እንደሆነ ሳላውቅ ብዙ ዘመን ኖርኩ፡፡ ሁልጊዜም የሚያስጨንቀኝ ይኸዉ ጉዳይ ነበር፡፡ አንዳንድ ወዳጆቼ "የኮማንዲንግ ፀባይ ያለው ሁሉ መሪ መሆን ይችላል" ይሉኛል፡፡ ይህ እንግዲህ ማኪያቬሊ ከሚጠብቅብን ፀባዮች አንደኛው ባህሪ ነው፡፡ የማኪያቬሊ የመሪነት ንድፈ ሀሳብ ኢ-ስብዕና የሚያይልበት በመሆኑ አንዲት ደቂቃ እንኳ የሚፈልገው ሆኖ አያውቅም፡፡ የሰውየው ፍልስፍና "ማንኛውም ነገር ለአላማህ ከጠቀመ ተጠቀምበት" የሚል ነዉ፡፡ ይህ ማለት "ማንኛውም ነገር አላማህን ካደናቀፈብህ እንደ ጋሬጣ ከመንገድህ ላይ አንሳ" እንደ ማለት ነዉ፡፡ ለምሳሌ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ስልጣኑን ለማደላደል "ወዳጆቹን" ተራ በተራ ወደ ሞት ሸኝቷቸዋል፡፡ ይህን የሚመረጥ የመሪነት መንገድ አድርጌ አልወስደውም፡፡ ይህን አድርጎ ዚምባቡዌ መኖሩ በራሱ ዕድለኛ ያሰኘዋል፡፡ ለነገሩ እንዴትስ ሆኖ ዕድል ይባላል? የፍትህ ሰዎች እንዲህ አይነቱን ሰው «ፍርድ ቤት ወስዶ ፍርድ ያለማሰጠት በራሱ የባሰ ይጎዳዋል» ይላሉ፡፡ ይህ ሰው ፍርድ ቤት ሄዶ በገለልተኛ አካሄድ ፍርድ ቢሰጠው ዘለዓለም ከሚኮሰኩሰው ሀጢያተኝነት /ጥፋጠኝነት በዳነ ነበር፡፡ ምክንያቱም የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ከፈፀማቸው ጥፋቶች የሚያነፃው ንስሐ አድርጎ ይቆጥረዋልና፡፡ በመሆኑም መንግሥቱ ኃ/ማርም ዕድለኛ አይደለም፡፡

ለማንኛውም ወደኋላ ልመለስ፡፡ መሪ ማን ነው? እንዴትስ ይገኛል? የሚለው ሁሌ ይጨንቀኛል፡፡ የዛሬው ፅሁፌ ግን እስከ 20/8/ 2004 ዓ.ም ድረስ ለዚህ ዕትም የምፅፈው አልነበረም፡፡ ነገር ግን የፕሮፌሰሩን (መስፍን ወልደማርያም ናቸዋ!) 82ኛ የልደት አመት ለማክበር በተገኘሁበት አጋጣሚ የመከራከሪያ ርዕስ ከነበሩ ጉዳዮች ዋነኛው ስለነበር ትንሽ ለማለት ነው፡፡ በነበረው ክርክር መሰል ውይይት ጠንካራ ተቋም ከመገንባት በፊት መሪን መገንባት ይቀድማል ወደ ማለት የሚጠጋ ሀሳብ ያራመደዉ ቡድን የበላይነት የያዘ ይመስል ነበር፡፡ እኔ መሪን ሁን ብለው በፍላጎትና በሳይንስ የሚገነቡ ሰዎች ትክክል ናቸው እላለሁ፡፡ ይህ መንገድ እነመንግስቱ ኃይለማርም ወደ «መሪነት» የመጡበትን ጥንታዊ መንገድ ያስቀራል፡፡ የአቶ መለስ ዜናዊ አወጣጥ በመፈንገል ላይ በመመስረቱ ከመንግስቱ አወጣጥ የሚለየዉ ሳይገድል ከፉክክር በማስወገዱ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በለቱ የበላይነት ከነበረዉ ቡድን የሚለየኝ አንድ ነገር መሪን በመገንባት ስራ የተጠመዱ ቡድኖችም በተመሳሳይ ሰዓት መገንባት አለባቸዉ የሚለዉን ሀሳብ ያለመያዛቸዉ ነዉ፡፡ አሁንም ቢሆን የተያዘዉ አላማ የሚያድርበት ጎበዝ መሪ ግድ ነዉ፡፡ ነገር ግን እንደግለሰብ በሚኖረው ውስንነት አሊያም ቢሞት አላማው አብሮት/አብሯት ሊሞት የማይችለዉ የመሪው/ዋ ገምቢዎችም በእኩል ትኩረት እየተገነቡ ሲመጡ ነው፡፡ አፄ ዮሓንስ በመተማ ጦርነት አሸነፉ በተባለበት ሰዓት ቢወድቁ አሸነፉ የተባሉት ወታደሮች ለመሸሽ ተገደዋል፡፡ ይህን ማቀንቀን የመሪ አገር ኃሊዮት (Leader State Theory) ካለማስታወስ የመጣ ሊሆን ይችላል፡፡ መለስ ኢህአዴግን ጥሎ የገነነበት አካሄድ የሚያስፈልገን አይመስለኝም፡፡

ሌላዉ ትኩረት የሚሻው ጉዳይ መሪን የሚፈጥሩ ሰዎች በተመሳሳይ ሰዓት የሚበቁበት ሁኔታ ካልተቀየሰ ጠንካራ ተቋም ማን ሊመሰርት ነው? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ጠንካራ መሪ በስሩ በገነባው ሌሎች መሪዎች አሊያም ለያዘው አላማ ተፈጻሚነት የሚረዱ ጠንካራ ተከታዮች በማፍራት መገመት ቢችል መልካም ይመስለኛል፡፡ አንድ ሰው ሀገር ከሚገነባ ሀገር የሚገነቡ ብዙ ሰዎችን ቢያስከትል/ቢያፈራ ከድካም ይድናል፣ ለስኬት ይቀርባል፡፡ እንዲህ ማለቴ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች የሉም ለማለት ያለመሆኑ ግልፅ ነዉ፡፡ ኢትዮጵያዊ መሆናችን ጥሩም መጥፎም ነገር የሰጠን እንደሆነ እገምታለሁ፤ ባብዛኛው የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተፃፉ ታሪኮችን እንደማንበባችን «የመሪ አገር» ስነልቡና ያሸንፈናል ብዬ እገምታለሁ፤ በሌላ መልኩ የገዳን ታሪክ ማየት ብንችል መሪ መገንባትና ራስን መገንባት እንደማይነጣጠሉ መረዳት በቻልን ነበር፡፡ በገዳ አሰራር ጥሩ ተመሪነት ጥሩ መሪነት ነው፡፡ ይህ በያንዳንዱ የ8 ዓመታት የገዳ ሳይክል ከሚሰጠን ሀላፊነት ጋር የሚሄድም ነው፡፡

መሪነት በሌላ መንገድ መተንተን እንደሚችልም ማየት ይቻላል፡፡ ለማንኛውም የዚህ ዘርፍ መሪነት ምን እንደሆነ መጀመሪያ አንቶኒ ሮቢንስ ቀጥሎ ብዙ ሰዎች ነግረውኛል፡፡ ተማሪ ወደ ት/ቤት የሚሄደው ለመማር መሆኑን አውቆ ካመነ መሪ ነው፡፡ መምህር ት/ቤት የሚሄደው ለማስተማር መሆኑን አውቆ ካመነ መሪ ነው፡፡ በመሆኑም እኔም ሌላም ብያንስ የራሳችን መሪዎች ነን፡፡ ትልቁ መሪነቴ በራሴ ላይ መሆኑ ደግሞ እንደምን ያለ ዕድል ነው? አንዳንዴ ት/ቤት ለመማር የሚሄዱ አሉ-መሪዎች ናቸው ማለት ነው፡፡ ለማስተማር የሚሄዱም አሉ- እነዚህ መሪም ተማሪም አይደሉም፡፡ የት/ቤቱ መሪነት የሚታየው ግን ለሚማሩት ብቻ ሳይሆን ለማይማሩትም/ለሚያስተማምሩትም መቆሙን ሲያረጋግጥ ነው፡፡ የመንግሥት መሪነትንም ከዚሁ አንፃር ስንተነትን ቆይተናል፡፡ በምርጫ የሚመሰረት ከሆነ ለመረጡት መንግሥት እንደሆነ ሁሉ ላልመረጡትም ተመሣሣይ መንግስት መሆን አለበት፡፡

እኔ ለራሴ መሪ ከሆንኩ የመሪነቴ መጠን መለካት ይቻል ይሆን? ተማሪዎች ይፈተናሉ፡፡ ታዲያ የፈተና ውጤቱ ተማሪው በምን ደረጃ እንዳለ ሊያሳይ ይችላል? አንዳንዴ ፈተና ላይ ተቀምጠው የሚኮርጁ /አስተማሪን መልስ የሚጠይቁ አሉ፡፡ ፈተና በፍፁም ሰውን በትክክል አይገመግምም፡፡ ታዲያ ከኮረጁ/መልሱን አስተማሪ ከነገራቸው ደግሞ የባሰ አይገመግምም፡፡

መሪ ሁል ጊዜ ጥሩ ነውን? የሚል ጥያቄም ይመጣብኛል፡፡ አንዳንድ ጥሩ መሪዎች በሆነ አጋጣሚ ጥሩ ያልሆነ ነገር ሲሰሩ ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ ጀርመን በምርጥ እቃዎች ትታወቃለች፡፡ በዚህ ረገድ መሪ መሆኗ ነው፡፡ ታዲያ `semiens` የተባለውን ጥራት የሚጎድለው ዕቃ በማምረቷ "semiens unfortunately made

ወደ 15 የዞረ

# የውሸት ዕድገት መሐንዲሶቹ

በለጠ ጐሹ ወ/ሚካኤል

እጅግ የተከበሩ ሌሬት አፈወርቅ ተክሌን ዜና እረፍት ለማንበብ በዓመት ሦስት ጊዜ እንኳን የማልገዛውን አዲስ ዘመን ጋዜጣ (ሚያዝያ 4፤2004) ገዝቼ የምፈልገውን ሳነብ፤የአቶ ሱፊያን አህመድን ፎቶ አየሁ፡፡ እኝህ ሰው ዛሬ ደግሞ ምን እያሉ ይሆን ብዬ የተናገሩትን ሳነብ፤በጣም ተናደድኩ፡፡ በ2003 የበጀት ዓመት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) በ 11.4 በመቶ አደገ፤ድህነት ከ38.7 በመቶ ወደ 29.6 በመቶ ቀነሰ፤የሀገር ውስጥ ቁጠባ ከ5 በመቶ ወደ 8 በመቶ አደገ፤የሰብል ምርት ከ20.2.5 ሚሊዮን ኩንታል ወደ 221.8 ሚሊዮን ኩንታል ጨመረ፤ወዘተ.እያሉ በእሳቸው ምናብ ውስጥ ብቻ ያሉ የዕድገት አሓዞችን ደረደሩልኝ፡፡

ከሁሉም የበለጠ ያናደዱኝ ዓረፍተ ነገሮች ግን የሚከተሉት ናቸው፤

“በከተማም በገጠርም የድህነት መጠን ቀንሷል፡፡ በከተማ ግን በከፍተኛ መጠን ሊቀንስ ችሏል፡፡ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታንና መልካም አስተዳደርን የማስፈኑን ጥረት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚያስችሉ ተግባሮች ተከናውነዋል፡፡”

በረጅሙ ተነፈስኩና የዚህን ቅጥፈት ወርድና ስፋት ለማውጠንጠን ሞከርኩ፡፡ የኢህአዴግ ባለሥልጣኖች ለምን ይሆን እንደዚህ ዓይነት ዓይን ያወጣ ቅጥፈት በየአደባባይ የሚናገሩት? በአዲስ አበባ ከተማ ሳይራቡና መሠረታዊ ፍላጐቶችን አሟልቶ ለመኖር ለአንድ ሰው ብቻ በወር ቢያንስ ሦስት ሺ ብር ገቢ ያስፈልጋል ብለው የገመቱ ኢኮኖሚስት አጋጥመውኛል፡፡ ከአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ስንቶቹ ናቸው? ይህንን አነስተኛ መነሻ ገቢ የሚያገኙት? በእኔ ግምት በአዲስ አበባ የድህነት መጠን በከፍተኛ ደረጃ ስለጨመረ፤ከጠቅላላው ነዋሪ ሕዝብ ቢያንስ ሰማኒያ አምስት በመቶው ከድህነት ወለል በታች ወርዷል፡፡ እንዲየውም፤ዳያስፖራው የሚልከው ሐዋላ ባይኖር ኖሮ፤የድህነት መጠኑ (እነ አቶ ሱፊያን አህመድን ሳይጨምር) ወደ መቶ በመቶ እንደሚጠጋ እርግጠኛ ነኝ!

አይ! አቶ ሱፊያን! የዴሞክራሲ ግንባታው ወደ ላቀ ደረጃ ደረሰ አሉ?! እንዴ! እርሶ የት ሀገር ነው ያሉት? እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ አይደለም እንዴ የሚኖሩት? መድረክ በእርሶ ፓርቲ ወይም ኢህአዴግ ላይ ከፍተኛ የሃሣብ የበላይነት በመቀዳጀቱ ከመናጆዎቻችሁ ጋር ከምታደርጉት “የፓርቲዎች ክርክር” አገለላችሁት አይደለም እንዴ?! ሌላው ቀርቶ፤መድረክ ከደጋፊዉ ሕዝብ ጋር እንዳይወያይ የኪራይ ሂሣብ የከፈለበትን አዳራሽ አላስከለከላችሁትምን? የእርሶ ፓርቲ የፃፈውን ሕገ መንግሥት እንኳን አያከብርም፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን በገዛ ሀገራችን በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ሕዝባዊ ስብሰባ፤ሠላማዊ ሠልፍ እና የሥራ ማቆም አድማ እንዳናደርግ ተከልክለናል! በነገራችን ላይ፤እርሶ ስለ ፖለቲካው በምን ስሌት ነው “ወደ ላቀ ደረጃ ስለደረሰው ዴሞክራሲ” ሊሰብኩን የሚፈልጉት? ይልቅስ፤በእርሶ ኃላፊነት ሥር ስላለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ብናወራ ይሻላል፡፡ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በ11.4 በመቶ አደገ አሉ? ካለዚች አሓዝ (11.4 በመቶ) ሌላ የሚያውቁት ቁጥር የለም ማለት ነው? እስኪ አንዳንድ ቀላል የኢኮኖሚክስ ጥያቄዎች ልጠይቅዎት? በስንት የኢንቨስትመንት ምጣኔ (investment rate) ነው ይህን ያህል ዕድገት ያስገኙት? አይኮር (ICOR) ስንት ነው? በኢትዮጵያ አይኮር ከአምስት ሊያንስ አይችልም የሚል ግምት አለ፡፡ እናም፣ የኢንቨስትመንት ምጣኔው ሃምሣ ሰባት በመቶ (57 በመቶ) ነው ማለት ነው? ይህ ፍፁም ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ አሥራ አንድ ነጥብ አራት በመቶ ያሉት የኢካኖሚ ዕድገት መጠን ውሸት መሆን አለበት! እርሶ በሰጡን ስታትስቲካዊ አሓዝ መሠረት የሀገር ውስጥ የቁጠባ ምጣኔ (saving rate) ስምንት በመቶ ከሆነ፤የኢንቪስትመንቱ አርባ ዘጠኝ በመቶ በውጭ ርዳታ፤ብድር እና ኢንቨስትመንት ዕድገት አንድ በመቶ ብቻ ነው ከተባለ፤አብዛኛው ኢንቨስትመንት የተሸፈነው በውጭ ርዳታና ብድር ነው ማለት ነው፡፡ ጠቅላላ የውጭ ብድር ዓመታዊ ግኝት እና ክምችት ስንት ደረሰ? የውጭ ብድር የዋናው እና የወለድ ክፍያስ ስንት ነው? የውጭ ብድር ክፍያዎች ከጠቅላላ የኤክስፖርት ገቢ ስንት መቶኛ ሆነ? ሌላው ጥያቄ፤11.4 በመቶ ዕድገት ለማስገኘት ለስንት ኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል ተከፈተ? ምን ያህል ተጨማሪ መሬት ታረሰ? ምን ያህልስ ተጨማሪ ካፒታል ተሠማራ? የአጠቃላይ ምርታማነት ምጣኔስ (total factor productivity) ስንት ሆነ?

ትንራንስፎርሜሽን ዕቅድ የምትሉት በ2003 በጥሩ ሁኔታ ተግባራዊ ሆኗል ሲሉ፤የአምስት ዓመት ዕቅድ እንደመሆኑ፤የዕቅዱ አንድ አምስተኛ ተግባራዊ ሆኗል ማለት ነውን? ለዕቅዱ የተበጀተው ገንዘብ አንድ ትሪሊዮን ብር ስለሆነ፤አንድ አምስተኛው ሁለት መቶ ቢሊዮን ብር ይሆናል፡፡ የ2003 ጠቅላላ የመንግሥት በጀት 118 ቢሊዮን ብር ነው፡፡ እዚህ ላይ የአባይ ግድብ በጀትን (80 ቢሊዮን ብር) ስንጨምርበት 198 ቢሊዮን ብር መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ለነባር መደበኛ ወጪዎች የተበጀተ እንደመሆኑ፤የልማት ወጪው ከዚህ በጣም ያነሰ እንደሚሆን የታወቀ ነው፡፡ እናም “ትራንስፎርሜሽን” ለምትሉት ወጪ የተደረገው እጅግ አነስተኛ ነው የሚሆነው፡፡ ታዲያ፤እንዴት “ትራንስፎርሜሽኑ” በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ሆኗል ይላሉ? በነገራችን ላይ፤የአባይ ግድብ ፕሮጀክትን አንደኛ ዓመት ተገቢ ባልሆነ ብዙ ጋጋታ ስታከብሩ፤አፈፃፀሙ ስድስት በመቶ ብቻ ነው ብላችኋል፡፡ በዚህ የአፈፃፀም ፍጥነት የአባይ ግድብ ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ ወደ አሥራ ስድስት ዓመታት ሊፈጅ ነው? ሌላው ቢቀር፤ጥሩ የሥልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ ሊሆንላችሁ ይችላል!

አቶ ሱፊያን፤ውስጠ አዋቂዎች እንደነገሩኝ፤እነዚህን የውሸት ኢኮኖሚያዊ አሓዞች እንዴት እንደምታቀነባብሯቸው ትንሽ ላጫውትዎት፡፡ እርሶ የገንዘብና የኢካኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ቢሆኑም፤ይበልጡኑ ሚናዎ በከፍተኛ የፖለቲካ ካድሬነት ነው ይባላል፡፡ የሐሰት ኢኮኖሚያዊ አሓዞቹን ከበስተጀርባ ሆነው የሚያቀነባብሩት አሁን የኢንዱስትሪ ሚኒስትር የሆኑት አቶ መኮንን ማንያዘዋል እንደሆኑ ተነግሮኛል፡፡ አቶ መኮንን ጉበዝ ቴክኖክራት ናቸው፡፡ በኢኮኖሚክስ (economic development) እና በስታስቲክስ የዩኒቨርሲቲ ድግሪ (ሁለተኛ ዲግሪ) እንዳላቸው ይነገራል፡፡ ማስተርስ ዲግሪአቸውን የሐሰት ኢኮኖሚያዊ አሓዞቹን ከበስተጀርባ ሆነው የሚያቀነባብሩት ጉበዝ ቴክኖክራት ናቸው፡፡ ማስተርስ ዲግሪአቸውን የማታ ትምህርት ደግሞ በስታቲስቲክስ “ሰቅለው” እንዳለፉ መረጃ ደርሶኛል፡፡ በደርግ ዘመን በነበረው ማዕከላዊ ፕላን በማክሮ ዲፓርትመንት በከፍተኛ ኤክስፐርትነት እንዳገለገሉና በሙያ ብቃታቸውም ምስጉን እንደነበሩ የቅርብ ጓደኞቻቸው ይመሰክራሉ፡፡ የኢህአዴግ አባል ሳይሆኑ የኢህአዴግ ባለሥልጣን ለመሆን የበቁ ብቸኛው ሰው እንደሆኑም ተገልጿአል፣

## ዴሞክራሲን ማምጣት ያቃተው . . .

ከገፅ 3 የዞረ

ውስጥ የስራ- ክፍፍል እንዳይዳብር ከማገዱም ባሻገር ገበሬው ኮሙኒቲ እንዳይመሰረት ያደርገዋል። ይህም ማለት በገጠር ውስጥ በልዩ ልዩ መልኮች የሚገለጽ የባህል እንቅስቃሴ እንዳይኖር ያግዳል። አሁን ደግሞ የስኳር ምርት ለማስፋፋት የሚያካሄደው እርምጃና ወደ ሰድስት የሚጠጉ የስኳር ፋብሪካዎች ተከላ ዕቅድ የአገራችንን ኢኮኖሚ እንዲዛባ ያደርገዋል። ልክ እንደ ብራዚል ገበሬውን ወደ ተራ ባርነት እንዲቀየር የሚያደርግ ነው። ይህም ማለት ይህ ዐይነቱ ፖሊሲ የዴቬሎፐሜንታል ስቴትን መሰረተ-ሃሳብ ይፃረራል። በተጨማሪም የአበባን ተከላ ማስፋፋትና ቡናን የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ዋና ዕምብርት ማድረግና ሊሎች አጠቃላይ የሀብት ፈጠራን የማያመጡ ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔዎች በመሰረቱ ከዴቬሎፐሜንታል ስቴት ፖሊሲ ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም። ተቃራኒ ናቸው ማለት ነው።

ወደ ከተማዎች ስንመጣ፣ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለልማት እየተባለ የሚካሄደው የመሬት ንጥቂያና ተፈናቃዮች ራሳቸውን እንዲገሉ ወይም በየሜዳው ወድቀው እንዲቀሩ ማድረግ ከዴቬሎፐሜንታል ስቴት ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም አይደለም። ዕውነተኛ በመንግስት የሚደገፍ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የህዝብን መብት የሚረግጥና ከቦታቸው የሚያፈናቅል አይደለም፤ መሆንም የለበትም። አካባቢው መልማት ካለበት ደግሞ የግዴታ ለብዙ ዓመታት በቦታው የሚኖር ሰው ሌላ አማራጭ ማግኘት አለበት፤ ወይም ደግሞ የቀድሞው ቦታ ሊመለስ የሚችልበት ሁኔታ ከመጀመሪያውኑ መታቀድና መዘጋጀት አለበት። የኢህአዴግ ፖሊሲ ግን በተለይም ደሀውንና ድጋፍ የሌለውን የህበረተሰብ ክፍል የሚመታና ሶሻል ዳርዊኒዝምን የሚያስፋፋ ነው። በተለይም በሪል ስቴት ስራ የተሰማሩ ከዓለም አቀፍ

የፊናንስ ካፒታል ጋር የተቆላለፉ ኃይሎች የሚሰሩት የታሪክ ወንጀል በቀላል ቋንቋ የሚገለጽ አይደለም። ከዚህም ከዚያም በመምጣትና በመሰባሰብ፣ እንዲሁም ከውጭ የገንዘብ አበዳሪ ኃይሎች ጋር በመመሰጣጠር የሀብት ቁጥጥር እያደረጉ ነው። ህዝባችን በአገሩ ውስጥ ሁለተኛ ዜጋ እየሆነ እንዲታይ ተደርጓል። በኮሞዲቲ ገበያም ያለው ሁኔታ ከዚህ የሚያንስ አይደለም። የተሰተካከለና ሚዛናዊ የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚቀናቀን ኃይል በመፍጠር አገራችንን ዘለዓለሟን የጥሬ-ሀብት አምራች ሆና እንድትቀር የሚያደርግ ነው። በዚህም ምክንያት ቡና አምራቹ ገበሬ ህዝባቸን ኑሮው በምንም ዐይነት አለተሻሻለም። ከጎጆ ቤቱ አልተላቀቀም። ልጆቹን ለማስተማር እንዳይችል ሆኗል። በሚያገኘው በዓለም ገበያ ላይ በሚወሰን ዋጋ የምርቱን ሂደትና ኑሮውን ለማሻሻል የቻለ አይደለም። በአንጻሩ ግን የኮሞዲቲ ገበያውን የሚቆጣጠሩት ግለሰቦችና የመንግስት ባለስልጣናት ልዩ ዐይነት ኑሮ በመኖር ለዋጋ መናርና ለሀብት ነጠቃ ምክንያት ሆነዋል ማለት ይቻላል።

ከዚህ ስንነሳና በተለይም እየጨመረ የመጣውን ድህነትና የቆሻሻ መኖሪያዎችን አካባቢ ስንመለከትና በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣውን የኑሮ ውድነት ስንመረምር የኢህአዴግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አብዛኛውን ህዝብ የባሰውኑ ወደ ድህነት የገፈተረና ወደፊትም የሚገፈትር ነው። ይህ በውስጥና በውጭ ኃይሎች በተቀነባበረና በረቀቀ መልክ የሚካሄደው ኢኮኖሚያዊ መዛባትና፣ እንዲሁም የሀብት ቁጥጥርና ዘረፋ ልዩ ዐይነት የህብረተሰብ ግንኙነት እየፈጠረ ነው ማለት ይቻላል። እንደዚህ ዐይነቱን በዓለም አቀፍ ፋይናንስ ካፒታል የሚደገፈውን የኢኮኖሚ ፖሊሲና የሀብት ዘረፋ ዘመናዊ ፊዩዳሊዝም ተብሎ ሊጠራ ይቻላል። በዘመናዊነትና በዕድገት ስም ገበሬውን ወደ ቀን ሰራተኛነትና ወደ ጥገኝነት የሚለውጠው ነው። ከዚህ ስንነሳ ምን መደረግ አለበት ወደሚለው እናምራ።

### ምን መደረግ አለበት !

የኢህአዴግ አገዛዝ ከመሻሻልና ራሱን ከማረም ይልቅ በተለይም ባላፉት ሰባት ዐመታት እየባሰበት የመጣ አገዛዝ ነው። በአፍሪካ ውስጥም ተወዳዳሪነት የሌለው ጨቋኝ አገዛዝ ብቻ ሳይሆን አገራችንን በሁሉም አቅጣጫ እንድትዳከምና በዘለዓለማዊ ውዝግብ ውስጥ ወድቃ ህዝቧ ነፃነትን እንዳይቀዳጅ የሚያደርግ አስቸጋሪ አገዛዝ ሆኖ ብቅ ብሏል። ራሱ አገዛዙ በህዝባችን ላይ ሽብርተኝነትን እያካሄደ እያለ ለነፃነትና ለመብት የሚታገሉ ኃይሎችን በሽበርተኝነት የሚወነጅል አገዛዝ ነው። የአንድ አገር ህልውና ስልጣን ላይ ባለው የገዢ መደብ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በጠቅላላው ህዝብም የመንፈስ ጥንካሬና በስነስርዓት መኖር ነው። ለዚህ ደግሞ ኢኮኖሚ ቁልፍ ቦታን የሚይዝና፣ የአንድ አገር ውድቀትና ጥንካሬ በኢኮኖሚ ሁኔታ የሚወሰን ነው። አንድ አገዛዝ ሆን ብሎ አንድን አገር የሚያዳክም ከሆነ፣ ከውጭ ኃይሎች ጋር በመመሳጠር ሀብቷ እንዲዘረፍ የሚያደርግ ከሆነ፣ ባጭሩ ህልውናዋን የሚያዳክም ከሆነ በህዝብ ዘንድ ምንም ዐይነት ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። የአንድ አገዛዝ ዕውቅናና ተቀባይነት ሊወሰን የሚችለው በሚሰራው ጥሩም ሆነ መጥፎ ተግባር ነው። እንዲያው በህገ-መንግስት ብቻ እያታለለ ሊኖር ምንም መብት የለውም ማለት ነው።

ከዚህ ስንነሳ የአንድ አገር ዕድገትና ህልውና ሊወሰን የሚችለው ባለው የፖለቲካና የመንግስታዊ አወቃቀር ሁኔታ ነው። ይህም ማለት አንድ አገዛዝ ራሱንና የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ለማደለብ ሲል የመንግስቱን መኪና የባሰ ጨቋኝ የሚያደርግ ከሆነና ከውጭ ኃይሎች ጋር በብዙ ድሮች የተሳሰረ ከሆነ ለአገር ህልውናና ለጠቅላላው ህብረተሰብ ተስማምቶ መኖር አደገኛ ነው። አንድ ህዝብ እየተዘረፈ፣ እየተጨቆነ፣ የኑሮው ሁኔታ እየተበላሸበትና አቅጣጫውም የሚጠፋው ከሆነ ይህ እንደተፈጥሮ ህግ መታየት የለበትም። የሰው ልጅ ከእንስሳ የሚለየውም እንደዚህ ዓይነት ነገር እንዴት ሊመጣ ቻለ ብሎ በመጠየቅ ራሱንና አካባቢውን ለመለወጥ የሚችል ከሆነ ብቻ ነው። ሁኔታውን መለወጥም ሆነ ለማሻሻል የማይችል ምሁርም ሆነ ህዝብ በታሪክ

ውስጥ እየተጠቃ የሚኖርና በመጭውም ትውልድ ተጠያቂ የሚያደርገው ነው። ስለዚህ ለአንድ አገር ዕድገት ቁልፉ የመንግስቱ አወቃቀር ሁኔታና የሚያካሄደው የፖለቲካ ዓይነት ወሳኝ ሚናን ይጫወታሉ። በታሪክም እንደተረጋገጠው የፖለቲካ ሁኔታ ሲሻሻልና ህዝቡም ነጻነትን ሲቀዳጅ ነው ሃሳብ ሊመጣለትና ህብረተሰቡንም ሆነ ኢኮኖሚውን ሊያሳድግ የሚችለው። በሌላ አነጋገር አንድ ህዝብ የበለጠ ነጻ እየሆነ በመጣ ቁጥርና ከላዩ ላይ ያለው ጭነት ሲቃለልለት የመፍጠር ኃይሉም ይዳብራል፤ ህብረተሰብአዊ ሀብት ይፈጥራል። ስለዚህም የፖለቲካ ጥያቄና የመንግስቱ መኪና ጉዳይ ቁልፍ ቦታን ይይዛሉ ማለት ነው። ህዝባዊ ባህርይ እንዲይዙና ታሪካዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ በአዲስ መልክ መደራጀት አለባቸው። ህዝብን ከማስፈራራት ይልቅ የህዝብ ወዳጅና አለኝታ መሆን አለባቸው። ህብረተሰብአዊ ፍቅርን የሚለግሱና አገራችን ተከብራ እንትኖር የሚያድርጉ ሆነው መደራጀት አለባቸው። የሰላዮች መጨፈሪያ መሆን የለባቸውም። ባጭር ቋንቋ የኢህአዴግ ታሪካዊ ተልዕኮው ጥፋት በመሆኑና ሊታረምም የማይችል ስለሆነ ከኮመን ሴንስ አንፃርም ሆነ ከተፈጥሮ ህግ ሁኔታ ስልጣን ላይ መቆየት ያለበት አይደለም። ወደፊትም እንደዚህ ዐይነቱ አገር አጥፊ ኃይል የፖለቲካ ህይወት አይኖረውም፤ሊኖረውም አይገባም።

## ዜና

# የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ተፈረደበት

በአንዱዓለም አራጌ የክስ መዝገብ ላይ ያሉ ተከሳሾችን በተለይም ፍትህ ጋዜጣ የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ የአቶ ናትናኤል መኮንን እና የአቶ ክንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶን)፤ ነጋድራስ ጋዜጣ ደግሞ የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን ቃል ነው የተባለውን በጋዜጣቸው አማካኝነት ለህዝብ በማድረሳቸው የፌደራል አቃቤ ህግ የፍርድ አሰጣጡን ያዛባል በሚል በዋና አዘጋጆቹ ላይ ክስ መመሥረቱ ይታወቃል፡፡ የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ እና የነጋድራስ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ሱራፌል ግርማ በጋዜጦቻቸው ላይ የወጡት የተከሳሾች ቃል እንደሆነና ተከሳሾቹም በችሎት ላይ ያቀረቡት መሆኑን ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል፡፡ በተለይ የአቶ ክንፈሚካኤል ደበበ ቃል በፍትህ ጋዜጣ የወጣው ፅሑፍ የአቶ ክንፈሚካኤል መሆን አለመሆኑን አቶ ክንፈሚካኤል ሚያዝያ 5 ቀን 2004 ዓ.ም ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት ፍ/ቤት ቀርበው እንዲያስረዱ በተወሰነው መሠረት ቀርበው አስረድተዋል፡፡ አቶ ክንፈሚካኤልም በፍትህ ጋዜጣ ላይ የወጣው ሙሉ በሙሉ የእሳቸው እምነትና አስተሳሰብ እንጂ የጋዜጠኛ ተመስገን አይደለም፣ ፅሑፉም የራሴው ነው፣ በጋዜጣው ላይ የተጨመረም ሆነ የተቀነሰ ፅሑፍ የለም ሲሉ ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል፡፡ አያይዘውም ፅሑፉ የተከሳሽነት ቃሌን ለችሎት ያዘጋጀሁት ሲሆን ፍ/ቤቱ በቃል አቅርብ ሲለኝ እኔም እንደሌሎቹ ተከሳሾች በቃሌ አቅርቤያለሁ በማለት ሲያስረዱ ፍ/ቤቱ ፅሁፍ እንዴት ለጋዜጣው እንደደረሰ ጠይቋቸዋል፡፡ አቶ ክንፈሚካኤልም ፅሑፉን እዚሁ ፍ/ቤት ችሎት ውስጥ በቤተሰቦቼ አማካኝነት ለጋዜጣው እንዲደርስ አድርጌያለሁ ብለዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ለጋዜጠኞቹ ውሳኔ ለመስጠት ለትናንት ሰኞ ሚያዝያ 22 ቀን 2004 ዓ.ም ቀነ ቀጠሮ ሰጥቶ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት ፍ/ቤቱ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ የአራት ወር እስር ወይም ሁለት ሺህ ብር ቅጣት ሲፈረድበት በቃሊቲ ማረሚያ ቤት የሚገኘው አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ ላይ 8 ወር እስር ተፈርዶባቸዋል፡፡ ጋዜጠኛ ሱራፌል ግርማ ግን ከተመሰረተበት ክስ በነፃ ተሰናብቷል፡፡ ከውሳኔው በኋላም ጋዜጠኛ ተመስገን ልደታ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሚገኘው ጊዜያዊ ማረፊያ እንደሄደ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለህትመት እስከገባንበት ድረስም ጊዜያዊ ማረፊያ እንደነበር ተጠቁሟል፡፡

## የእስልምና እምነት ተከታዮች ጥያቄ በጥንቃቄ ሊፈታ ይገባል ሲል ኢራፓ ማሳሰቢያ ሰጠ

በቅርብ ጊዜ በእስልምና ተከታዩ ህብረተሰብ እየተነሳ ያለውን ጥያቄ መንግስት በጥንቃቄ ተመልክቶት እንዲፈታ ጥረት መደረግ ይጠበቅበታል ሲል የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ /ኢራፓ/ ማሳሰቢያ ሰጠ፡፡ የፓርቲው አመራሮች ይህንን የገለፁት ባለፈው ሳምንት የፓርቲው ፕሬዝዳንት አቶ ተሻለ ሰብሮ ም/ፕሬዝዳንቱ አቶ ሄኖክ እውነቱና የፓርቲው ዋና ፀሐፊ መምህር ሰለሞን ቦጋለ በመሆን በሰጡት በፓርቲው ጽ/ቤት መግለጫ ነው፡፡

የፓርቲው አመራሮች በጋራ በሰጡት መግለጫ በርካታ ጉዳዮችን አንስተዋል፡፡ ካነሷቸው ነጥቦች ውስጥ የፓርቲውን የሦስት ዓመት የትግል ጉዞ ዳሰዋል፤ የመምህራን፣ የእስልምና እምነት ተከታዮችና የቤንቺ ማጂ ነዋሪዎች መፈናቀል መንግሥት በጥንቃቄ ተመልክቶ እንዲፈታው ማሳሰቢያ ከመስጠታቸው በተጨማሪ ለብሔራዊ መግባባት ፓርቲው ተግቶ እንደሚሰራ አሳስበዋል፡፡ ለብሔራዊ መግባባት ዲያስፖራው፣ ፓርቲዎች መንግስትና ኢህአዴግ የሃይማኖት አባቶች ምሁራን በጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ የድርሻውን ይወጣ ሲሉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

በተያያዘ ዜና የኢራፓ ማዕከላዊ ም/ቤት ሚያዝያ 20 ቀን 2004 ዓ.ም ስብሰባ አድርጐ በበርካታ አጀንዳዎች ላይ መክሮ መጠናቀቁን ፓርቲው በላከልን የአቋም መግለጫ ገልፃዕል፡፡ ባለአራት ገጽ የአቋም መግለጫ እንዳስታወቀው በወቅታዊ ጉዳዮች አቀዋም ከመያዙም በተጨማሪ በወደፊቱ የፓርቲ እንቅስቃሴ ላይ የትግል አቅጣጫ መቀየሱን በአቋም መግለጫው ተገልፃዕል፡፡

## በአዲስ አበባ ሲካሄድ የነበረው ዓለም አቀፍ የማኅበረሰብ ጤና ጉባዔ ተጠናቀቀ

አዲስ አበባ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ሲካሄድ የነበረው ዓለም አቀፍ የጤና ጉባዔ ተጠናቀቀ፡፡ ጉባዔውም በኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማኀበር እና በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አስተባባሪነት ከሚያዝያ 15-19 ቀን 2004 ዓ.ም ከዓለም የጤና ማኀበራት ፌዴሬሽን ጋር በመተባበር "ፍትሀዊ የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት" በሚል መርህ መካሄዱ ይታወቃል፡፡ በጉባኤውም የአፍሪካ ጤና ማኀበራት ፌዴሬሽንም ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ በተካሄደው 13ኛው ዓለም አቀፍ የማኀበረሰብ ጤና ጉባዔ ላይ መሳተፉ ታውቋል፡፡ቦሌ በሚገኘው በሚሊኒየም አዳራሽ በተደረገው በጤና ጉባኤ ላይም 700 ያህል ጥናቶች በጽሑፍ፣ በፎቶና በተለያዩ መንገዶች የቀረቡ ሲሆኑ ከቀረቡት ጥናቶች ውስጥ 100 ያህሉ በኢትዮጵያውያን መቅረቡ ታውቋል፡፡ የጉባኤው በአዲስ አበባ መካሄድ ለኢትዮጵያም ሆነ ለሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች የጤና ባለሙያዎች ሰፊ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ጥሩ እድል እንደ ፈጠረ የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማኀበር ፕሬዘዳንት ዶ/ር ተዋበች ቢሻው ገልፀዋል፡፡ በጉባኤው ላይም ከ115 ሀገሮች 3000 ባለሙያዎች መሳተፋቸው የተገለጸ ሲሆን በመጨረሻም "የአዲስ አበባ ዓለም አቀፍ የጤና ድንጋጌ" በማውጣት ጉባኤው በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁ ተጠቁሟል፡፡

# ምርጫ ቦርድ ፓርቲያችን ለመዘጋት ተግቶ እየሰራ ነው ሲል መኢአድ ከሰሰ

### ፓርቲው ለራሱ ህገ ደንብ እየተገዛ አይደለም ምርጫ ቦርድ

"የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ፓርቲያችንን ለመዘጋት ተግቶ እየሠራ ነው" ሲሉ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ አመራሮች ገለጹ፡፡ ይህ የተገለፀው የፓርቲው ተ/ም/ፕሬዝደንት/ አቶ ወንድምአገኝ ደነቀው፣ የፓርቲው ዋና ፀሐፊ አቶ ተስፋዬ ታሪኩ፣ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዋ ወ/ሪት መሶበወርቅ ቅጣውና የህዝብ ግንኙነት ም/ኃላፊው አቶ ጌታቸው አበበ ባለፈው ሳምንት በጽ/ቤታቸው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ነው፡፡

የፓርቲው አመራሮች በጋራ በሰጡት መግለጫ "ምርጫ ቦርድ" ፓርቲው በህገ ደንቡ መሠረት በዲሲፕሊን ከፓርቲው ያባረራቸውን ግለሰቦች በመሰብሰብ ፓርቲውን ለማበጣበጥ እየሠራ ይገኛል በማለት ተናግረዋል አክለውም "ለዚሁም ዓላማው የፓርቲውን ማህተም ከሚያዚያ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በኋላ እንዳትጠቀሙ የሚል ደብዳቤ ጽፏልናል" ብለዋል፡፡ ምርጫ ቦርድ በበኩሉ "ፓርቲው ለራሱ ህገደንብ እየተገዛና እየተዳደረ ባለመሆኑ የተፈጠረ ችግር ነው፡፡ ፓርቲው ያለበትን የውስጥ ችግር እንዲፈታ ከተፈለገ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ጉባኤው እልባት ሊሰጥበት ይገባል፡፡" ብለዋል፡፡

# የኢትዮጵያ መምህራን . . .

ከገፅ 5 የዞረ

ጥያቄ ካልሰሙ ስሙ ያልተጠራውን የድምጽ ቆጠራ ከየት አመጡት? ዋናውን ጥያቄ (የደሞዝ ጭማሪውን) በደሞዝ እስኬል ማሻሻል አታድበስብሱብን ማለት የእስኬሉን መስተካከል መቃወም ማለት አይደለም፡፡ ለመሆኑ 500 ያክል የተባሉት መምህራን ምን ብለው ነው የደሞዝ እስኬሉን መስተካከል የሚቃወሙት? እንኳን መምህራን ህፃናት እቃ ዕቃ ሲጫወቱ ለምርጫ በማይቀርብ ጉዳይ ላይ ጎራ ለይተው ድምጽ አይሰጡም፡፡

«አሥር የማይሞሉ፤ ከሥራ የታገዱት መምህራን፤ የማስተማር ብቃት የሌላቸው፤ የነውጠኞችና የሽበርተኞች ተላላኪዎች ስለሆኑ መባረራቸው ሳይሆን ርምጃው መዘግየቱ ነው ጥፋቱ፡፡ በወላጆች ከተነገረን ሰንብቷል፡፡» አሉ፡፡ እነዚህ መምህራን በብቃት ማነስ ነው ወይስ በሽብርተኝነት ወይስ በሁለቱም ነው ሥራቸውን ያጡት? ከሰሞኑ ከሙብት ማስከበር ጥያቄው፤ ከሥራ ማቆም አድማው ጋር ምንም ንኪኪ አልነበራቸውም ወይስ ይሄ በህግ ስለሚፈቀድ ታልፎ ነው? በህጉ መሠረት አንድ ሰው በአንድ ጥፋት ሁለት ሦስት ጊዜ መቀጣት ስሌለበት ቢያውቁት ይጠቅማቸዋል ብዬ ነው ማንሳቴ፡፡ ለመሆኑ እነዚህን መምህራን ገምግሞ የማስተማር ብቃት ስሌላቸው እንዲባረሩ የፈረደባቸው ህብረተሰብ የቱ ነው? መቼና የት ተሰብስቦ ነው እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰው?

የሚሉ ጥያቄዎች በማንሳት አቶ መለስን እያፋጠጥኩ ሙግት ልገጥም ለራሴ ቃል ገብቻለሁ፡፡ ክቡር ጠ/ሚኒስትሩ ያመኑበትንና የመሰላቸውን እንደተናገሩት ሁሉ እኔም ተንጠራርቼ እሳቸውን በዛው ስሜት መሞገቱ ቀርቶብኝ በዜግነቴ ስለመምህራንና የትምህርት ጉዳይ የማውቀውን በትህትና መመስከርና መምከር መረጥሁ፡፡ ለትምህርት ሥራ ተቆርቋሪ የሆኑ ዜጎች ሁሉ ሀሳብ ቢሰጡበት መፍትሔ ለማፈላለግ ያበረታታል የሚል እምነት አለኝ፡፡ አቶ መለስ ጊዜ ኖሯቸው እራሳቸው ቢያነቡኝ ደስታውን አልችለውም፡፡ ሌላ ሰው ከሆነ አሳጥሮ የሚነግራቸው ስለማስተማር ሙያ ክብር ብሎ እውነታውን እንዳለ እንዲአቀርብልኝ ከወዲሁ ባአደራ ጭምር እለምናለሁ፡፡

ለ) የመምህራን ሁለት ተፃራሪ ማህበራዊ ቦታዎች (Social Status)

በእኔ ግንዛቤ የአንድ ሙያተኛ የሆነ የመንግሥት ቅጥር ሠራተኛ የወር ደሞዝ የሠራተኛውን የትምህርት ደረጃና የሚሰጠውን አገልግሎት የሚመጥን፤ ራሱንና ቤተሰቡን ያለጭንቀት ማኖር የሚያስችል መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ይህም ማለት ከተመጣጠነ ምግብ የወር ፍጆታና ከልብስ መግዣ ባለፈ ለክፉ ቀን የሚሆነውን ገንዘብ ከወር ወር በጁ ላይ አያጣም ማለት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ የሚኖር ሰው በግሉ ጤናማ፤ በሥራው ደስተኛና በህብረተሰቡም ዘንድ ማህበራዊ ከበሬታ የሚሰጠው ይሆናል፡፡ እስከ 1950ዎቹ አጋማሽ የነበሩት የኢትዮጵያ መምህራን ይሄን የምቾት ሕይወት ኖረውት ነበር፡፡ ወር ቆጥረው የሚቀበሉት ደሞዝ ብዙ ሆኖ አይደለም፡፡ ከመምህራን ማሰልጠኛ የተመረቀ የጀማሪ መምህር ደሞዝ ብር 200 ብቻ ነበር፡፡ የድሎቱ ምንጭ የብሩ የመግዛት አቅም እጅግ ጠንካራ ስለነበረና ኑሮው ደግሞ ሲበዛ ርካሽ ስለነበር ነው፡፡ መምህራን ኑሮ መክበድ የጀመራቸውና ማህበራዊ ክብራቸው እየወረደ የደሞዝ ጭማሬ ጥያቄ ማንሳት የተገደዱት በ1960 መባቻ ነበር፡፡ እነዚህን ሁለት ተፃራሪ የመምህራን ሕይወት በተጨባጭ ለመረዳት ከግርጌ ያለውን ሰንጠረዥ 1 ይመልከቱ፡፡

በሠንጠረዡ ባለው መረጃ መሰረት ከ1958/59 እስከ 1993/94 (እ.ኤ.አ.) ለአንድ የመምህራን ማሰልጠኛ ምሩቅ መምህር መነሻ ደሞዙ ያደገው በ15% (ብር 30) ነበር፡፡ ለመኖር መሠረታዊ የሆኑ የምግብ ምርቶችና የልብስ ሸቀጦች ዋጋ ግን በአማካኝ ወደ 900% ገደማ ጨምሯል፡፡ የመምህራን ኑሮ ያሽቆለቆለው እነዚህ ሁለት ቁልፍ ሁኔታዎች (የደሞዝ ጭማሪውና የዋጋ ንረቱ) ባለመመጣጠናቸው ነው፡፡ ስለሆነም መምህራን ለደሞዝ ጭማሬ መንቀሳቀስ ግድ ሆነባቸው፡፡ በዚህና በተያያዥ የሀገር ጉዳዮች ላይ የጋራ ግንዛቤ ይዞ መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር ማህበራቸው ጠቅላላ ጉባኤዎችና የም/ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባዎች በዴሴ/ወሎ በ1970፤ አርባምንጭ/ጋሞጎፋ በ1972፤ ወለጋ/ ነቀምት በ1973፤ ከፋ/ጂማ ከጳጉሜ 1975 እስከ መስከረም 1976 (ሁሉም ዓመቶች እ.ኤ.አ.) ባካሄዳቸው ስብሰባዎች ላይ የመምህራን ተወካዮች እየመከሩ ባስተላለፉት ውሳኔና በወሰዱት ርምጃ የንጉሡን መንግሥት ወጥረው ያዙት፡፡ ይሄን እንቅስቃሴ ለፖለቲካ ሥልጣን የሚታገሉ ኃሎች ገብተውበት የአፄውን ሥርአት ለመገርሰስ የጎላ ሚና ቢኖረውም በደርግ አሸናፊነት ስለተጠለፈ የመምህራን ችግር ሳይፈታ ለ17 ዓመት የሆነው ሁሉ ሆነ፡፡ (ይቀጥላል)

## አንድነት ፓርቲ በደቡብ ክልል ከህዝብ ጋር ሊመክር ነው

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) በደቡብ ክልል ባሉ ሁለት ዞኖች በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ከህዝብ ጋር ሊመክር ነው፡፡ፓርቲው የሚመክረው በወቅታዊው አዲሱ የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ፣ የኑሮ ውድነት፣ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት አጠባበቅ እና አንድነት ስለሚያደርገው ትግል ዙሪያ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት ውይይት ይደረጋል፡፡አንድነት ከህዝብ ጋር የሚመክረው ቅዳሜ ሚያዝያ 27 ቀን 2004 ዓ.ም በወላይታ ዞን ወላይታ ሶዶ ከተማ በሚገኘው በሶዶ ዙሪያ ወረዳ ዋና አስተዳድር ጽ/ቤት አዳራሽ ከቀኑ 7 ሰዓት ጀምሮ እንደሆነ ከፓርቲው የድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡

በተጨማሪም እሁድ ሚያዝያ 28 ቀን 2004 ዓ.ም ደግሞ በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ በጋሞጐፋ ዞን አርባምንጭ ከተማ በሚገኘው ሲቀላ ፖሊስ አዳራሽ ከቀኑ 7 ሰዓት ጀምሮ ከህዝቡ ጋር ውይይት እንደሚደረግ ተጠቁሟል፡፡ በሁለቱም የውይይት መድረኮች ከህዝቡ ጋር የሚመክሩት የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ፣ ኢንጂነር ዘለቀ ረዲ፣ በፓርላማ ብቸኛው የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ የሆኑት የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ እና የፓርቲው የደቡብ ቀጠና አደራጅና ሰብሳቢ አቶ ግርማ አማረ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ አመራሮቹም የአካባቢው መስተዳደር አባላት ለሚደረገው ሀገራዊ ውይይት ላደረጉት ቀና አስተዋፅዖ ከወዲሁ በአንድነት ፓርቲና በህዝቡ ስም አመስግነዋል፡፡

## ምክር ቤቱ . . .

ከገፅ 2 የዞረ

ብቻ ማሸነፍ ችለው የነበሩት ተቃዋሚዎች አስገራሚ ለውጥ ታይቶበታል በተባለው የምርጫ 1997 ዓ.ም 173ቱን በማሸነፍ 32 በመቶ ድምጽ መያዝ ችለው ነበር፡፡ ሆኖም በወቅቱ በነበረው ሁኔታ በመደናገጥ በተወሰነ መልኩ ነበር የሚባለውን ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ ኢህአዴግ መጠርቀሙ ይነገራል፡፡ በውጤቱም በ2002 ዓ.ም በነበረው ምርጫ ‹መድረክን› የሚያክል ጥምረት መፍጠር ቢችሉም ተቃዋሚዎች ማሸነፍ የቻሉት አንድ ወንበር ወይም 0.2 በመቶ ብቻ ነበር፡፡ ይህ በ1992 ዓ.ም ከነበረው 2 በመቶ ውጤት በ1.8 በመቶ የሚያንስ ነው፡፡

### የመሪ አገር

«የኢህአዴግ መንግሥት ሀገሪቷ የመሪ ሀገር (leader state) አድርጓታል» ሲሉ የሚተቹ ምሁራን አሉ፡፡ የዚህን አካሄድ መጨረሻ የሚተነብዩ ተንታኞችም የህዝብ ተወካዮች አባላት በሀገርና በመንግሥት መካከል ያለውን ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል በተቃራኒው እንደሚያደርጉት ይነገራል፡፡ ማንኛውም ተወካይ በየትኛውም አካሄድ ከመንግሥት ጥቅም ይልቅ የሀገር ጥቅምን እንደሚያስቀድም ይገመታል፡፡ በመሆኑም ሀገርን እየጎዳ መንግሥት የመሠረተውን ወይንም የሚወከሉባትን ተቃዋሚ « የሚጠቅም» ህግ ቢወጣ /ረቂቅ -ተወካዮች ይቃወሙታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሪ ሀገር ግን ጉዳዩ የተገላቢጦሽ እንደሆነ ይነገርል፡፡ ተወካዩቹ ከሀገሪቱ ይልቅ የተወከሉበትን ሀገር ጥቅም የሚከላከሉ ሆነው ይወጣሉ፡፡ እንደ ዘርፉ ምሁራን እይታ የእነዚህ አካላት ውሱን ጥቅመኝነት (Partial opportunism) የራሳቸውንም ነፃነት የሚጋፉ እስከ መሆን ይሄዳል፡፡ የዚህ አካሄድ መጨረሻ ጠ/ሚ/ሩን መሾምና መሻር የሚችለውን ም/ቤት በተቃራኒው ጠ/ሚ/ሩ የሚሰራው አሊያም የሚበትነው እስከ መሆን ህልውና (Viability) የሌላው ያደርገዋል፡፡

# ብአዴን አማርኛ ተናጋሪ የሕወሓት ክንፍ ወይስ የአማራው ወኪል?

አንዳርጌ መስፍን ሽፈራው

እንደሚታወቀው ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ የአማራ ህዝብ ላይ እጅግ ዘግናኝና አሣፋሪ የሆኑ የጅምላ ግድያዎች ተካሂደውበታል፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ አማራዎች እጆቻቸውና እግሮቻቸው የፊጥኝ እየታሰሩ እስከነ ሕይወታቸው በገደል ተጥለዋል፡፡ አሶሳ ላይ ስብሰባ ተብለው ተጠርተው ባንድ መጋዘን ውስጥ ከታጎሩ በኋላ በውጭ ተዘግቶባቸው በእሳት ተቃጥለዋል፡፡ በዚህ ሥልጡን ዘመን እንዲህ ዓይነት ዘግናኝ ግድያ በንፁሐን ዜጎች ላይ ይፈፀማል ተብሎ አይታሰብም፡፡ የአሰቦት ገዳም ደካማ መነኮሳት ሳይቀሩ ተገድለዋል፡፡ ጥቅምት 5 ቀን 1999 ዓ.ም የአቦ በአልን ለማክበር ከጅማ ከተማ 60 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ባሻሸ አቦ በተባለ አካባቢ በአሮጊቶችና በሴቶች ላይ የተፈፀመው አሰቃቂ ግድያ(እርድ) ኃይማኖትን ሽፋን ያደረገ ቢመስልም የሥርዓቱን አስከፊነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ነው፡፡

ካለፈው የካቲት ወር መገባደጃ ጀምሮ ከቤንች ማጂ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ በሺዎች የሚቆጠሩ አማራዎች ተባረው ርቃናቸውን አዲስ አበባ ሲገቡ አይተን አንጀታችን በሐዘን ተላውሷል፡፡ መጠጊያ አጥተው ላይ ታች ሲንከራተቱ ማየት ደግሞ ሌላው አሣዛኝ ገፅታ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ የከፋው ቤተክርስቲያን እንኳን «ከሞቀው ዘፋኝ» ሆና ወይም በጎሳ አስተሳሰብ ታጥራ አላስጠጋም ማለቷ የእምነቱን አባቶች ጥያቄ ውስጥ ያስገባ ተግባር ሆኖ አልፏል፡፡ ይህንን በተመለከተ አንድ አዛውንት፡-

“ድሮ ድሮ ቤተክርስቲያን እንኳንስ መጠጊያ ላጡ ዜጎች ይቅርና ወንጀል የፈፀሙ ወንጀለኞች ቤተክርስቲያን ገብተው ደውል በመደወል መንግሥት ምህረት እንዲያደርግላቸው ሲጠይቁ የሃይማኖት አባቶችም ያማልዱ ነበር፡፡ የዛሬዎቹ አባቶች ግን ደጀሰላምን ለመጠለያነትም እንኳ ከለከሉ” በማለት ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡ አዛውንቱ እንዳሉት እነዚህ የዘመኑ የሃይማኖት አባቶች ዜጎችን በጭንቅ ጊዜ ቤተክርስቲያን እንዳይጠለሉ ሲከለክሉ ይህ የመጀመሪያ ጊዜያቸው አይደለም፡፡ በ1993 ዓ.ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የመብት ጥያቄ ባነሱበት ወቅት የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ከግቢ አስወጥተው ሲያሳድዷቸው ቅድስት ማርያም ወርደው አባቶች ካሣዳጇቻቸው እንዲታደጓቸው ሲማፀኗቸው አሳልፈው መስጠታቸው አይዘነጋም፡፡

ከጉራፈርዳ የተሰደዱት ዜጎች እንዳረጋገጡት ድብደባና እንግልት ደርሶባቸዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ወጣት እየተደበደበ መኪና ላይ ቢጫንም በደረሰበት ድብደባ ተበሳጭቶ ከመኪናው ላይ ተወርውሮ ራሱን ፈጥፍጦ ገሏል፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ፍትሕ ከመጥፋቱ የተነሳ ራሳቸውን በገመድ እያነቁ የሚገሉና ከላያቸው ላይ ቤንዚን እያርከፈከፉ ክብሪት እየጫሩ ተቃጥለው የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር እየተበራከተ መጥቷል፡፡ መምህር የኔሰው ገብሬ እስከ ጠ/ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ድረስ አቤት ቢልም ሰሚ በማጣቱ ተበሳጭቶ ራሱን አቃጥሎ ሰማዕት ሆኗል፡፡ ካድሬዎችና ባለሥልጣናት ግን “አእምሮው ንክ ነበር” ሲሉ በከፈለው ዋጋ ተሳልቀውበታል፡፡ ጎንደርም አንድ መምህር እንዲሁ ፍትሕ አጥቶ ራሱን በገመድ ሰቅሎ ሲሞት “አእምሮ በሽተኛ ነበር” አሉት፡፡ ይህንን በተመለከተ አንዳንድ የስርአቱ ተቺዎች “ኢሕአዴግ አንድ ጊዜ ብቻ አይገልም፡፡ ከገደለ በኋላም የሟቾችን ታሪክ ጥላሸት ይቀባል” በማለት ይነቅፋሉ፡፡

አቶ ሽፈራው ሽጉጤም ዜጎችን ማፈናቀላቸው ሳያንስ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም በቴሌቪዥን ቀርበው፡-

“አንድም አማራ አልተባረረም፡፡ 33 የሚሆኑ ብቻ ደን ስላቃጠሉ ተባረዋል” በማለት የሰጡት ማስተባበያ ራሱ ሕሊናን የሚያቆስል ነው፡፡ ይህንን ፕሮግራም የተከታተሉ አንድ የደቡብ ኢትዮጵያ ተወላጅ ግርምታቸውን እንዲህ ሲሉ ገልፀዋል፡-

“እነዚህን አማራዎች ለማባረር ሲባል ደኑ ላይ እሳት ለቀቁና እነሱ እንዳቃጠሉት ተቆጥሮ ለቴሌቪዥን እይታ አበቁት፡፡ ምነው እንግዲያው የእነሱ ቤት ሲቃጠል አላሳዩን? እሺ ይሁን እነሱ አቃጠሉት እንበል፤መቼም እነዚህ ዜጎች ሆነ ብለው ለጥፋት አያቃጥሉትም፡፡ በቆሎ ወይንም ማሽላ ለመዝራት ነው፡፡ ታዲያ ለልማት ከሆነ ወንጀሉ ምኑ ላይ ነው?” በማለት ይጠይቁና “የደኑ መቃጠል ያየር መዛባትን የሚያስከትል ከሆነ የሕንድ፣የቻይናና የቱርክ ቱጃሮች የምዕራብ ኢትዮጵያን ደን በዘመናዊ ቡልዶዘር እየመነገሉ ምድረበዳ ሲያደርጉት ለምን ዝም ተባሉ? ታሪክ ይፍረደው!” ሲሉ በምሬት ተናግረዋል፡፡

አቶ ሽፈራው ሽጉጤ “አንድም አማራ አልተባረረም” ይበሉ እንጂ አማራን ከደቡብ ክልል ጠራርጎ ለማስወጣት በወጣው እቅድ መሠረት እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ 78 ሺ አማራዎች እንደሚባረሩ መረጃ አለ የሚሉ ወገኖችም አሉ፡፡

ሌላው አሳፋሪ ጉዳይ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ በጻፉት ደብዳቤ ላይ አባሪ ተደርጎ የተገኘዉ ወረቀት “ወደ ሀገራችሁ ሂዱ” የሚል ሀይለ ቃል መገኘቱ ነው፡፡ ለመሆኑ ሰውየው እንዲህ ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? መቼም ቢሆን አቶ ሽፈራውን የሚያህል ሰው የሀገርን ትርጉም አያውቅም ለማለት ይከብዳል፡፡ እሳቸውን ጨምሮ በኢህአዴግ ቋንቋ ሁላችንም ያለችን የብሔር ብሔረሰቦች አገር የሆነችው አንዲት ኢትዮጵያ ነች፡፡ ርግጥ ነው እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ፣የተወለደበት ቀዬ ወይንም እትብቱ የተቀበረበት የትውልድ ሥፍራ አለው፡፡ ችግሩ ግን አማራ በዚህ 20 ዓመት ውስጥ የሀገርም፣የክልልም፣የቀየም ባለቤት አለመሆኑ ነው፡፡ ስማቸውን እንዳልጠቅስ ያስጠነቁቁኝ አንድ ጎንደሬ፡-

“አማራ በኢህአዴግ ዘመን ከማርስ እንደመጣ ፍጡር መብረጃና መቋጫ በሌለው ሁኔታ ላይ ታች እየተዋከበ ማረፊያ ዛፍ ያጣ አሞራ ሆኗል፡፡ ተከዜን የሚያህል ዓለም አቀፍ ወንዝ ወሰን ሆኖ እያለ ጊዜ አገኘን ብለው ሰቲት ሁመራን፣ወልቃይት ጠገዴንና ማይፀምሪን ወደ ትግራይ ከለሏቸው፡፡ አማራውን ግን ከቀየው እያፈለሱት ነው፡፡ ይህም ሆኖ እንደ ሀገር አብረን እስከኖርን ድረስ ችግር የለውም፡፡ ችግሩ የሚመጣው የትግራይ ሪፐብሊክ የመሠረቱ እለት ነው፡፡ ያኔ ሆዱን ሞልቶ ተኝቶ የሚያድር አማራ አይኖርም፡፡ ሌላው አማራንና የኢትዮጵያን ሕዝብ የናቁበት ሁኔታ ነው፡፡ ለባህሪ መግዣ (ማባበያ) የመተማን ለም መሬት ለሱዳኖች እንደ አንባሻ እየቆረሱ መስጠታቸው ነው፡፡ ይህንን ውል የፈፀሙት ሚንስቴር ደረጃ ደርሰዋል” በማለት በቁጭት ተናግረዋል፡፡

ለመሆኑ በአማራ ላይ የበቀሉ ሁኔታ መነሻ ምክንያቱ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ አንዳንድ አማራዎች በግልጽ እንደሚናገሩት ከሆነ “ሕወሓት ገና ከመነሻው ጀምሮ ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ የትግራይን ሪፐብሊክ ለመመስረት ሲነሳ አማራን ቀንደኛ ጠላቱ አድርጎ ነው፡፡ ይህንንም በፋኖነት ዘመኑ ‘አማራ ገዳይ’ እያለ ተግብሮታል፡፡” ይላሉ፡፡ እኒሁ የአማራ ተቆርቋሪዎች “የሚገርመው ግን ዛሬም መንግሥት ሆኖ ከ21 ዓመት በኋላ እንኳን አማራን እየተከታተለ ከማሳደድ አለመቆጠቡ ነው፡፡ አማራ የጭንቅላት ካንሰር ሆኖበታል” ይላሉ፡፡

አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች በበኩላቸው “ሕወሓት ወደ ሥልጣን ከመምጣቱ በፊትም ሆነ ከመጣ በኋላ በፈፀማቸው ጥፋቶችና በሚፈፅማቸው ስህተቶች ሁሉ የታሪክ ተጠያቂና ተወቃሽ ላለመሆን በአማራ ላይ ጣቱን ከመቀሰር ተቆጥቦ አያውቅም፡፡ ማባሪያ በሌለው የፕሮፖጋንዳ ዘመቻና የማፈናቀል ተግባር ተጠምዷል” ይላሉ፡፡

አንድ ስማቸው እንዲጠቀስ የማይፈልጉ ግለሰብ ደግሞ “ሕወሓት በሽብር ተፀንሶ በሽብር ተወልዶ፣የባሩድ ጪስ እያሻተተ ያደገ ፋኖ ድርጅት በመሆኑ በአእምሮው ውስጥ ሠላም አልተቀረፀበትም፡፡ የተጠናወተው ጀብደኝነትና ማንአህሎኝነት ነው፡፡ በመሆኑም በማኅበረሰቡ ውስጥ የተረጋጋ ሠላም የለም፡፡ ሕወሓት የፋብሪካ ጭስ ከማየት ይልቅ የባሩድ ጭስ ማሽተትን ይናፍቀዋል፡፡ በዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ሕዝቡ የሰቀቀን ኑሮ ነው የሚኖረው፡፡ ከሥራ መባረር፣ከመኖሪያ ቀዬ መፈናቀል በየእለቱ የምናያቸው ክስተቶች ናቸው፡፡ ሕወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ እስከ ቆየ ድረስም እነዚህ ሁኔታዎች ይቀጥላሉ” በማለት ቁጭታቸውን ይገልፃሉ፡፡ ሌላው አስተያየት ሰጪ በበኩላቸው፡-

“ሕወሓት ኢትዮጵያን የባሕር በር ማሳጣቱንና ኤርትራን ተዋግቶ ማስገንጠሉን ሕጋዊና ፍትሐዊ ለማድረግ አንቀጽ 39ኝን በሕገ መንግሥት ቢቀርጽም የኢትዮጵያን ሕዝብ ይሁንታ ግን ማግኘት አልቻለም፡፡ በዚህ ምክንያትም አምባገንን ሆኗል፡፡ ሥልጣን አያያዙ በሕገወጥና በትጥቅ ትግል ነው፡፡ በኃይልና በመፈንቅለ መንግሥት የተያዘ ሥልጣን ደግሞ ሕጋዊነት ስለሌለው የተረጋጋ ሠላም የለውም፡፡ ሕወሓት/ኢህአዴግም ወይ የንጉሣውያን ደም አለኝ ብሎ ዙፋኑን አልወረሰ ወይ ዴሞክራት ነኝ ብሎ በመድበለ ፓርቲ ሥርዓት በምርጫ አሸንፎ ሥልጣን አልያዘ ወይ ለይቶለት ኮሚንስት ነኝ ብሎ የአንድ አምባገነን ፓርቲ ሥርዓት አልመሠረተ፤ እስከ መቼ እያምታታና ኮርጆ እየገለበጠ ይኖራል?” በማለት በትዝብት ይጠይቃሉ፡፡ እውነትም ኢህአዴግ እያምታታና እያተራመሰ የሚገዛበት ጊዜ ያበቃለት ይመስላል፡፡ ሕጋዊነትን ለመላበስ ግን ሁለት ምርጫዎች ይኖሩታል፡፡

አንደኛው የጭፍን የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ እየነዛ አገሪቱን ቀውስ ውስጥ ከቶ መሞት፡፡ ሁለተኛው ነፃ ምርጫ አካሂዶ ካሸነፈ ሕጋዊ መንግሥት መሥርቶ በሥርዓት ማስተዳደር፤ ከተሸነፈም በሥርዓት ለአሸናፊው አካል አስረክቦ የታሪክ ባለቤት መሆን ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን የሚፈጠረው አንዳንዶች “ሕወሓት ውሉ የጠፋበት ገና ከውጥኑ ‘የትግራይ ነፃ አውጭ ነኝ’ ብሎ በረሃ የገባ ጊዜ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ከድቷታል፡፡ እንዴት ብሎ ነው የካዳትን ሀገር ሕጋዊ ሆኖ የሚገዛት? ዛሬ እንኳን ከዚህ አዙሪት ውስጥ አለመውጣቱ እንዳሸመቀ መሆኑ ይታወቅበታል” እንደሚሉት ነው፡፡ ፡፡

ሰሞኑን ከጉራፋርዳ የተባረሩትን አማራዎች በተመለከተ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች አፅንኦት ሰጥተው እንደሚናገሩት ከሆነ “ኢሕአዴግ በዘር ማፅዳት ወንጀል (ethnic cleansing) በዓለም አቀፍ ፍ/ቤት መከሰስ አለበት” ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ የመኢአድ ፕሬዚዴንት ኢንጅነር ኃይሉ ሻወል ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ 2ኛ ዓመት ቁጥር 38 እትም በሰጡት ቃለምልልስ “ከደቡብ ክልል ስለተፈናቀሉት ሰዎች የሚሉት ይኖራል?” ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፡-

“. . . ጉዳዩ የዘር ማጥፋት ዓላማ ያለው ነው፡፡ በመሆኑም ከዓለም ዓቀፍ የሕግ ባለ ሙያዎች ጋር እየመከርንበት ነው” ብለዋል፡፡ አንድነት ለዴሞክራሲና ፍትህ ፓርቲ (አንድነት) በበኩሉ፡-

“በዜጎቻችን ላይ እየደረሰ ያለው የማፈናቀል በደልን በማስመሰል ፕሮፖጋንዳ መደበቅ አይቻልም” በሚል ርእስ በሰጠው መግለጫ “የኢሕአዴግ የከፋፍለህ ግዛው የጎሳ ፖለቲካ ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት 1983 ዓ.ም ጀምሮ በሀገራችን ተደጋጋሚ የሆኑ በደሎች ተፈጽመዋል፤ በበደኖ፣ በአርባጉጉ፣ በጉጂ፣ በወለጋ፣ በጋምቤላ፣ በሲዳማ፣ በተለይ በጌዲኦና በጉጂ ዞን የተፈፀሙ ግጭቶች የቅርብ ጊዜ አስከፊ ትዝታዎቻችን ናቸው” ይልና መግለጫው በመቀጠል “የደቡብ ክልል አስተዳደር በወሰደው ዜጎችን በኃይል የማፈናቀል ተግባር የሰው ሕይወት ጠፍቷል፣ ዜጎች በጦር ተወግተዋል፣ ለዓመታት የደከሙበትን ንብረት አጥተዋል. . . በዜጎች መፈናቀልና መሰቃየት ምክንያት የሆኑና መመሪያዎችን የሰጡ ባለሥልጣናት በሕግ መጠየቅ አለባቸው . . .” ብሏል፡፡ በመጨረሻም “ለመሆኑ ‹ለአማራ ሕዝብ መብትና ጥቅም የቆምኩ ነኝ› የሚለው ብአዴንስ ምን ይላል?” በማለት አንድነት ጠይቋል፡፡

አንድነት እንዳለው ለመሆኑ “የአማራው ሕዝብ ወኪል ነኝ” የሚለው ብአዴን ምን እየሠራ ነው? ብአዴንስ ማነው? የብዙዎች ጥያቄ ነው፡፡

ብአዴን ማነው?

አልታደልንም እንጂ ሕዝብ የመሪዎቹን ማንነትና ምንነት የማወቅ መብት ነበረው፡፡ የኛ መሪዎች ግን እንኳንስ ማንነታቸውን ለሕዝብ ሊያስተዋውቁ ይቅርና ስማቸውን ሳይቀር ቀይረው ያሸመቁ ናቸው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም የመጡበትን የዘር ግንድ ሳይቀር የደበቁና የቀየሩ ናቸው፡፡ ለማንኛውም የብአዴን ቁንጮ መሪዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. አዲሱ ለገሠ (አቦ) የአሰበ ተፈሪ ልጅ ወይንም ተወላጅ

2. በረከት ስምዖን (መብራቱ) ጎንደር ተወልዶ ያደገ በእናቱም በአባቱም ኤርትራዊ

3. ተፈራ ዋልዋ የሀገር ማርያም ልጅ ወይንም ተወላጅ በአባቱ አማራ በናቱ ሲዳማ

4. ታደሰ ካሣ (ጥንቅሹ) ኮረም ተወልዶ ያደገ በግማሽ ትግሬ በግማሽ አገው

5. ካሳ ተክለ ብርሃን (ሽሪፎ) ሠቆጣ ተወልዶ ያደገ ትግሬና አገው

6. ሕላዊ ዮሴፍ (ቦግን) የአ.አ ልጅ ትግሬ ምናልባትም የኤርትራ ዘር ያለበት

7. ዮሴፍ ረታ (ገይድ ወይንም ዶሪ) የናዝሬት ልጅ ቤተሰቦቹ አርሲ

8. ተሠማ ገ/ሕይወት (የጎንደር ልጅ) ሙሉ በሙሉ ትግሬ (አድዋ)

9. ከበደ ጫኔ (ጣሣ) የራያ (ዋጃ) ልጅ ትግሬና አማራ

10. መለሠ ጥላሁን አርሲ ተወልዶ ያደገ ኦሮሞ

## 11. ኃይሌ ጥላሁን (ዘሪሁን) ሰሜን ሸዋ

እነዚህ ናቸው የብሔር አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) መሪዎች የነበሩት፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ዜጎች ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ እንደ ኢትዮጵያዉያንነታቸው የአማራን ሕዝብ የመምራትም ሆነ የማስተዳደር መብት አላቸው፡፡ ጥያቄው የሚነሳው ‹‹ሁልህም ወደ ወገንህ ሲባል አክንባሎም ወደ በረት፤ርኮት ወደ ቁርበት ተጠጉ›› እንደሚባለው ሁልህም በየክልልህ በገዛ ብሔረሰብህ ተዳደር ከተባለ መብቱን ለብሔሩ ተወላጅ መተው ነበረበት ነው ነቀፋው፡፡

‹‹በቅሎ አባትሽ ማነው ቢሏት ፈረስ አጎቴ ነው

# ከሰኞ እስከ ሰኞ

## ምስራቅ ወለጋ ፎጌ ወረዳ

ባለፈው ሳምንት በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ምስራቅ ወለጋ ድንበርና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ድንበር ላይ በተፈጠረው ግጭት መፈናቀል ማስከተሉን የዜና ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቁ፡፡ ምንጮቻችን እንደሚሉት "በተፈጠረው ግጭት እስከአሁን ድረስ 26 ሰዎች የሞቱ ሲሆን ግጭቱ በፈጠረው ከፍተኛ ሥጋት በአካባቢ መፈናቀልን አስከትሏል፡፡" ይላሉ ስማቸው እንዳይጠቀስ የሚፈልጉ አንድ የአካባቢው ነዋሪ እንደሚሉት "በግጭት ከሦስት ሺ በላይ አባወራዎች ከመኖሪያ ቦታቸው ተፈናቅለው ወደ ምስራቅ ወለጋ ፎጌ ወረዳ ውስጥ የተሰባሰቡ ሲሆን የተወሰኑ ግለሰቦች ደግሞ ፋፊጋ በሬዳና በሎ በሬዳ በተባሉ ቀበሌዎች ተሰባስበው ለችግር ተጋልጠዋል" ብለዋል፡፡

እንደ ምንጮቻችን አባባል "የአካባቢው ነዋሪዎች ቤታቸውንና ንብረታቸውን ጥለው የቤተሰባቸውን ህይወት ለማትረፍ በመሸሻቸው መጠለያ፣ ምግብና ውሃ እጥረት ገጥሞአቸዋል፡፡ እርዳታም ማግኘት ባለመቻላቸው ችግር ውስጥ ናቸው፡፡" ሲሉ ያብራራሉ፡፡

## ቤኒሻንጉል ጉምዝ ማቡክ ወረዳ

በተለያዩ ጊዜ ከተለያየ የአገሪቱ ክፍሎች ተንቀሳቅሰው በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስት ማቡክ ወረዳ ላይ ሠፍረው በግብርና ይተዳደሩ የነበሩ አማርኛ ተናጋሪ አርሶአደሮች አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ በመደረጉ ለከፍተኛ ችግር ተጋልጠናል ሲሉ አማረሩ፡፡ ከሥፍራው ተባረን ባህርዳር የመጣን ነን የሚሉ አርሶአደሮች ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት "በአካባቢው ኃላፊዎች አስገዳጅነት ከ2ሺ በላይ አባውራዎች ከሥፍራው ተፈናቅለናል፡፡ የተሰጠን ትዕዛዝ ወደ ትውልድ ሥፍራችሁ ተመለሱ ብንባልም ትውልድ ሥፍራችን ለመድረስም ከደረስንም በኋላ ቦታ ባለማግኘታችን ለችግር ተጋልጠናል፡፡" ይላሉ፡፡

እነዚህ ተፈናቃዮች ነን የሚሉት ሰባት አባውራ አርሶ አደሮች በትላንትናው እለት ባህርዳር ለምግብ ዋስትና አመልክተው መፍትሔ አለማግኘታቸውን በቅሬታ ገልፀዋል፡፡ አርሶአደሮቹ እንደሚሉት "ከመኖሪያ ሥፍራችን ካፈናቀሉን የአካባቢው ባለሥልጣናትና ታጣቂዎች ባልተናነሰ መልኩ በትውልድ ሥፍራችን የሚገኙ የአካባቢው ባለሥልጣናትም በጥላቻ እያመናጨቁን ናቸው" ይላሉ፡፡ አያይዘውም "አቤት የምንልበት ቦታ አተናል፡፡ ማንም ሊሰማን አልቻለም፡፡ እባካችሁን ለሚመለከተው የመንግሥት አካል አሳውቁልን" ሲሉ የድረሱልን ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

## ቤንቺ ማጂ ጉራፋርዳ ወረዳ

ባለፈው ተከታታይ ሳምንታት በከፍተኛ የክልሉ ባለሥልጣናት ትዕዛዝ ከመኖሪያቸው በመፈናቀል ላይ ያሉት የቤንች ማጂ ዞን ጉራፋርዳ ወረዳ ነዋሪዎች ዛሬም የማፈናቀሉ ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሎአል ሲሉ የዜና ምንጮቻችን ገለፁ፡፡ ምንጮቹ እንደሚሉት "ከዚህ በፊት ከ2ሺ በላይ አባወራዎች ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ሲሆን ወደ የተለያየ ቦታ ተበታትነዋል፡፡ መሄጃ የለንም ብለው አዲስ አበባ አዋሬ አካባቢ የነበሩ ወደ ቦታችሁ ትመለሳላችሁ ብለው መልሰው ቢወስዷቸውም እስከአሁን ድረስ በሥፍራቸው ላይ አልመለሷቸውም፡፡ በሚዛን ተፈሪ ማዘጋጃ ቤት ፊት ለፊት ሜዳ ላይ ሰፍረው ለሥቃይ ተዳርገዋል" ይላሉ፡፡

"ሌሎች ከመኖሪያ ቦታቸው ያልተነሱትን አሁንም ታጣቂዎች በማስገደድ እያፈናቀሉ ይገኛሉ፡፡ የክልሉ ባለሥልጣናትና ጠ/ሚኒስትሩ የተፈናቀሉት 33 ሰዎች ብቻ ናቸው ቢሉም የማፈናቀል ሥራው ዛሬም ተጠናክሮ ቀጥሎአል" ይላሉ፡፡

## ብአዴን አማርኛ . . .

አለች›› እንደሚባለው በአንድ ወቅት አቶ ታምራት ላይኔ(ጌታቸው ማሞ) ‹‹በእናቴ ወሎዬ በአባቴ ጎንደሬ ነኝ›› ብለው ነበር፡፡ ኡጋዴን ወርደው ግን ‹‹ሽርጣም ይሏችሁ የነበሩትን ነፍጠኛ አማራዎችን አሳዩዋቸው. . .›› በማለት ንፁሀን ዜጎችን አስጨፍጭፈዋል ፡፡ ሌላው የብአዴን ከፍተኛ አመራር የሆኑት አቶ ተፈራ ዋለዋ በአንድ ወቅት ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ወደ ዩኒቨርሲቲ ስለሚገቡ ተማሪዎች የኮታ አደላደል ጉዳይ ለሕዝቡ ለማስረዳት፣ እግረ መንገዳቸውንም ፖለቲካቸውን ‹‹ለመስራት›› ሰብስበው ‹‹ከክልሉ ብሔረሰቦች ተወላጅ ልጆች 2 ነጥብ ባልሞላ መግባት ይችላሉ. . .›› በማለት ሲናገሩ ‹‹እዚህ ተወልደው ያደጉት የአማራ ልጆችስ?›› ተብለው በሕዝቡ ሲጠየቁ ‹‹አማራውማ ድሮ ተምሯል›› በማለት የፌዝ መልስ ነበር የሰጡት፡፡ በተጨማሪም ‹‹ብአዴኖች›› የጎንደር መሬት ተቆርሶ ወደ ትግራይ ሲከለልም ትንፍሽ አላሉም፡፡ ለነገሩ ሊሉም አይችሉም፣ አማርኛ ተናጋሪ የሕወሓት ክንፍ ናቸውና፡፡

አንዳንድ የዋሀን "ብአዴን ምን እየሰራ ነው?" ብለው ለጠየቁት ጥያቄ ከበቂ በላይ መልስ የሚሆን ይመስለኛል፡፡ እውነት እንነጋገር ከተባለም ብአዴን አማርኛ ተናጋሪ የሕወሓት ክንፍ እንጂ አማራን አይወክልም፡፡ በ1983 ዓ.ም የሽግግር መንግሥቱ ጊዮን ሆቴል ላይ ሲመሠረት የሀገሪቱ ዜጎች ወኪሎቻቸውን ሲልኩ አማራ ወኪል አልነበረውም፡፡ እንዲልክም እድሉ አልተሰጠውም፡፡ በወቅቱ አቶ መለስ ዜናዊ "አማራ ወኪል የለውም፤ወደ ፊት ግን ተደራጅቶ እንደሚልክ ተስፋ አለን" ማለታቸው አይዘነጋም፡፡

በዚህ መሠረት በ1984 ዓ.ም መጋቢት ወር ላይ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአሕድ) ሲመሰረት እንደተለመደው ነበር ሕወሓት በቆረጣ የገባው፡፡ አዲስ ድርጅት እስከ ሚመሰርት ድረስ አላቆይ ብሎት ወደ አማራ ክልል እንደ መሸጋገሪያ ድልድይ የተጠቀመበት ሕብረ-ብሔራዊውን ድርጅት ኢሕዴንን አፍርሶ "ብአዴን" ብሎ በመሰየም ባሕርዳር ላይ አምባሻ ቆርሶ፣ፈንድሻ ረጭቶ "ከዛሬ ጀምሮ የአማራ ሕዝብ ወኪል ነህ" ብሎ መርቆ ለቀቀው፡፡ እንግዲህ ባጭሩ ብአዴን ማለት ይሄ ነው፡፡

## የሰሜን ጐንደር ሕዝብ የቁም እስረኛ ሆኗል

"ኢህአዴግ በአማራ ብሔር ላይ ጣቱን ቀስሯል" ሲሉ አንዳንድ የሰሜን ጐንደር አርሶአደሮች ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡ የዜና ምንጮቻችን እንደሚሉት "ኢህአዴግ የአማራውን ህዝብ ከመኖሪያውና ከሥፍራው ለማፈናቀልና የሃይማኖት ብጥብጥ ለማስነሳት እቅድ ይዞ እየሰራ ነው፡፡ ደቡብ የሚገኙ አማሮችን በመመሪያ እያፈናቀለ ይገኛል፡፡ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ያለውን ቀጥሎአል፡፡ ተፈናቅለው የሚመለሱትም እንዲቋቋሙ ምንም ዓይነት ድጋፍ አይደረግም" ብለዋል፡፡

እነዚህ ጉዳዩን በቅርብ እየተከታተልን ነው የሚሉት አርሶ አደሮች እንደሚሉት ሰሞኑን ደግሞ በሰሜን ጐንደር ሱዳን ድንበር አካባቢ በምትገኝ ምዕራብ አርማጭሆ /ኢብርሃጂራ/ በምትባል ወረዳ በእርሻ ሥራ ተሰማርተው የሚኖሩ አርሶአደሮች የእርሻ መሬታቸውን ተነጥቀው ተባረዋል፡፡ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ በአካባቢው በእርሻ ሥራ ላይ ያሉትን አርሶ አደሮች መሬቱ "በብሎክ" ስለሚደለደል ያለሰለስኩቱ ማሣዬ ነው፤ ለኔ ይገባኛል የሚል ጥያቄ እንዳያነሱ ማስጠንቀቂያም ተሰጥቷቸዋል፡፡ አንዳንድ ታዛቢዎች "የኢትዮጵያን መሬት ቆርሶ ለሱዳን በመስጠት በሥፍራው ያሉትን አርሶአደሮች አፈናቅሏል" ይላሉ፡፡

የዜና ምንጮቻችን እንደሚሉት "ታች አርማጭሆ ወረዳ /ሣንጃ/ ለረጂም ዓመታት ኪዳነምህረት ቅዱስ ሚካኤል ጽላት ማደሪያ ሥፍራ ለልማት በሚል ስልታዊ አባባል ለአንድ ባለሀብት መወሰኑ በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ ከፍተኛ ቅሬታን ፈጥሮአል፡፡ ውሳኔው የአካባቢው ህብረተሰብ ባለመቀበሉ የወረዳው ኃላፊዎች ህብረተሰቡን ሰብስበው ለማግባባት ቢሞክሩም ህዝቡ አንቀበልም በማለቱ በአካባቢው ውጥረት ነግሷል፡፡ በምርጫ 97 ኢህአዴግ ምንም አይነት ድምጽ ያጣበት አካባቢ በመሆኑ የአካባቢውን ህብረተሰብ እንደጠላት እያየ ከፍተኛ የሆነ አስተዳደራዊ በደል ሲፈጽምበት የቆየ አካባቢ ነው፡፡" ብለዋል፡፡

በመጨረሻም ምንጮች እንደሚሉት "በአሁኑ ጊዜ የአካባቢውን ህብረተሰብ ነፃነቱ ሙሉ በሙሉ ተገፏል፡፡ ሁሉም ዜጋ የቁም እስረኛ ተደርጓል፡፡ ከሚኖርበት ቀበሌ ወደየትኛውም ቀበሌ ለመሄድ ቢፈልግ ለአካባቢው ኃላፊዎች አሳውቆ የይለፍ ወረቀት መያዝ ይጠበቅበታል፡፡ የፍቃድ ወረቀት ሳይኖረው ከሚኖርበት ቀበሌ ተነስቶ ወደ ሌላ ቀበሌ ቢሄድ ይታሰራል" ብለዋል፡፡

## በአፋር ክልል በተፈጠረ ግጭት 3 ሰዎች መሞታቸው ተገለፀ

በአፋር ክልል ዞን 3 አሚባራ ወረዳ እሁድ ሚያዝያ 21 ቀን 2004 ዓ.ም ጠዋት ካላአስ ቀበሌ በተፈጠረ የእርስ በርስ ግጭት 3 ሰዎች ሲሞቱ 6 ሰዎች መቁሰላቸው ተገለፀ፡፡

በወረዳው አካባቢ በተለያየ ጊዜ ግጭቶች እንደሚፈጠሩና የመንግስት አካል ከዚህ በፊት ግጭቶችን ለማስቆም እንዲረዳቸው ማኅበረሰቡ ቢጠይቅም እስከአሁን መፍትሄ እንዳልተገኘ ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡

የወረዳው መስተዳደርና ፖሊስ እንዲሁም የዞኑ አስተዳደር ኃላፊዎች በተንቀሳቃሽ ስልኮቻቸው ስለ ጉዳዩ ለማጣራት ብንሞክርም አልተሳካም፡፡ ይሁን እንጂ ወደ ክልሉ ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ስለ ሁኔታው ጠይቀን በተጠቀሰው ጉዳይ ምንም መረጃ እንዳልደረሳቸው አቶ ሰለሞን በተለይ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀውልናል፡፡

## በአርሲ አሳሳ የተገደሉት ሰዎች ቁጥር ሰባት ደርሷል

### - የታሰሩት ቁጥር 250 በላይ ደረሰ

በአርሲ አሳሳ ባለፈው አርብ በተፈጠረው ግጭት በፌደራል ፖሊስ የተገደሉት ሰዎች ቁጥር ወደ ሰባት ከፍ ማለቱን ከስፍራው ያገኘናቸው መረጃዎች አመለከቱ፡፡ ባለፈው አርብ በአርሲ አሳሳ በሙስሊሙ ህብረተሰብና በፌደራል ፖሊሶች መሀከል በተፈጠረው ግጭት የሞቱት ሰዎች 5 የነበረ ቢሆንም ትላንት በደረሰን መረጃ የሟቾቹ ቁጥር ወደ 7 እንደ ደረሰ አመላክቷል፡፡

ስለ ግጭቱ መንስኤ መንግስት ባወጣው ዘገባና እና ከስፍራው በሚወጡ መረጃዎች መካከል ልዩነት የሚታይ ሲሆን፣ ስለሁኔታው ከገለልተኛ ምንጮች ለማጣራት አልተቻለም፡፡ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለፍኖተ ነፃነት እንደገለፁት ግጭቱ የተቀሰቀሰው ሼህ መስኡድ የተባሉ የሀይማኖት አባት "አህባሽ አይወክለንም" እንዲሁም "ለ20 ዓመት ኢህአዴግን ደግፈን ኖረን እንዴት አሸባሪዎች ናችሁ ይለናል" የሚሉ መልዕክቶችን በትምህርታቸው ውስጥ አካተው በማስተማራቸው ነው፡፡ መንግስት ግለሰቡን ለመያዝ ያደረገውን ጥረት የአካባቢው ሙስሊም ህብረተሰብ በመከላከሉ በተፈጠረው አለመግባባት ፖሊሶች በተቃዋሚዎች ላይ በከፈቱት ተኩስ አንድ የስድስት አመት ህጻንን ጨምሮ መገደላቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በጉዳዩ ላይ የመንግስትን አስተያየት ለማግኘት የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ምክትል ኃላፊ የሆኑት አቶ ሽመልስ ከማል ጋር ደውለን ጉዳዩ በምርመራ ላይ እንደሆነ ገልፀው አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበዋል፡፡

## ጋምቤላ የሼክ መሐመድ አላሙዲን ሰራተኞች ላይ በደረሰው ጥቃት 3 የውጪ ሀገርና 5 ኢትዮጵያውያን ተገደሉ

በጋምቤላ ክልላዊ መንግስት አቦቦ የሼክ መሐመድ ሁሴን አሊ አላሙዲን ንብረት በሆነው ሳውዲ ስታር በተሰኘው እርሻ ልማት ሠራተኞች ላይ የመሬት ቅርምቱን በሚቃወሙ ኃይሎች በደረሰ ጥቃት ሶስት ፓኪስታናውያንና አምስት ኢትዮጵያውያን መገደላቸውን በአካባቢው የሚገኙ ምንጮቻችን ዘገቡ፡፡

ቅዳሜ ሚያዝያ 20 አመሻሹ ላይ በአካባቢ በጋምቤላ አቦቦ ስራቸውን ጨርሰው ወደ ካምፓቸው በመግባት ላይ በነበሩበት ወቅት በተከፈተው በዚህ ጥቃት ከሞቱት ስምንት ሰዎች ውጪ የቆሰሉ ሰራተኞችም እንዳሉ ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡ በጥቃቱ የተደናገጡ የሳውዲ ስታር ሰራተኞች ከአቦቦ ወደ ጋምቤላ ከተማ ሸሽተው እንደተጠለሉ ምንጮቹ አያይዘው አስረድተዋል፡፡

ምንጮቹ "በጋምቤላ ክልል በተፈጠረው የመሬት ቅርምትና የአካባቢውን ነዋሪዎች ከየለም ቦታዎች የማፈናቀሉ ሥራ እንዳቀጠለ ሲሆን ግጭቱም እየተባባሰ ይገኛል" ይላሉ፡፡ አያይዘውም የሟቾቹ አስክሬን በትላንትናው እለት እንደተሸኘ ተናግረዋል፡፡

መንግስት በሰጠው መግለጫ የሟቾቹን ቁጥር አምስት ብቻ እንደሆነ መግለፁ ይታወሳል፡፡

# መሸሽ መሸሽማ አንበሳም ይሸሻል መለስ ያለ ለታ አገር ያበላሻል

ከመ/ር ቀለሙ ሁነኛው
kelemhun@yahoo.com

ማክሰኞ ሚያዝያ 17/2004 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ በአዲስ አበባ መስተዳድር በየካ ክፍለ ከተማ ስር የሚገኙ ት/ቤቶች የመሠረታዊ መምህራን ማህበር አመራር አባላት በኮከበ ፅባህ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት አዳራሽ ከፍተኛ ጭቅጭቅ የበዛበት ሰብሰባ አካሂደው ነበር:: የኢመማ ፕሬዝዳንት አቶ ዮሐንስ በንቲ ከአዲስ አበባ ከተማ መምህራን ማህበር አመራር አካላት ጋር በመሆን ስብሰባው ላይ የተገኘ ቢሆንም ያልጠበቀው ውዝግብ ገጥሞታል:: በተለይም ስብሰባው የተጠራው ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ መምህራንን ለማባረር በፓርላማ በፎከሩ በሳምንቱ በመሆኑ የመምህራኑ ፊት እንደ ትንታግ እሳት የሚፋጅ መሆኑ በቂ ማስረጃ ነው::

በዕለቱ የፕሬዝዳንቱ መገኘት አቢይ ጉዳይ ስለ እርከን ማስተካከያው ማህበሩ የሄደበት የእስካሁን ጉዞና ቀጣዩ እንቅስቃሴ ምን መምሰል እንደሚገባው ማብራሪያ ለመስጠት ቢሆንም የስብሰባው ታዳሚ መምህራን በከፍተኛ ጩኸት አጀንዳውን ተቃውመውታል:: በብዙሀን መገናኛና በተለይም ከጠቅላይ ሚ/ሩ የፓርላማም ንግግር ከተረዳነው ውጭ አዲስ ነገር ስለሌለህ አናዳምጥህም በሚል ሌሎች አጀንዳዎች እንዲያዝላቸውና እንዲያወያዩ ጠየቀ::

የስብሰባው አባላት ቅድሚያ የሰጡት ከኮከበ ፅባህ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤትና ከሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ስለተባረሩት አምስት መምህራን ወደ ሥራ መመለስ ጉዳይ ነበር:: ከተባረሩት መምህራን ት/ቤት ማህበሩን ወክለው የመጡ የማህበሩ አመራሮች በመምህራኑ ላይ የተወሰደው እርምጃ እጅግ አሳዝኝና እንደ ድንገተኛ /sudden death/ የሚቆጠር መሆኑን አብራርተዋል:: ሥራ ያቆሙት ሁሉም መምህራን ሆነው ሳለ በጣት የሚቆጠሩ መምህራንን ብቻ ለይቶ በአንዲት ገፅ ወረቀት ማባረሩ በህገ መንግስቱ ላይ የተደነገጉ የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የጣሱ እንደሆኑ አፅንኦት በመስጠት አስረድተዋል:: በተለይም ከሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከተባረሩት አራት መምህራን መሀከል ሦስቱ በዕለቱ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ክ/ጊዜ ክፍል ስላልነበራቸው ወትሮም እንደሚያደርጉት ዘግይተው ሦስተኛውን ክ/ጊዜ ለማስተማር ተዘጋጅተው ሲመጡ የሰንብት ደብዳቤ የተሳጣቸው ናቸው:: አንደኛው መምህር ደግሞ እናቱ በጠና መታመማቸው የፋክስ መልዕክት ደርሶት ወደ ቦረና ዞን በመሄዱ በወቅቱ አልነበረም፤ ሲመለስ ግን ከስራ መባረሩን የሚያስረዳ ደብዳቤ ደረሰው:: ኮከበ ፅባህ ት/ቤት የተባረረው የፊዚክስ መምህር በማስተማር ሥራውን የጠለቀ ዕውቀት እንዳዉ እጅግ የተመሰከረለት በኮምፒዩተር ዕውቀቱ ለት/ቤቱ ከፍተኛ የሆነ ትብብር የሚያደርግና በትርፍ ሰዓቱ አስተዳደራዊ ሥራዎችን በመስራት እገዛ የሚያደርግ እንዲሁም ከውጭ መያዶች (NGOs) ጋር በመፃፃፍና ግንኙነት በመፍጠር ችግርተኛ ተማሪዎች እንዲረዱ በማድረግ ቅን ተግባር የሚፈፅም መምህር ስለመሆኑ የት/ቤቱ አስተዳደር ሕጋድ ደብዳቤ በመፃፍ ያረጋገጠለት ሆኖ ሳለ ከስራ እንዲሰናበት ተደርጓል:: ስለዚህ እነዚህ በግፍ የተባረሩ መምህራን በአስቸኳይ ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመለሱ ለማድረግ ማህበሩ ያደረገውን እንቅስቃሴ በተመለከተ ለፕሬዝዳንቱ ጥያቄ ቀርቦለታል::

መልሱ ግን አንድን ማህበር ከወከለ መሪ የሚጠበቅ አይደለም:: "እኔም የሰማሁት በወሬ ደረጃ ነዉ" የሚል ነበር የፕሬዝዳንቱ ምላሽ:: "ለአባላቶቼ ጥላ ከለላ ነኝ" የሚል አንድ ማህበር የተፈፀመውን በደል በወሬ ደረጃ እንደሰማ የበታች አካላቱን ስለጉዳዩ እውነታነት ጠይቆ ማረጋገጥ ለምን አልቻለም? የሀገር ውስጥና የውጭ ሚዲያዎች ጭምር መምህራኑን በማናገር በሰፊው የዘገቡትን ጉዳይ ቸል ማለቱ ተገቢ እንዳልሆነ ተሰብሳቢዎቹ የማህበሩን የበላይ አመራሮች በብርቱ ኮንነዋል:: የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር በወቅቱ ከየካ ክ/ከተማ የደረሰውን ስለ መምህራኑ መባረር የሚገልጽ ደብዳቤ ለኢመማ ለማሳወቅ ሁኔታዎችን ማጠናቀቁን ገልፆ መምህራኑ ወደ ሥራ የሚመለሱበትን መንገድ ከአዲስ አበባ ት/ቢሮና ከሚመለከታቸው ባለስልጣናት ጋር ድርድር እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል::

በዕለቱ የተገኙት ተሰብሳቢዎች ለኢመማ ፕሬዝዳንት የተለያዩ ጥያቄዎችን አቅርበው ነበር::

ከኢመማ ምክር ቤት እውቅና ውጭ በግልህ ለፋና ኤፍ. ኤም ሬዲዮ ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ለምን መግለጫ ሰጥተህ? ማህበሩ ያቀረበው ጥያቄ በተለይም ደረጃ 6 ላይ ቆሞ የነበረው የደረጃ እድገት እንደሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች ወደ ደረጃ 9 ከፍ እንዲል የተጠየቀው ከመንግስት ይሁንታን ተነፍጎት እያለ የማህበሩ ጥያቄ እንደተመለሰ አድርገህ መግለፅህ ተገቢ ነበርን?

ጠቅላይ ሚ/ር መለስ በሚያዝያ 7/2004 ዓ.ም የፓርላማ ማርፈጃቸው መምህራን 99.9% መደሰታቸውን የገለፁትን መረጃ የሰጣቸው ማህበሩ ነውን?

አቶ መለስ መምህራን የሀገሪቱ ህገ መንግስት አንቀፅ 42/ለ በሚፈቅደው መሠረት ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን ተጠቅመው ሥራ በማቆማቸው አሁን ከተባረሩት መምህራን በተጨማሪ በቀጣይ ለማባረር መዛታቸውን እንዴት ትመለከተዋለህ?

የሚሉ ነበሩ::

ፕሬዝዳንቱ አቶ ዮሐንስ በንቲ በፍርሃት ቆፈን ውስጥ ሆነው ምላሽ ሰጡ

➢ የመጀመሪያ ጥያቄ ምላሽ:-

"በወቅቱ እናንተም በእኔ ቦታ ብትሆኑ ኖሮ የምታደርጉት እኔ ያደረግኩትን ነበር:: ከግራ ከቀኝ ተወጥሬ መግለጫ እንድሰጥ በመደረጉ ችግሮችን ለማለዘብ ስል ተናግሬአለሁ:: የኔነው መግለጫ ከዘገቡ ብዙሃን መገናኛዎች ከሞላ ጎደል በትክክል ያስተላለፈው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ብቻ ነው:: ኢቴቪና ፋና ኤፍ ኤም ከሰጠሁት መግለጫ ለኢህአዴግ ፖለቲካዊ አካሄድ ጠቃሚ የሆኑትን ብቻ በመዘገባቸውና ያልተመለሰልን ቀሪ ጥያቄዎች እንዳሉና እነሱንም በሂደት ለማስፈፀም እንደምንታገል የገለፅኩትን ቆርጠው በማስቀረታቸው እኔም አዝኜአለሁኝ::

➢ የሁለተኛው ጥያቄ ምላሽ

"ማህበሩ ለጠቅላይ ሚ/ሩ የሰጠው አንዳችም መረጃ የለም:: በምንም አይነት መንገድ ከአቶ መለስ ጋር የተገናኘንበት ስንሰለት አልነበረም:: የማህበሩ አመራር አካላትም እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ መምህር ንግግራቸውን የሰማነው በሚዲያ ነበር:: ምን አልባት አቶ መለስ በድርጅታቸው መዋቅር ያገኙትን መረጃ ይመስለኛል የተናገሩት::"

➢ የሦስተኛው ጥያቄ ምላሽ

"መምህራን ይህንን ልትፈሩ አይገባም:: "ተሰብሳቢዎቹ ንግግሩን አላስጨረሱትም" ለምን አንፈራም! የሥራ ባልደረቦቻችን በአንዲት ገፅ ወረቀት ወደ ቆሻሻ ገንዳ እንደሚጣል እቃ ሲወገዱ እያየን እንዴት አትፍሩ ትለናለህ?" በአዳራሹ የቁጣ ነበልባል ተቀጣጠለ "በቀጣይ ስለአለመባረራችን ምን ዋስትና አለን? በምንስ ማረጋገጥ ይቻላል?"

ይህ ጽሑፍ አፅንኦት ሰጥቶ ለመዳሰስ የሚሞክረው ይህንን ነው:: ርዕሱም በአንድ የቅኔ ግጥም የተሰየመው ለዚህ ጉዳይ አፅንኦት ለመስጠት ነው::

ውድ አንባቢያን አቶ ዮሐንስ "መምህራንን ስለመባረር አታስቡ" የሚለው ምን አስበው ይሆን? ይህ ሰው እስከዛሬ የኢትዮጵያ ፖለቲካ በተለይም የአቶ መለስን የ21 ዓመታት አካሄድ በውል አልተረዳውም እንዳይባል ሰውዬው የኢመማ ፕሬዝዳንት ነው:: ከሌላው ተራ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይልቅ ለኢህአዴግ ፖለቲካ ቅርበት ያለው እሱ ነው:: ከማህበሩ አባላት ይልቅ ኢህአዴግን ካስቀደመ ሥፍራውን ይልቀቅና የኢህአዴግ ሹመኛ ይሁን:: (ወደፊት መሆኑ ባይቀርም) ነገሩን በዋዛ ፈዛዛ መምህራን በቸልታ እንዲያልፉት በማሰብና በወቅቱ በስብሰባው አዳራሽ የነገሰውን የፍርሀትና የንትርክ ድባብ ለመለወጥ ከሆነም "የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም!" እንዲሉ ነውና ማንም አይዘነጋም::

ባለፉት ሁለት አስርት አመታት የኢህአዴግ መንግስት አያሌ ሠራተኞችን በሰበብ በአስባቡ ከስራ አፈናቅሎ ለረሀብ ለእርዛት ለቤተሰብ መበተን፣ ከሀገር ለመሰደድና ብሎም ለሞት እንደ ዳረጋቸው ለአፍታም የሚዘነጋ ጉዳይ አይደለም:: ወገኖቻችን ከስራ ተፈናቅለው ለከፋ ችግር ሲዳርጉ ከንፈር ከመምጠጥ የዘለለ አንዳች ነገር አልፈየድንም::

ከምርጫ 97 በኋላ ነገሮች ፈራቸውን ስተዋል:: ኢህአዴግ በምርጫው የገጠመውን ሽንፈት ለመበቀል ጎራዴውን ከሰገባው ከመዘዘ ዓመታት ተቆጠሩ:: በተለይም ዜጎችን በከፍተኛ ፍርሃት እያሸማቀቀ የሚገኘው የፀረ ሽብር ህግ በፓርላማ ፀድቆ መተግበር ከጀመረ በኋላ የአቶ መለስ ንግግር "ንግር" እንደሚባለው የልቦለድ ድርሰት የማቅረቢያ ዘዴ የነገውን ርምጃ ፍንጭ እንደሚሰጥ በተደጋጋሚ ከተከሰቱት ሁኔታዎች መረዳት ይቻላል:: አቶ መለስ ፓርላማ ቀርበውም ይሁን ለጋዜጠኞች በሚሰጡት መግለጫ የተናገሯቸው ሁሉ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሲተገበር አይተናል:: "ከአሸባሪ ቡድኖች ጋር ግንኙነት ፈጥረው ጥፋት የሚያደርሱ ሀይሎችን በመረጃ ደረሰንባቸዋል" ባሉ በ10 እና 15 ቀናት ውስጥ የሰላማዊ ትግል አቀንቃኝ፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና ምስኪን ጋዜጠኞች ወደ ቃሊቲ ተነዱ:: የፍርድ ሂደቱ በቀጠለበት ሁኔታ "በቂ እና አሳማኝ የሆነ መረጃ ስላለን በቅርቡ ይፋ እናደርጋለን" ባሉ በቀናት ዕድሜ ውስጥ "አኬልዳማን" የመሳሰሉ ዶክመንተሪ ፊልሞች በኢቴቪ ቀረቡ "ይቅርታ የሚጠይቁ ከሆነ መንግሥት ለይቅርታው ቅድሚያ ለመስጠት ዝግጁ ነው" ባሉ በወራት ውስጥ በሽብርተኝነት ተፈርጀው የታሰሩ ሲፈቱ ተመልክተናል::

ይህ ትናንት የተከሰተ ሀቅ መሆኑ እየታወቀ አቶ ዮሐንስ በአቶ መለስ ንግግር መምህራን እንዳይሰጉ ለማሳመን መሞከር ተላላነት ነው:: አቶ መለስ እንኳን ዛሬ ቤተ መንግስት ከትመው ከደደቢት በረሃ ጀምሮ የሀሳብ ተቀናቃኞቻቸውን ሰበብ ፈጥረው ከጨዋታ ውጭ የማድረግ ብቃታቸው የረቀቀ መሆኑ ይታወቃል:: በድል ማግስት እንኳን ከአቶ ታምራት ላይኔ ጀምሮ እነ ስዬ አብርሃን የመሳሰሉ የበረሃ ወንድሞቻቸውን በሙስና ሽፋን ዘብጥያ አውርደው አይተናል:: ታዲያ የኑሮ ውድነት ያደቀቀው መምህር ከዕለት ጉርሱና ከኑሮ መሠረቱ ላይ ነቅሎ ለመጣል ምን ይቸግራቸዋል?

ላለፉት አራት አመታት ከትምህርት ጥራት ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ችግሮች እንደ አንድ መፍትሄ የተቀመጠው ለመምህራን የማስተማር ፍቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (certeficate) በግምገማ ሂደት ውስጥ በማሰለፍ መስጠት የሚል ነው:: በየዓመቱ ይተገበራል እየተባለ ቢነገርም እስከ ዛሬ ሲጓተት ቆይቶ በአሁኑ ወቅት ሰዓት ጠብቆ የሚፈነዳበት ደረጃ ላይ የደረሰ ይመስላል:: ምክንያቱ ደግሞ በተደረገው የእርከን ማሻሻያ ምክንያት በአዲስ አበባና በአማራ ክልል አካባቢ ለአጭር ቀናት የተደረጉ የሥራ ማቆም አድማዎች አቶ መለስን ግስላ ስላደረጋቸው ነው:: "ለምንስ የሥራ ማቆም አድማ ይታሰብና! ይሄ ድርጊት ለሌሎችም ባር ስለሚከፍት ከወዲሁ ቋንጃውን መቁረጥ ያስፈልጋል::" በሚል የኢህአዴግን ፖለቲካ የማያቀነቅኑና ስህተቱን ደፍረው የሚነቅሱ መምህራንን ከስራ በማባረር በችግር አረንቋ ውስጥ መዘፈቅ "ይህችም ቂጥ ሆና ቂጥኝ አፈራች" እንዲሉ ይሄም ኑሮ ሆኖ፣ ያለ አንዳች ሀጢአታቸው ኮንኖ ሲግል ለመወርወር:: እንደ አቶ መለስ የፓርላማ ገለፃ በመምህርነት የተቀጠረ ሁሉ "certified" እንደማይሆኑ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል:: አንድ መምህር ፍላጐትና ብቃት ከሌላው በሥራ ገበታው ላይ አይቀጥልም:: ደህና ሰንብች የኮሌጅ ዲፕሎማ ቻዎ! ቻዎ! የዩኒቨርስቲ ዲግሪ::

መሸሽ መሸሽማ አንበሳም ይሸሻል
መለስ ያለ ለታ አገር ይበላሻል

ሰምና ወርቁን ለአንባቢያን ትቻለሁ:: የዕለቱ ስብሰባ ከመጠናቀቁ በፊት የተባረሩ መምህራንን በገንዘብ ለመርዳት ውሳኔ ተላልፏል:: በማህበሩ አማካኝነት በየት/ቤቱ የትብብር ደብዳቤዎች ተሠራጭተው መምህራን በግፍ ከስራ ገበታቸው ተፈናቅለው ለሚራቡና ማደረያ ላጡ የስራ ባልደረቦቻቸው የአቅማቸውን እንዲለግሱ ከስምምነት ተደርሷል፤ ለወገን ደራሽ ወገን ነውና:: በወቅቱ የመባረር ስጋት በመምህራን ዘንድ መስፈኑን የገለፁ ተሰብሳቢዎች መንግስት በአቅም ማነስና በፍላጐት ሰበብ ከስራ ሲያባርር ረጅም አገልግሎት ላላቸው የጡረታ መብታቸው ተረጋግጦ ቀሪ የህይወት ዘመናቸውን ቆሎም እየቆረጠሙ እንዲገፉ ጀማሪ (ወጣት) መምህራን ከሆኑም በጥቃቅንና አነስተኛ በማደራጀት የዕለት ጉርሳቸውን የሚሸፍኑበት ሁኔታ እንዲፈጠር ለአቶ ዮሐንስ በንቲ የቤት ስራ ሰጥተዋቸዋል::

በስብሰባው መቋጫ ላይ ግን አንድ ነገር ተፈጠረ:: የስብሰባውን ሂደት በዘመናዊ መቅጃ ሲቀርፅ የነበረ ፀጉር ልውጥ ሰው መቅረጫውን ሲነካካ ድንገት ተከፍቶ እጅግ በጎላ ድምፅ ፕሬዝዳንቱ አቶ ዮሐንስ ባንቲ ያደረጉትን ንግግር ሲያሰማ በአዳራሹ ማጉረምረም ሰፈነ:: አቶ ዮሐንስም እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው የሰውዬውን ማንነት ባያውቁም በቁጣ ወረፉት "እንዴት ሳይፈቀድልህ ገብተህ ትቀዳኛለህ? ለመሆኑ ይሄ ወንጀል መሆኑን ታውቃለህ? ደግሞም አንተ ስለቀረፅከኝ የሚመጣ ነገር የለም:: እዚህ የተናገርኩትን የትኛውም አካል ፊት እናገረዋለሁ. . ." ሰውዬው ግን መረጃውን ይዞ ወደላኩት ዘንድ ወጥቶ ሄደ::

ኢትዮጵያ፣ ዜጎች በኢህአዴግ ሰላዮች የሚሸማቀቁባት የግል ሀሳብን መግለፅ ወንጀል የሆነባት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ የተከሰቶች የአቶ መለስ ዜናዊ የእጅ ሥራ ሀገር እየሆነች ነው:: ከውርደት እናድናት::

**ውድ አንባቢያን አቶ ዮሐንስ "መምህራንን ስለመባረር አታስቡ" የሚለው ምን አስበው ይሆን? ይህ ሰው እስከዛሬ የኢትዮጵያ ፖለቲካ በተለይም የአቶ መለስን የ21 ዓመታት አካሄድ በውል አልተረዳውም እንዳይባል ሰውዬው የኢመማ ፕሬዝዳንት ነው:: ከሌላው ተራ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይልቅ ለኢህአዴግ ፖለቲካ ቅርበት ያለው እሱ ነው:: ከማህበሩ አባላት ይልቅ ኢህአዴግን ካስቀደመ ሥፍራውን ይልቀቅና የኢህአዴግ ሹመኛ ይሁን:: (ወደፊት መሆኑ ባይቀርም) ነገሩን በዋዛ ፈዛዛ መምህራን በቸልታ እንዲያልፉት በማሰብና በወቅቱ በስብሰባው አዳራሽ የነገሰውን የፍርሀትና የንትርክ ድባብ ለመለወጥ ከሆነም "የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም!" እንዲሉ ነውና ማንም አይዘነጋም::**

## 180 የሃዘንና...

ከገፅ 3 የዞረ

: ይኸንንም ስትራቴጂ በማገዝ በኩል አበሻዊ ባህርይ የልምድ እጦትና ጊዜያዊ ጭብጨባ የበኩላቸውን ጉለህ ሚና ተጫውተዋል::

የቅንጅቱ ጥምር ፓርቲ የሆነ አንድ ክንፍ "በማይታመንና፤ቢሆንስ" በሚል ተቃርኖአዊ ምክንያት ፓርቲውን ከፍተኛ ሁከት ውስጥ ከከተተው በኋላ ዕገዳ ተጣለባት:: ሌላኛው "ሕብረ ብሔር" ፓርቲ አመራርም የሙሉ ጥምረቱን ሃሣብ ሳትቀበሉ በራሳችሁ ውሣኔ ተጉዛችኋል በሚል ከአመራርነታቸው ሲነሱ አብረዋቸው የነበሩ ጥቂቶች ደግሞ የራሳቸውን ቡድን አደራጅተው "ኧረ ፓርላማ እንድንገባ ፈቀዱልን - - -?" የሚል አሳዛኝ ደብዳቤ አሸናፊ ለተባለዉ ፓርቲ እስከማቅረብ የደረሱ ድርጊቶች ተከሰቱ:: በሌላ አንፃርም ሕዝብ ድምጽ የሰጣቸው አንዳንድ የተፎካካሪ ፓርቲ አባላት ከመደብደብና ከመታሰር በላይ በጥይትም ተገደሉ::

የፖለቲካው እሳት እያጋመ ባለበት ጊዜ ዋንኛው ተፎካካሪ ፓርቲ ሕዝቡን ለጠቃላላ ሠላማዊ አመጽ ለመጥራት ዝግጅት በሚያደርግበት ወቅት፤ኢህአዴግ በእኩል ሌሊት ለሠላማዊ ድርድር ዝግጁ መሆኑን አሣወቀ:: በዚህ ዕድሜ መግፊያ ከመሆን ውጪ ምንም ፋይዳ ሳይዝ በተቋጨው ድርድር የተፎካካሪ ፓርቲ መሪዎችን ጨምሮ ሕዝቡ እጅግ አዘነ:: ተስፋው ሙሉ ለሙሉ ተሟጠጠ:: ድርድሩንም በተመለከተ ከአዲስ አበባ ለቪኦኤ የሚዘግበው ጋዜጠኛ ውይይቱ ያለስምምነት መቋረጡን ዘግቦ እንደጨረሰ «አልሔድም ሸንጎ ምን ሆንኩኝ ብዬ ይበለኝ! የእጄን ነው ያገኘሁት» የሚለውን ሀገራዊ ዘፈን አየር ላይ አውሎ አስደመጠ:: ነገሩ ጋዜጠኛዊ አሽሙር መሆኑ ነው::

በተለይ ከሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ "ትግራይ" ብቻ ሲቀር በመላ ሀገሪቷ የተፈፀመው ግድያ፣አስራት፣ከቀዬ ማፈናቀል፣አካለ ጐደሎ ማድረግ፣ንብረት መዝረፍ የመሣሰሉትን ጭካኔያዊ ተግባሮች ለማውገዝ ያልሞከሩ የኃይማኖት አባቶች ዝምታ የሕዝቡን ስሜት ክፉኛ ጐድቶታል:: በጊዜው በተፈጥሮአዊው ሱናሜ አደጋ ላለቁ የኢንዶኔዥያ ዜጐች ራርቶና አዝኖ ፍታት እስከማድረግ የደረሰ አንጀት በወገን ሲሆን ጨከነ:: ይኸም የሕዝብ ቁጣ መስከረም 16 ቀን 1998 ዓ.ም በተከበረው የደመራ በአል ላይ በግልጽ ተንፀባረቀ:: እስከ ዛሬ ተደርጐ በማይታወቅ ሁኔታ የጥፋታቸው መደራረብ የበዛበት የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ምዕመን የሃይማኖት መሪዎቹን "ይሁዳ" ሲል ስየማቸው የደመራው ሥነ ስርዓት ይበጠበጣል በሚል ስጋት 11:00 ሰዓት እንኳን ሳይሞላ ተለኮሰ::

የሕዝቡን ስሜትና ፍላጐት ከቁብ ያልቆጠረው ኢህአደግ ጥቅምት 1998 ዓ.ም በወሩ መግቢያ የመጀመሪያ ቀን ፓርላማውን ከፍቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ሚኒስትሮቹን አሣወቀ:: የተፎካካሪ ፓርቲዎችን ያለመከሰስ መብት ገፎ ሥራ ጀመርኩ ሲልም አስታወቀ:: በዚህ ጊዜ ፓርላማ ገብተው የነበሩ የተፎካካሪ ፓርቲ አባላትና አንድ የግል ተመራጭ ያለመከሰስ መብት መነሳቱን በመቃወም ፓርላማውን ረግጠው ወጡ::

ገዢው ፓርቲ ፓርላማን ጨምሮ ያሸነፋችሁትን የክልል ምክር ቤት ወንበር ካልተረከባችሁ በሚለውና በሌላም ግትር አቋሙ የማስፈራራት ዘመቻ ቢከፈትም ፓርቲዎቹ ያገኘነውና የተሰጠን መቀመጫ ብዛት እኩል አይደለም በማለታቸው ንትርኩ ቀይቶ ችግር እንደሚያስከትል በዲፕሎማቶች፣ ባዉሮፓ ሕብረት፣ አሜሪካ እንዲሁም በተለይ በአናጐሜዝ (ምርጫውን ተፎካካሪ ፓርቲዎች እንደሚያሸንፉ እርግጠኛ ሆኖና ማድረግ ያለባቸውን ስትራቴጂ ጽፏል በሚል በነ በረከት ስምኦን በየውይይት መድረኩ መጽሐፏን እያሣዩ ያወገዙትና ለመጽሐፏ መነበበ አስተዋጽኦ ያደረጉለት እውቁ የመኢሶን ፖለቲከኛ ነገደ ጐበዜ እህትነት የፈረጇEቸው ዲፕሎማት መሆናቸው ይታወቃሉ) ጂሞ ክላርክን ጨምሮ በህዝቡ መሀል ስጋት የነበረ ቢሆንም ስጋቱ ስጋት ከመሆን ዘሎ ጥቅምት 21 ቀን 1998 ዓ.ም የተፈራው ነገር ሁሉ ደርሶ አዲስ አበባችን ዳግም በእንባ ታጠበች:: ነዋሪዎቿ አነቡ:: ህፃናቶች፣በሽተኞች፣አካል ጉዳተኞች በጭንቀት ተዋጡ:: ደም የለመደው ግንቦት እንደ 1981-1983 ሁሉ በ1997 ዓ.ም በጥቅምት ተመልሶ መጣ:: ከታዳጊ ህፃን እስከ አዛውንት ያሉት ዜጐች የጥይት ጭዳ ሆኑ:: አስከሬን ቤቱም አስቀምጦ፣በደዌ ከተያዘበት አልጋ የወሣንሣ ተይዞ፣ወደ ሌላ ቦታ የሚሔድበት ቀን ሠርዞ አሊያም ካለበት ሲከንፍ የደረሰ፣ ከሠርጉ ሥነ-ሥርዓት በፊት ቀድሞ ድምጹን የሰጠ ሁሉ ምነው በቀረብኝ ሲል ምሬቱን አሰማ::

"ስድስቱ የሰቆቃ ቀናት"

ቅጥምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም ማለዳ መርካቶ በሠላም ውላ በሠላም አንደምታመሽ ምንም ፍንጭ አላሣየችም:: እንደ ወትሮዋ ሁሉ ወፍ ሲንጫጫ ጀምሮ ወደ እሷ የሚተመውን ሕዝብ በእቅፏ ለመሙላት ሁለመናዋን ዘረጋግታ እየተጠባበቀች ነው:: የመርካቶ ቅድሚያ ገበያዋ፣ገንዘቧ፣አድባሯ ሰው ነውና:: የጧቷ ፀሐይም ተስፋን፣ጤንነትን፣ዕድሜን እየተኘች ሙቀቷን ያለስስት እየሰጠች ነው:: የዚህ ጽሑፍ አቅራቢም ያለበትን ወርሐዊ የስልክ ክፍየ ለመክፈል አውቶቡስ ተራ አጠገበ ከሚገኘውና ከቀናት በኋላ በተቆጣ ሕዝብ የመቃጠል አደጋ ደርሶባት ወደ ነበረው የቴሌኮሙኒኬሽን ምዕራብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለመድረስ ታክሲ ይዟል::

ይቀጥላል::

## ኢህአዴግ እውቀቱም ...

ከገፅ 7 የዞረ

አለው:: በህገመንግሥቱም የተቀመጠው መድብለ ፓርቲ ሥርዓት ነው:: የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅ ረገድ የመንግስትም የተቃዋሚ ፓርቲዎች የህብረተሰቡም ድርሻ መኖር አለበት:: ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ነጋዴው፣ ሰራተኛው፣ አርሶ አደሩ፣ አስተማሪው፣ ተማሪው፣ ባጠቃላይ ህብረተሰቡ በውጥረት ውስጥ ይገኛል:: እርግጥ ነው፤ ዝም ብሏል:: ነገር ግን ዝምታውን መንግስት ወዶኝ ነው ወይስ ፈርቶኝ? ካልሆነስ ሌላ ምክንያት ብሎ ራሱን መጠየቅ ይገባል:: በእምዬ ምንሊክ ዘመን ግብር ሲጨምሩ መኳንንቶቻቸውን ህዝቡ ምን አለ? ብለው ይጠይቃሉ እነሱም ያስተዋሉትን በሀቅ የሚናገሩ ፈሪሀ እግዚያብሄር ያደረባቸው ናቸውና አትረምርሟል ይሏቸዋል፤ አሁንም ግብር ይጨምሩና ህዝቡ ምን አለ? ሲሉ አረ ጃንሆይ አትረምርሟል ይላሉ:: ለ3ኛ ጊዜ ግብር ይጨምሩና አሁንስ ህዝቡ ምን አለ? ሲሉ አሁን ዝም ብሏል:: አሏቸው ይሄኔ አፄ ምንሊክ በ3ኛው የተጨመረውን የግብር ጭማሪ አነሱ ይባላል:: ምክንያቱም ዝምት ጥሩ አይደለም ያስፈራል:: ዝምታ የመጨረሻው ውጤት የከፋ ነው:: አፄ ምንሊክ ከ117 ዓመት በፊት ዝምታ ውጤቱ ጥሩ ያለመሆኑን ተገንዝበዋል:: አንድ መንግስት የህዝቡን ፍለጎት መረዳት ግዴታው ነው:: ኢህአዴግ ለሰላምና ደህንነት ራሱን ብቻ ዘብ እንዳቆመ ማሰቡ አግባብ አይደለም:: ሁልጊዜ እንደሚነገረው ህገ- መንገስቱ ዋስትና ነው ስለተባለ ብቻ በራሱ ውጤት አይደለም:: ህግ-መንግስቱን የማክበር ጉዳይ የሁሉም ነው:: በመጀመሪያ ላወጣው ህገ-መንገስት ተገዥ በመሆን አርአያነቱን ማሳየት የነበረበት:: ኢህአዲግ ነበር ሆኖም በርካታ ህገ-መንግስታዊ ጥሰቶች የሚፈፀሙት በኢህአዲግ ነው:: ሲፈለግ ህገመንግስት በአዋጅ ይሻራል:: መቼም ኢህአዴግ ከደርግ የሚለየው በታክቲክ ነው:: ለደርግ ማሰር፣ መግደል፣ መውረስና የመሳሰለውን ለመፈፀም ወታደራዊ ትዕዛዝ በቂ ነው:: ኢህአዴግ ግን ለፈለገው ጉዳይ አዋጅ ያወጣል:: ከዚያ ተግባሩን ይፈፅማል ሁለቱም በየትም ይሁን በውጤት ይመሳሰላሉ:: ኢህአዴግም ደርግም ለህዝብ አንድ ናቸው:: "በሲኦል በኩል ገነት ይገኛል፤" አይነት ፕሮፖጋንዳ ይለቀቅለታል:: ተቃዋሚ ፓርቲን ለመቃወም ብቻ የተቋቋሙ አድርጎ ማሰብና ሁሉንም እኔ ብቻ ልፍፅም ከሚል አባዜ ተላቆ ለውይይት ለመቀራረብ ለመደራደር በሩ ዝግ መሆን የለበትም:: «ለምስራቅ አፍሪካ ሰላም የሚሰራነ ግንባር መጀመሪያ ለአገሩ ህዝብ ሰላምና ደህንነት ዋስትና ሊሰጥ ይገባል:: ማክሲም ጎርኪ «ፀጥ ያለ ውሃ ያሥፈራኛል» ብሏል:: ፀጥ ባለ ነገር ውስጥ የምትፈጠር ኮሽታ ረብሻዋ ይጎላል:: በመሆኑም አገሪቱ የሁላችንም ናት ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል:: ትልቁ ዕውቀት ድግሞ ፀጥ ባለ ነገር ውስጥ ያለን ነገር ማወቅ ነው:: ለ21 ዓመት በመከፋፈል በማቧደን፣ በመለያየት፣ በማጋጨት፣ በማስፈራራት፣ በማሸማቀቅ፣ የሚታለል ከተገኘም በመደለል እዚህ ተደርሷል:: ይሄ ህዝብ እንዲሁ ሁሉን ያውቃል:: መሪውን ያከብራል:: ፈጣሪውን ይፈራል:: ለሚበድለው ግፍ ለሚፈጽምበት የሚበላው የሚጠጣው የሚጠለልበት ለነሳው ላዋረደው መሪ ክፋ እንዳይገጥመው የሚፀልይ ህዝብ ነው:: ለዚህ ህዝብ ሊታዘንለት ይገባል:: ስለዚህ ፅዋው ሞልቶ ሳይፈስ ማስተዋል ለሁላችንም ይበጃል እላለሁ:: እግዚያብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ!

## መሪን መገንባት...

ከገፅ 9 የዞረ

in Germany" ሲል ዘ ኢኮኖሚስት ፅፏል:: የቶማስ ኤዲሰንን ፅናት በምሳሌነት ባነሳሁበት ወጌ መሪዎች ከስህተት እንደሚማሩ አብራርቻለሁ:: ለአንድ መሪ ስህተት ኩፍኝ ነው፤ ይወጣለታል:: መሪነት የሂደት ውጤት ነው:: በአንድ ቀን የሚገኝ ተሰጥኦ እንዳልሆነ ደግሞ አንቶኒ ሮቢንሰን የተባለው አነቃቂ መሪ "ስኬት የጥሩ ውሳኔ ዉጤት ነው፣ ጥሩ ውሳኔ ደግሞ የብዙ ልምዶች ውጤት ነው:: ብዙ ልምዶች ደግሞ የብዙ ጥሩ ያልነበሩ ውሳኔዎች ድምር ውጤት ነው" ሲል ይመክራል::

መሪና ስህተት ቤተሰቦች ናቸው:: ለምሳሌ ኤዲሰን አምፖል ያበራው በ1000ኛ ሙከራው ነው ይባላል:: ታዲያ ከተሰጠው 1000 ስህተቶች በ500ኛው ስህተቱ ቢያቆም ኑሮ ቀሪ 500 ስህተቶቹን ላይሳሳት አምፖልንም ሳያበራ ይኖር ነበር::

ስህተቱን ተሸክሞ:: ስለዚህ መሪ ስህተት አይፈራም:: ባለመፍራቱ ደግሞ አብረውት ሊኖሩ የነበሩትን ስህተቶች በአጭር ጊዜ ይጨርሳቸዋል:: እድሜው ከፍ እያለ ሲመጣ ስህቶቹ ቀንሰዋል ማለት አንችል ይሆን? ኤዲስን በዚህ ዘርፍ የሁል ጊዜም መሪ ነው:: እኔ ግን በለቱ የውይይቱ ርዕስ ሆነው የነበሩት አንዳንድ የፖለቲካ ስህተት ሰሩ የተባሉ ሰዎች በዚህ መልኩ ቢታይላቸው ደስ ይለኛል፤ለነ ልደቱ አያሌው፣ለነብርሀኑ ነጋ፣ ለነብረቱካን እና ሌሎችም ብዙ የቅንጅት ... መሪዎች:: ካልሆነ እነዚህ ሰዎች ከታረሙ በኋላም እንደቀድሞው ስናያቸው ብንኖር ስህታችንን ይዘን በመኖር መሪነት የምናጣው እኛ ነን ማለት ነው:: እነሱን ይቅር ብሎ ወደ ትግሉ ማሰለፍ ግን መሪነት ነዉ::

ቤንያሚን ናታንያሁ በሌላ ዙር ለድጋሚ የኤስራኤል ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ ሲመረጥ "A man a country loves to hate" (ለመጠላት የተወደደ ሰዉ) ሲል የገለፀው ዘ-ኢኮኖሚስት መጽሔት ነበር:: የሰውየው መመረጥ መወደዱን ያሳያል:: ነገር ግን ለዚህ ቦታ መመረጡ ደግሞ የመረጡት ሰዎች ራሳቸው በብዙ የቦታው ውሳኔ እንዲያጉረመርሙ፣ እንዲበሳጩበት ብሎም እንዲጠሉት ያደርጋል:: መሪያችን ከምንለው ሰው /ቡድን/ተቋም ብዙ ብዙ ነገር እንጠብቃለን:: ደግሞ ምርጫችን ስለሆነ መጥፎ መጥፎውን አንወድም:: በመሆኑም በያንዳንዱ ጥሩ ያልሆነ ነገሩ በኛነት ስሜት እንወቅሳለን::

እስካሁን በመጣሁባቸው አንቀፆች ውስጥ ‹አለቃ› የሚል ቃል አልተጠቀምኩም:: ላወራ የፈለግሁት ስለ መሪነት ነበርና:: አዲሱ አካዳሚያዊ ተዋስኦ (Discourse) ሰዎች ከአለቃነት አሰራር (managerial function) ወደ መሪነት አሰራር (leadership function) እንዲሄዱ ይጠይቃል:: መሪ የሚያዝ እና በህግ ማዕቀፎች ብቻ ተጠብቆ የተለዩ (exceptional) የሚባሉትን ማስተናገድ የማይችል አይደለም:: መሪ በተከታዮቹ በመተማመን ተመሪዎቹን ያበቃል፤ በራስ መተማመናቸውን ይገነባል::

መሪ ማለት ሰርቶ የሚያሳይ ምሳሌ ሆኖ የሚቀርብ እና ለራሱም በስራ የሚጠመድ እንጂ ሰዎችን በመቆጣጠር የሚጠመድ አይደለም:: ለዚህ ነው ዛሬ በኛ ሀገር አልሳካለት ያለውን የ«BPR» ፅንሰ ሀሳብ በመጀመሪያ ከተረዱት ህዝቦች፣ የጃፓኖች ሰራተኞች "ለመሪዎቻችን ስራ ስጧቸው፤ እነሱን አይተን እንሰራለን" ያሉት:: አለቆች በስራ ሲጠመዱ መሪ የሚሆኑ ይመስላል:: አሁንም ለአለቆቻችን ስራ ካልተሰጠ በቀር በ «BPR» ፈንታ እየረቀቀ ነው የሚባለው "የዜጎች ቻርተርም" ተመሳሳይ ዕጣ ይገጥመዋል ብዬ "አሟርታለሁ":: ከሁሉም በላይ መሪነት በየትኛውም ስፍራና ዘርፍ የሚያጋጥም የህይወት አንዱ ገፅ ነው::

መሪዎች አዲስ ነገር በማግኘትም ይማራሉ:: በአሁኑ ወቅት በአለማችን የግኝቶችና የፈጠራዎች ፍጥነት ከሰው የመጠቀም አቅም እያለፈ ነው:: አንዱ ግኝት ስለመገኘቱም ሳንሰማ ሌላ እሱን የሚያስንቅ ይመጣል:: ፈረንጆቹ «planned obscelence & obscelence» የሚሉት ይህ ችግር እንደኛዎቹን የባሰ ያጠቃል:: በመሆኑም መፍጠር እንኳ ቢቀር የተፈጠሩትን ነገሮች ከተቻለ የመጠቀም ክህሎት ካልተቻለ የማወቅ አቅም መፍጠር መቻል አለብን:: ይህን ማድረግ መሪ ለመሆን የሚደረግን ጥረት ቢያንስ ያግዛል ብዬ አሁን አምናለሁ:: በኋላ እንዴት እንደማምን መድረሱ ውስጥ ነው::

# የብርሃንና ሰላምን ማተሚያ ድርጅት ባወጣዉ የውል ረቂቅ ላይ በአንድነት ፓርቲ የህግ አማካሪ የተሰጠ አሰስተያት

1.የረቅቁን ይዘት በሚመለከት

ከቀረቡት አስራ አንድ አንቀጾች ዉስጥ ህግን ያልተከተሉት አንቀጾች 3(4)፣9 እና 10 ናቸዉ:: እነኝህ አንቀጾች በዋነኝነት በዉል ሰጭና በዉል ተቀባይ መካከል የዉል መነሻ ሆነዉ ልቀርቡ የሚገቡ ሳይሆኑ በሌላ የመንግስት አካል ስልጣን ስር የሚወድቁ ናቸዉ::

2.ረቂቅ ዉሉ ከኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንጻር

ከኢፌዴሪ ህገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 ክፍል ሁለት ‹‹ዴሞክራሲያዊ መብቶች›› በሚለዉ አንቀጽ 29 የአመለካከትና ሀሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት በሚለዉ ድንጋጌ ስር በንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽና የማሰራጨት መብት ተረጋግጧል::ይህንን መብት ለመገደብ የሚደረግ ማንኛዉም ድርጊት የተከለከለ መሆኑን ተመልክቷል:: ከዚህ የህግ ድንጋጌ አንጻር ስንመለከተዉ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በኩል የቀረበዉ ረቂቅ የዉል ሰነድ ይህንን የህገ መንግስት ድንጋጌ የሚቃረን ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም::

3. ከ1996 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የወንጀል ህግ አንጻር የረቂቅ ዉል ህጋዊነት

በዚህ የወንጀል ህግ መጀመሪያ ታላቅ ክፍል ጠቅላላ ክፍል አንደኛ መጽሃፍ ክፍል ሁለት ምዕራፍ አራት በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት በሚደረጉ ወንጀሎች ተካፋይ መሆን በሚለዉ ስር ከአንቀጽ 42 እስከ አንቀጽ 47 በግልጽ እንደተመለከተዉ የአታሚን ሀላፊነት ከህትመት ሥራ ላይ በተገናኘ የሚደነግግ ወይም ይህን አይነት ዉል እንዲገባ የሚያስገድድ ህግ የለም:: ብቸኛዉ አታሚን ሀላፊ ሊያደርግ የሚችለዉ በአንቀጽ 43(1)ሠ) ላይ የተመለከተዉ ነዉ:: ይሀዉም የፕሬስ ዉጤቱ በተሰራጨበት ወቅት የፕሬሱን አሳታሚ ለማወቅ ከልተቻለ በአሳታሚ ምትክ ኃላፊ የሚሆነዉ አታሚዉ ይሆናል የሚለዉ ነዉ:: ከዚህ ተነስተን ስንመለከተዉ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ በኩል የቀረበዉ ራሴን ከኃላፊነት ለመከላከል ያደረኩት ነዉ የሚለዉ መከራከሪያ የህግ መሰረት ስለሌለው ተቀባይነት የለዉም::

5. ረቂቅ ዉሉ ከመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነጻነት አዋጁ ቁጥር 590/2000 አንጻር

በዚሁ አዋጅ ክፍል አምስት ህጋዊ እርምጃዎችን ስለመዉሰድ በሚለዉ ስር ከአንቀጽ41 ስለተጠያቂነት ከሚለዉ አንስቶ እስከ አንቀጽ 42 የእገዳ እርምጃዎችን ስለመዉሰድ እስከሚለዉ ድንጋጌ ድረስ ከህትመት ጋር ተያይዞ ለሚፈጸም የወንጀል ድርጊት አታሚ አንድም ሀላፊነት የለበትም:: የመቆጣጠርም ሆነ በህትመቱ ላይ እገዳ የማድረግ ስልጣን አልተሰጠዉም::ሀላፊነት ሳይኖር ተጠያቂነት የለም:: ስለዚህ በብረሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በኩል የቀረበዉ የዉል ረቂቅ ራስን ለመከላከል ሳይሆን ሌላዉን ተዋዋይ ሆን ብሎ ጉዳት ለይ ለመጣል የቀረበዉ ሀሳብ ስለሆነ የሕግ መሰረት ወይም መነሻ የለዉም::

6. ረቂቅ ዉሉ ከፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንጻር

ምናልባት ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት የረቅቅ ዉሉን አስመልክቶ ሊያቀርብ የሚችለዉ ይህንን የፀረ ሽብር አዋጅ ሊሆን ይችላል:: በዚህ የፀረ ሽብር አዋጅ አንቀፅ 6 ሽብርተኝነትን ስለማበረታታት በሚለዉ ድንጋጌ ስር ሆን ብሎ ወይም በግዴለሽነት ያተመ እንደሆነ ከ10 እስከ ሀያ አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል ይላል:: ይህም ቢሆን ተጠያቂነት የሚኖረዉ ሆን ተብሎ ወይም በግዴለሽነት ከተደረገ ብቻ ስለሆነ ያቀረበዉ ረቂቂ ዉል ተገቢነት የለዉም::

ማጠቃለያ

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ያቀረበዉ ረቂቅ የዉል ሰነድ ራሱን ከተጠያቂነትና ሀላፊነት ለመከላከል ሳይሆን የሌሎችን መብት ለማጣበብ ሆን ብሎ የፈጸመዉ ስለሆነ የህግ መሰረት የለዉም::

# የታክሲ ስራ በሂደት ይጠፋል

**-የታክሲ ባለንብረቶች**

ብሩክ ከበደ

በአሁኑ ጊዜ በከተማ ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ አንዳንድ ስማቸው እንዳይገለፅ የፈለጉ በዘርፉ የተሰማሩ ዜጐች አሁን ባለው የአሰራር ሂደት ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ከዘርፉ ለመውጣት እንደሚገደዱ ገለፁ::

እነዚህ ግለሰቦች ከዘርፉ ለመውጣት የሚገደዱበትን ምክንያት ሲገልፁም ተገልጋይና አገልጋይ በትክክል ተማምነው የሚከፍሉት ክፍያ ቢኖር የትራንስፖርት ዘርፍ ብቻ መሆኑን ገልፀው አሁን እየተሰራ ያለው የአገልግሎት ክፍያ እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ በየጊዜው እየናረ የሚሄደው የነዳጅ ዋጋና መለዋወጫው ኪሳራ እንጂ ትርፍ የለውም ብለዋል::

አያይዘውም “መለዋወጫ ስንገዛ ከቫት ውጪ እንድንገዛ የማይደረግ በመሆኑና በየጊዜው እየናረ የሚሄደው የነዳጅ ዋጋም ህዝብን እንደማገልገላችን አስተያየት ስለማይደረግልን ችግራችን ከለት ወደለት እያባባሰው መጥቷል” ሲሉ ይገልፃሉ:: ባሁኑ ጊዜም በከተማ ውስጥ ከ13 ሺህ የሚበልጡ በታክሲ ስራ ላይ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች እንዳሉ ይገመታል::

# የውድሮ ዊልሰን ማዕከልና የአሜሪካን ኤምባሲ ተወካዮች ከአንድነት ፓርቲ ጋር ተነጋገሩ

የዉድሮ ዊልሰን ኢንተርናሽናል የስኮላሮች ማዕከል/Woodrow Wilson International Center for Scholars/ ተወካዮችና የአሜሪካን ኤምበሲ ተወካይ ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ አመራሮች ጋር ተገናኝተዉ መነጋገራቸዉ ታወቀ:: የፓርቲዉ ህዝብ ግንኙነት ሀላፊ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስታወቁት ‹‹ትላንት ከሰዓት በኋላ በ10 ሰዓት ላይ የማዕከሉ ተወካዮች እና የኢምባሲዉ ተወካይ በፓርቲዉ ጽህፈት ቤት ተገኝተዉ ተነጋግረዋል›› ብለዋል::

የፓርቲዉ የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ እንደተናገሩት ‹‹የማዕከሉ የግጭቶች አፈታትና የእርቀሰላም የመፍጠር ተግባር የሚያከናዉን ሲሆን በአሁኑ ወቅት በኢትዮጲያ ዉስጥ ያለዉን ችግር በዉይይት ለመፍታት እንዲቻል ከኢህአዴግና ተቃዋሚዎች ጋር ማደራደር እንደሚፈልጉ ተወካዮቹ የፓርቲዉን አመራሮች ጠይቀዋል›› ሲሉ አስረድተዋል:: ዶ/ር ኃይሉ በማያያዝ ስገልፁ ‹‹የፓርቲዉ አመራሮች በበኩላቸዉ የተወካዮቹን ጥረት እንደሚያደንቁ ገልፀዉ ፓርቲዉ በዉይይት እንደሚያምን ፣ በዚህች ሀገር ተቀምጦ ዉይይት ማድረግ ካልተቻለ የሚፈጠረዉ አደጋ ሁሉንም ይዞ ይጠፋል ብለን እንደምናምን ተቀምጦ መወያየት የስልጣን ጥያቄ ሳይሆን አገርን የማዳን ጉዳይ መሆኑን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለዉይይቱ ዝግጁ መሆናችንን ገልፀንላቸዋል›› ብለዋል:: ተወካዮቹም ‹‹ኢህአዴግን አነጋግረዉ መግባባት ላይ መድረሳቸዉን ገልፀዋል:: ቀጥለዉም ሌሎች ፓርቲዎችን ለማነጋገር ማቀዳቸዉን ተናግረዋል›› ብለዋል:: በዉይይቱ ላይ የዉድሮ ዊልሰን ኢንተርናሽናል የስኮላርሽፕ ማዕከልን በመወከል ዳኪይ ዲዩፍ፣ የአፍሪካ ፕሮግራም ተባባሪ ስቲቭ ማክዶናልድ፣ የአፍሪካ ፕሮግራም አማካሪና አቅም ግንባታ ፕሮጀክት አማካሪ ዳይሬክተር ሲገኙ የአሜሪካን ኤምባሲን በመወከል ጄፈሪይ ግረሃም የፖለቲካና ኢኮኖሚ ምክትል አማካሪ የተገኙ ሲሆን ፓርቲዉን በመወከል አቶ አስራት ጣሴ የፓርቲዉ ዋና ፀሀፊ፣ አቶ ተመስገን ዘዉዴ የፓርቲዉ የዉጭ ጉዳይ ሀላፊ ፣ ዶ/ር ኃሉ አርአያ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊና ኢ/ር ዘለቀ ረዲ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ መገኘታቸዉን ለማወቅ ተችሏል::

# የአንድነት ፓርቲ ህዝብ ግንኙነት ለአመራር አባላት ስልጠና ሰጠ

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) የህዝብ ግንኙነት ኮሚቴ በአዲስ አበባ ለሚገኙ ወረዳዎች ሰብሳቢና የህዝብ ግንኙነት አመራሮች ስልጠና ሰጠ:: ስልጠናውም እሁድ ሚያዝያ 21 ቀን 2004 ዓ.ም በፓርቲ ዋና ጽ/ቤት አዳራሽ አንድ ቀን ሙሉ የፈጀ እንደሆነ የፓርቲው የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል::

የስልጠናውን ዓላማ በተመለከተም የህዝብ ግንኙነት ስራ ምንነትና ሚና ከፖለቲካ ፓርቲ አኳያ ምን መሆን እንዳለበት እና ለህዝብ ግንኙነት ሥራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ለይቶ በማወቅ ላይ ያተኮረ እንደሆነ ተጠቁሟል::

በስልጠናውም የአንድነት ፓርቲ በአዲስ አበባ ወረዳዎች የሚገኙ የየወረዳው ሰብሳቢዎችና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች ተሳትፈዋል:: ስልጠናውም አንድነት ፓርቲን በቀጥታ ከህዝብ ጋር ማስተዋወቅ፣ የአባላትን አቅም መገንባት፣ ለድርጅቱ የገቢ ምንጭ መፍጠር፣ በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ደካማና ጠንካራ ክንውኖችን መለየትና አማራጭ ሐሳብ ማቅረብ እንዲሁም ለፓርቲው የመረጃ ምንጭ መሆን ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን የደረሰን መረጃ አመልክቷል::

## ትላንት . . . ከገፅ 1 የዞረ

እስከረፋድ በባንኮቹ በራፍ ላይ ተሰልፈ ነበር:: ባንክቤቶቹ በአንፃሩ አገልግሎት ሳይሰጡ አርፍደዋል:: ለባንኩ ቅርበት ያላቸው ምንጫችን ባንኩ የሲስተም ችግር ሳያጋጥመው እንዳልቀረ ጠቁመውናል:: የዝግጅት ክፍላችን ጉዳዩን ከባንኩ ለማጣራት ያደረገው ጥረት ሳይሳካ ቀርቷል::

## ብርሃንና ሰላም . . . ከገፅ 1 የዞረ

ጨምረውም ‹‹ይህ ውል በማተሚያ ቤቱ የተዘጋጀ ሳይሆን የኢህአዴግ የተቀነባበረ አፈና ነው›› ብለዋል:: ሌላው የጋዜጣው ኤዲቶሪያል ቦርድ አባል ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በጉዳዩ ላይ ከማተሚያ ቤቱ ኃላፊዎች ጋር ለመወያየት ቀጠሮ መያዛቸውን ተናግረው ‹‹ይህ ረቂቅ ውል ሙሉ ለሙሉ ቅድመ ምርመራን የሚያሰፍን ነው ›› ካሉ በኋላ የፓርቲያቸው የህግ አማካሪ ውሉ አታሚውን የማይጠቅምና የሌሎችን መብት ለማጥበብ ያለመ በመሆኑ ምንም አይነት የህግ መሰረት እንደሌለው መግለፁን አብራርተዋል::

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
UNITY FOR DEMOCRACY & JUSTICE (UDJ)

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

የገቢ ማሰባሰቢያ የራት ፕሮጋራም

አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየታገለ ይገኛል:: ለትግሉ ስኬት የእርስዎ ድጋፍ ወሳኝ ነው::

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ የራት ዝግጅት ፕሮጋራም አዘጋጅቷል:: ለመግብያ ባለ 1,000፣ 500ና 300 ብር መግቢያ ካርዶች ተዘጋጅተዋል::

በራት ፕሮግራሙ ላይ ታዋቂ ግለሰቦች ንግግር ያደርጋሉ:: የእራት ግብዥው ግንቦት 24 ቀን፣ 2004 ዓ.ም. ይደረጋል። የሆቴሉ ስም ግንቦት 13 ቀን 2004 ዓ.ም. በሚወጣው ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ላይ ይገለፃል::

በውጭ ሀገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያኖች በሀገር ውስጥ በሚኖሩ ቤተሰቦችና ጓደኞች አማካኝነት ካርዱን መግዛት ትችላላችሁ::

ለተጨማሪ መረጃና ካርድ ለመግዘት በሚከተለው አድራሻ ይጠቀሙ፤
በቢሮ ስለክ ቁጥር 011-840-08-11
በተንቀሳቃሽ ስልክ 091-161-84-34
ኢ-ሜል:
andientfinance@yahoo.com
ወይም andinet@andinet.org

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
የሂሳብ ቁጥር፡ 510
ንብ ባንክ ዑራኤል ቅርንጫፍ

ለዴሞክራሲ ስርዓትና ለህግ የበላይነት መመስረት፣ ሁላችንም ካርዱን በመግዛት ድርሻችንን እንወጣ!